*ነበር (ሉቃስ 2:25 26)። (ዐዉደ ዕለት መስከረም 24 ቀን 1966 ዓም)*

የመልእክቱን ይዘት በአንድ ዓረፍተ ነገር ያጠቃለሉት ‹‹*የስምዖን ዕድል ፈንታ ለእኔም ይሆናል*›› በማለት ነበር።
በእርግጥም ዶ/ር ብርሃኑ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጽናናትንና በአጠቃላይም ምድሪቱ ከክህደት መንፈስ ፀድታ ለወንጌል ሥራ ምቹ የምትሆንበት ዘመን እንደሚመጣ ተረድተው ነበር። እስከዚያች ቀን ድረስ ለትምህርት ወይም ለሥራ በተላኩባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ከትምህርት ወይም ከሥራ ውጭ ያለውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ስደተኛዋን ቤተክርስቲያን በማገልገል፣ ወገኖችን በማፅናናትና በማሰባሰብ ነበር።

እዚህ ትረካ ጫፍ ላይ ስንደርስ ከዋና ርዕስ ጉዳያችን ወጣ ለማለት ልንገደድ ነዉ፤ ለአንባቢዉ የአዕምሮ መደላድል የሚሆኑ ታሪካዊ ክስተቶችን ለመዳሰስ ስንል። በተለይም የደርግ ዘመን ተብለው ከሚታወቁት 17 ዓመታት ወዲህ ነፍስ ያወቁ ወገኖችን አይገርምም። ‹‹*የኮሚዩኒዝም መንፈስ፣ ስደተኛዋ ቤተክርስቲያን፣ ወገኖችን ማፅናናት፣ በህቡዕ ማሰባሰብ፤ ብሎ ነገር ምን ማለት ነው?*›› ማለታቸዉ አይቀርምና። በሁለተኛ ደረጃም የዚያን ዘመኑን ውክቢያ፣ ኹካታ፣ መንፈሣዊ/ሥጋዊ ትርምስ በአጭሩ መግለፁ ባለ ታሪኩ ያለፉበትን ማህበራዊ ዐውድ፣ መንፈሳዊ ዉጊያ፣ የከፈሉትን ዋጋና የህይወት ጥንቃቄና ፅናት ወለል አርጎ ያሳያልና እነሆ!





# 5. ዘመነ መብሰክሰክ (1967- 1983)

## *5.1. ክርስቲያን ሰው ነው*

ክርስቲያን ሰው ነው፤ ክርስቲያን የአንድ አገር ዜጋ ነው፤ ክርስቲያን ተወልዶ ያደገበት ማሕበረሰብ አባል ነው። ክርስቲያን በክፉም ሆነ በደግ፣ አገሩ ወይም የገዛ ማሕበረሰቡ በሚያልፍበት ውጣ ውረድ ውስጥ ድርሻ አለው። ለክፉም ሆነ ለደግ በሚከናወኑ ሁኔታዎች፡- አዕምሮው፣ መንፈሱ፣ ስሜቱና ፈቃዱ ይነካል፤ ሰው ነውና። ከዓለሙ ሁለመና ተገንጥሎ ለብቻው የቆመ ፍጡር አይደለምና።

ይህ ክፍል ዶክተር ብርሃኑና ዘመነኞቹ እንዲሁም የዚያን ዘመን ትውልድ አባላት የነበሩ ክርስቲያኖች ያለፉባቸዉን አጠቃላይ ሁኔታዎችንና ከዚህም የተነሣ በእምነታቸው፣ በአመለካከታቸውና በማሕበራዊ ሕይወታቸው ላይ ያረፉትን መልካምና መልካም ያልሆኑ ተፅዕኖዎች በአጭሩ ለመግለፅ ያለመ ነው።

### *የሥርዓተ ዘውድ- ፍፃሜ*

የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት 252ኛው ንጉሥ የነበሩት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 80ኛ አመት ልደታቸውን ሐምሌ 16 ቀን 1964 ዓ.ም አከበሩ። የነፃነትና የጥቁር ሕዝብ ኩራት ምልክት አድርጎ የሚቆጥራቸው መላው የአፍሪካ አኅጉር ልደታቸውን አከበረ። ዝናቸውን ለመዘርዘር ሲባልም በርካታ

የአፍሪካ አገራት ጎዳናዎችና የተለያዩ ተቋሞች በስማቸው ሰየሙላቸው።

አገር ውስጥ ግን ሁኔታው መላው አፍሪካ በዓይነ ልቡናው ከቀረፀው ምስል ተቃራኒ የሆነ ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ጥግ ላይ ደርሶ ነበር። ይህ ከ1950ዎቹ መጀመሪያዎቹ አንስቶ እየተባባሰ የመጣው ተቃውሞ ሥርዓተ ዘውዱን እንደ ቀንቁን በልቶ ውድቀት አፋፍ ላይ አቆመው።

ለሃምሳ ዓመታት ያህል አገሪቱን የመሩት ንጉሠ ነገሥት የዕድሜ እርጅና ልክ መንግሥታቸውም ጃጅቶ ስለነበር ሕዝቡን ለተቃውሞ የአነሳሳው ኋላ ቀር አስተዳደር፣ የተዛባ የፍትሕ ሥርዓት፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ድንቁርና የተዛባ የመሬት ይዞታ እና የመሳሰሉት ችግሮቿን የመፍታት አቅም አጣ። የሕዝቡ ቁጣ በተለይም የለውጥ ፈላጊዉ ወጣት ተቃውሞ ወደ አመፅ ተሸጋገረ።

## 5.2. የተቃውሞዉ ቅኝት

በ1950ዎቹ መጀመሪያ ከዓለም ሕዝብ ሢሦ ያህሉ በኮሚዩኒዝም ቀጥተኛ ቀንበር ሥር ወድቆ ነበር። የኮሚዩኒዝም መንፈስም ብዙ አገራትን በተለይም አብዛኞቹን ታዳጊ አገራት የተጠናወተበት ወቅት ነበር። ለሁሉም አገራዊ ችግሮች መፍትሔ ሁሉም ሰው እኩል የሚሆንበት ሥርዓት ‹‹ኮሚዩኒዝም›› ብቻ እንደሆነ ተደርጎም ይሰበክ ነበር።





ከዚህም የተነሣ ኮሚዩኒዝም የአገሪቱን የሺህ ዓመታት ማሕበራዊና ባህላዊ እሴቶች ሳይገድቡት ሩብ ክፍለ ዘመን በማይሞላ ዕድሜው ምድሪቱ ላይ ከአጥናፍ - አጥናፍ ገነነ።

ወደ ኢትዮጵያችን ሁኔታ ስንመለስ ኮሚዩኒዝም ስተት ብሎ ገብቶ ለማንሰራራት የበቃው የተማሪዎችንና ‹‹የተራማጅ›› ምሁራንን አቀንቃኝነት ተጠግጎ ነዉ። ይሁን እንጂ ስለ ኮሚዩኒዝም ያላቸው ዕውቀት በአብዛኛው ግልብና በተግባራዊ ጭብጡ በእዉን የሚመሰክሩለት ሳይሆን በንድፈ ሃሳብ ሃተታዉ ብቻ እንዲሁ የሚማልሉለት ርዕዮተ ዓለም ነበር።

ውስን የንድፈ ሃሳብ ዕዉቀታቸዉም ቢሆን እንደ ገደላ - ገድል የሚያነበንቡት እንጂ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ የሞከሩና የበቁ ነበሩ ለማለት አያስደፍርም።

ከዚህ የተነሣ ለብዙዎቹ አብዮተኞች፦ ኮሚዩኒዝም *በዕውቀት የሚመሩበት* መርሆ መሆኑ ቀርቶ *በማያውቁት መንፈስ የሚነዱበት አባዜ* (Syndrom) ዓይነት ነገር ሆነባቸው። ከማርክስ፣ ሌኒን፣ ማኦ መጻሕፍት አብረቅራቂ ጥቅሶችን መሸምደድና መልሶም በአደባባይ እንዳሉ ማነብነብ (Vomitout ማድረግ) የጊዜው ፋሽን ሆነ።

ቆም ብሎ ማሰብ፣ አማራጭ ምልከታ መሰንዘር፣ ከታሪክ፣ ከባህልና ከወግ ጋር ለማዛመድ መሞከር ብርቅ ሆነ። በታረሙ ቃላት መናገርና ስመ እግዚአብሔርን ማንሳትማ በኋላ ቀርነት ተፈርጆ ነበር። እናም - ሁሉ ነገር ብስክስኩ ወጣ። ከሚያያዙት ይበልጥ የሚበጣጠሱት ብሔራዊ እሳቤዎች በዙ።

እንግዲህ እነ ወጣቱ ብርሃኑ የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ ትህርታቸውን የተከታተሉት በዚህ *ማሕበራዊ - ሥነ ልቡናዊ* ቀውስ ውስጥ ነበር።

## *5.3. ዘመነ ደርግ - መባቻ*

ከላይ የጠቀስነዉ የሕዝባዊ ተቃዉሞ እንቅስቃሴ መስፋፋትና ፅኑ የለውጥ ፍላጎት የዐፄ ኃይለ ሥላሴን *(የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ)* መንግሥትን ክፉኛ አንገዳገደው።

በአንዳንድ የታሪክና የፖለቲካ ተንታኞች አመለካከት ዘውዳዊዉ አገዛዝ ፍፁም የተናጋው የለውጥ አራማጆቹ ልሂቃን በጋራ አመለካከት ለጋራ ድል የሚያበቃ ዝግጅት ሳይኖራቸው ነበር። ስለሆነም ሥርዓተ ዘውድ ሲከስም ምን ዓይነት መንግሥታዊ ሥርዓት? በእነማን? እንዴት?. . . ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ አልነበሩም።

በተቃራኒዉ ዘውዱ ከተፍረከረከ በኋላ በስመ ተቃውሞ አንድ የነበሩት እንጭጭ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ጎሣ ተኮር ስብስቦች፣ አልፎ አልፎም ግለሰቦች ሁሉ እርስ በርሳቸው ወደ ሚጠላለፉበት እጅግ ዘግናኝና ደም ያቃባ የዘመን ምዕራፍ ተሸጋገሩ።

በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ይህቺ ጥንታዊት አገር የራሳቸውን ደመወዝ ለማስጨመር በተሰባሰቡ ወታደራዊ ኮሚቴ አባላት እጅ ወደቀች።





ስብሰቡም ‹‹ደርግ›› ተሰኝቶ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓም ግርማዊ ጃንሆይን ከዙፋን አውርዶ ራሱን ሥልጣን ላይ አቆናጠጠ።

***

*መሬትን ለሕዝብ ያደረገውን አዋጅ ጨምሮ አንዳንድ መሠረታዊ ለውጦችን ከማምጣቱ በስተቀር የደርግ አገዛዝ የዕብድ ገላጋይ ሆኖ ምድሪቱን በደም ያጨቀየበት ደወሉ ተደወለ።*

የሞት መልአክ የደውሉ መረዋ ድፍን ሀገሪቱን ሞላ። ጥድፊያ ሆነ፣ መዋከብ ሆነ። ‹‹ፖለቲካዊ የዋህነት›› ገነነ። ሌላው ቀርቶ ከቀድሞ የኮሚዩኒስት አገሮች ጥፋትና ልማት ለመማር የሚያስችል ፋታ ጠፋ።

በመሠረቱ ማርኪዝም በካፒታሊስት ሥርዓተ ማሕበር ውስጥ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በመተቸትና በማውገዝ የተመሠረተ ርዕዮተ ዓለም ነው። ስለሆነም ሥርዓቱ የተመሠረተበትን ባህላዊ ዳራ፣ ፍልስፍና፣ ማሕበራዊ እሴቶችና ቅርሶች በጥልቀት ሳይረዱ ማርኪዝም - ሌኒንዝም ባፈለቀው ትችት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የዚችን አገር ችግሮች ለመፍታት መነሣቱ በራሱ እብደት ነበር። ብቻ ምድሪቱ አበደች።

## *5.4. ስደት - በኮሚዩኒዝም አርጩሜ*

በቁጥር አንድ መቶ ሃያ ከሚሆኑት የደርግ አባላት መካከል ስለዚህ የግራ ክንፍ ፖለቲካ አማካኝ እውቀት ያላቸው ከአንድ እጅ ጣት አይበልጡም። ይልቁንም የሚበዙት *ዘውድ*

አምላኪዎች፣ አገር ወዳዶች፣ ኩሩ ወታደሮች . . . ነበሩ እንጂ። የትምህርት ደረጃቸውም ቢሆን ከማንበብና መጻፍ እስከ ዲፕሎማ ቢዘልቅ ነው። እርግጥ ነው አንድ ወይም ሁለቱ የዩኒቨርሲቲ የማታው ክፍል ትምህርት ተማሪዎችና ምሩቆች ነበሩ።

ስለሆነም አጠቃላይ አዕምሯዊ አቅማቸዉ ውስብስብ የሆነውንና እርስ በእርሱ በረቂቁ የተቆራኘውን የአገሪቱን ችግር ለመፍታት የሚያስችላቸዉ አልነበረም። የፖለቲካ አቋማቸውም ቢሆን በግለሰባዊ መረዳት የተመሠረተ ሳይሆን ከእነሱነታቸው ውጪ በነበረው የአመለካከት ነፋስ የሚገፋ ነበር።

በመሆኑም የወቅቱ ኮሚኒስታዊው መንፈስ እንደ ነዳው የሚነዳዉን ለዉጥ ፈላጊ ሕዝብ ለማስደሰት ሲሉ ጭምር አገሪቱ የምትመራበት ርዕዮተ ዓለም ሶሺያሊዝም እንደሆነ ታህሳስ 12 ቀን 1967ዓም በይፋ አወጁ። በዚህ አዋጅ የኮሚኒዝም መንፈስ *ግዘፍ ነስቶ* (አካል ሆኖ) ተገለጠ። የአገሪቱን ባህላዊ እሴቶችንና ወጎች ለማፈራረስ የክፉ ኃይላት እጅና መሣሪያ ሆኖ ተነሣ። ከማይረሱት ድካሞቹ አንዱም እንደ ቻይና ሁሉ ‹‹የባህል አብዮት›› በስውርና በግልፅ ማካሄዱ ነበር።

***

የባህል አብዮቱ አራማጆች ያዝ - ለቀቅ ባለ ስልት በሃይማኖትና በአማኞች ላይ በተለይም በወንጌላውያን ቤተ እምነቶችና በተከታዮቻቸው ላይ ስደት ማካሄድ የጀመሩት ከ1968 አንስቶ ነበር። ሁኔታዎች በፍጥነት የተለዋወጡት





የወቅቱ ‹‹ተራማጆች›› በተበታተነ መንገድ ሃይማኖት ላይ የሚያንፀባርቁት ጥላቻና ማንቋሸሽ ተቋማዊ ገፅታ ከያዘበት 1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው።

በዚህ ዘመቻ የተደናገሩ የወንጌል አማኞች ቁጥር ቀላል አልነበረም። ደርግ በተቀነባበረ ሁኔታ ሊያካሄድ ያለውን ስደት ለመቋቋም ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ ወንጌላውያን ቤተክርስቲያናት የተለየ መሰናዶ አድርገዋል ለማለት የሚያስደፍሩ መረጃዎች የሉም። የተቀነባበረውን ስደት በተባበረ ሁኔታ ለመመልከት እንደ መጀመሪያ ሙከራ የሚቆጠረው ‹‹የኢትዮጵያ አብያተ ቤተክርስቲያናት መተባበር ጉባዔ›› የሚባለውና በ1969 ዓም የተቋቋመው ሕብረት ነበር። መሥራች አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ነበሩ።

| ተ.ቁ | የቤተ ክርስቲያን ስም | የምዕመናን ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን | 15,000,000 |
| 2. | የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስትያን | 500,000 |
| 3. | የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን | 500,000 |
| 4. | ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ | 410,000 |
| 5. | የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን | 25,000 |
| 6. | የሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን | 15,000 |
| 7. | ብርሃን ወንጌል መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን | 8,000 |
| 8. | መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን | 5,000 |
| 9. | ሠፈረ ገነት ቤተ ክርስቲያን | 2,000 |

*(ምንጭ ኢሉሄና ሃሌሉያ፣ 1992)*

የትብብሩ ዓላማ፡-

- ወንጌልን ያለ ምንም ፖለቲካዊ ይዘትና ህፀፅ በንፁህ አቋም መስበክ፤
- አገራችን ኢትዮጵያ የጋራ እናታችን እንደ መሆኗ መጠን በማሕበራዊ ኑሮ ለሚደርስባት ችግሮች ሁሉ የጋራ አስተዋፅዖ ለማድረግ እንዲቻል፤
- የሕብረተሰብዓዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሰጠንን መብትና ነፃነት በሥራ ለመተርጎም፤(ተፃራሪዉን እያደረገ መሆኑን መቼምልባቸዉ ሳያዉቅ አይቀርም።)
- በአንዳንድ የኢትዮጵያን ሕልውና በሚቃረኑ አገሮች በሃይማኖት ምክንያት የሚነዙ ወሬዎች በአብያተ ክርስቲያናት መተባበር ጉባዔ ዋጋ ቢስ እንዲሆኑ ለማድረግና ያለንን መብትና ነፃነት ለመግለፅ መሆኑን ጉባዔው መቋቋሙን አስመልክቶ ይፋ የሆነዉ ሰነድ ይገልጻል።

ትብብሩ በወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የወቅቱ ፕሬዘዳንት ቄስ ጉዲና ቱምሣ እየተመራ ለሦስት ዓመት ያህል የዘለቀ ቢሆንም በውስጡ በተፈጠረው አለመቻቻልና በውጪም በነበረበት ብዙ ዓይነት ተፅዕኖ ምክንያት ከሰመ። ትብብሩ የከሰመበት ጊዜ ደርግ ‹‹የባህል ዘመቻዉን›› አጠናክሮ ሊያካሂድ በቆረጠበት ወቅት ጋር መገጣጠሙ አሳዛኝ አጋጣሚ ነበር።





*ሊቀ መንበር መንግሥቱ የባህል ዘመቻውን በድል አድራጊነት ካልተወጡ አብዮቱ የተነሣበትን ዓላማ እንደማያሳካ በማረጋገጥ ሕዝቡም በዘመቻው እንዲሳተፍ* በ1970 በአደባባይ ከለፈፉ በኋላማ የመከራው ዶፍ መዝነቡ እርግጥ ሆነ።

ሰማያት በስደቱ ደመና ጠቆሩ። ዘመኑን ሁሉ የመንግሥት እስትንፋስ ቅጥያ ከመሆን ዘሎ የማያውቀው የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃን የዘመቻውን የክተት ነጋሪት ሳያቋርጥ መጎሰምን ሥራዬ ብሎ ተያያዘዉ። እናም እሳቱ ላይ ቤንዚን ጨመረበት። እንዲህ እንዲህ እያለ፡-

> *ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በልዩ ልዩ ስሞች የሚጠሩ ሃይማኖቶች ወደ አገራችን ገብተዋል። . . .ከእነዚህ <u>መጤዎች</u> ውስጥ አንዳንዶቹ <u>የሚያስተምሩትና የሚፈጽሙት ድርጊት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው</u> መስሉ ያሰገምታቸዋል።*
>
> *ዜጋውን በስንፍናና በራስ አለመተማመን አዘናግቶ ‹‹ይህ ዓለም ቤቴ አይደለም›› ብሎ እንዲቀመጥ ገፋፍተዋል። ተማሪ እንዳይማር በተዘዋዋሪ መንገድ ከልክለዋል።*
>
> *... ተማሪዎች ያለፈውን መንግሥት ለመጣል በሚታገሉበት ጊዜ እንዚህን ሃይማኖቶች የሚያመልኩ አብዛኛዎቹ ወጣቶች አልተሳተፉም (ይህ ነጥብ በመጠኑም ቢሆን እዉነትነት አለዉ)።*
>
> *የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውልድ የሆኑ የዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊስቶች ጥቅም አስከባሪዎች የሕረተሰብ አእምሮ አኮላሾች፣ የአብዮቱ ቀልባሾች የሆኑትን ዛሬ 'በልዩ ልዩ ዘዴ በአብዮታችን ላይ ደባ ሲሰሩ በቸልታ ልናልፋቸው አንችልም።*

በተጨማሪም:-

‹‹መጤ፣ የኢምፔሪያሊዝም ወኪል፣ ሜታ ፊዚሺያን፣ የሲ አይ ኤ ኤጀንት . . . የሚሉ አዳዲስ ቅፅል ስሞችና ክርስቲያኖችን የማዋረጃ ቃላትና ሐረጋት በመፈልፈል ሰድቦ ለሰዳቢ ከመስጠት አልፎ የፀረ ሃይማኖት ዘመቻው በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ላይ ብቻ እንዲያነጣጥር በማድረግ ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት የመገናኛ ብዚኃኑ ነበሩ::

## 5.5. የቅዱሳን ዕምባ፣ ምርኮና ብዝበዛ

በተበታተነ ስልትና መልክዓ ምድር ብልጭ ድርግም ሲል የነበረው ስደት ዓይን ባወጣ ሁኔታ በ1970 ዓ.ም ተገለጠ:: እግዚአብሔር በራሱ ምክንያት እንደ ቅሬታ ከአስተረፋቸው የጥቂት ቤተ እምነቶች ዋና ጽሕፈት ቤቶችና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በስተቀር የአብዛኞዎቹ አምልኮ ሥፍራዎች ሁሉ በዘመቻ ተዘጉ:: ለምዕራባውያን የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞችና ለዲፕሎማቲክ ማሕበረሰብ እይታ ቅርብ የሆኑ ማለት በአዲስ አበባ በዙሪያዋ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት እንኳ አልተረፉም:: በክፍለ ሐገራት፣ በአውራጃዎችና በየዳር አገሩማ ባሉት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ላይ የወረደው ግፍ ቃላት ከሚገልፁት በላይ ነበር::

በብዙ መቶ የሚቆጠሩ አጥቢያዎች ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጀምበር ነበር የወደሙበትን ወላይታን እንደ ምሣሌ መጥቀሱ በቂ ነዉ:: አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ሕንፃዎቻቸው ፈረሱ፣ ንብረቶቻቸው ተዘረፉ፣ የመዘምራን የሙዚቃ መሣሪያዎች





ለየወረዳውና ቀበሌዉ የኪነት ቡድኖች ተከፋፈሉ፤ አብዛኛዎቹ መሪዎቻቸው ታሰሩ፣ የወህኒ ቤቶች ቅጥር ግቢዎች ለማስተናገድ የሚችሉትን ያህል አማኞች እየተያዙ ታጎሩ፣ ተገረፉ፣ ተዋረዱ፣ ተሰደቡ፣ *አሳዳጁ አሳዳጁን በርታ* አለው::

አንዱ ቀበሌ *‹‹አንድ መቶ የኢምፔሪያሊስት ምንደኞች በቁጥጥር ስር አድርጌልሃለሁ››* የሚል ሪፖርት ለአለቆቹ መላኩ ከተሰማ፣ በጊዜዉ የአሠራር ፊሊጥ የሌላው ቀበሌ ሹመኛ ምርኮዉን ወደ አንድ መቶ ሃያ ከፍ ለማድረግ ተግቶ ሠራ:: ለካስ ሰው ህሊናውን ከሸጠ ወዲያ እንስሳነቱ ነውር አይመስለውም!! እንዲያ ባይሆንማ:-

- መጽሐፍ ቅዱስ ቤታቸው ስለ ተገኘባቸው ብቻ ወንድም ወንድሙን ይገርፋልን?
- ‹‹እግዚአብሔር ይመስገን›› የሚል የሰላምታ ምላሽ ስለ ተናገሩ ወገን ወገኑን ይዘልፋልን?
- አሜሪካ ወይም ምዕራብ አውሮፓ ስለ ታተሙ ብቻ ቤተ መጻሕፍት ሙሉ የአጠቃላይ እዉቀት መጻሕፍት በእሳት መቃጠል ይገባቸዋልን?
- ሰው እንዴት ፊደል የቆጠረበትን የትምህርት ተቋም የቤተ ክርስቲያን ንብረት ስለሆነ ብቻ ያፈራርሳል? ሌላም፣ ሌላም - ሌላም!...

ይህ ወቅት ሌላም ለትዝብት የሚበቃ ትውስታ ትቶልን አልፏል:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል:-

- ክርስቲያኖች መሸሻና መጠጊያ አጥተው ሲባዝኑ ወደ ጓዳቸው አስገብተው፣ አብልተውና አጠጥተው፣

መሣፈሪያ ‹ፈራንካ› አስቋጥረው ወደ ሌላ አካባቢ የሸኙ ሙስሊሞች የተገኙበት ወቅት ነበር፤

- ልጁ ካድሬ፣ አባት ክርስቲያን አገልጋይ ወይም የተገላቢጦሹ የመሆን ዕጣ የገጠማቸው ቤተሰቦች አንዱ ሌላውን ሲያሳድድ ወይም አንዱ ከሌላው ሲሸሽ የታየበት ወቅት ነበር፤

በቤተ ክርስቲያን ውስጥም፡- አይረባም የተባለው ፀንቶ የቆመበት፣ የቆመው የወደቀበት፣ እረኛው ‹‹አንዷን ጠቦት ይዞ ዘጠና ዘጠኙን የበተነበት፣›› ‹‹በጎቹ እረኛውን›› ያስማሩበት አደናጋሪ ወቅት ነበር፡፡በአጠቃላይ የመከራው ዘመን፡-

- የብዙዎችን እምነት ያጎበጠበት፣ ተስፋቸውን ያከሰመበት ወቅት ነበር፤
- በሌላዉ አንፃር፡- መከራው በሚያስገርም ሁኔታ ብዙዎች እንደ ወርቅ ነጥረው እንዲወጡ የአደረገበት ጨለማ ነበር፡፡
- አንዳንዶቹ የታሠሩበትና የተገረፉበት ወንጀል መዝሙር ስለ ዘመሩ ነበር፤ ነገር ግን በአሳዳጃቸው አኮርባጅ እየተገረፉም የዘመሩ ፅኑዓን የታዩበት ወቅት ነበር፤
- ሌሎች የተገረፉት የወንጌልን ቃል ስለ መሰከሩ ነበር፤ ነገር ግን እየተገረፉም ለገራፊዎቻቸው የፍቅርን ወንጌል በመስበክ ወንጃዮቻቸውን ከእሳት ነጥቆ የማውጣትን ያህል ፅናት የአሳዩበት ወቅት ነበር፤

ይህ ሁሉ የመከራ ዝናብ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ከቶም አላጠፋትም፤ ሊያጠፋትም አይችልም፡፡ ይልቁንም ቤተ





ክርስቲያን ወደ ህቡዕ ጉብታ በቤተ ክርስቲያን የወንጌል ታሪክ አዲስ ምዕራፍ የከፈተችበትን ዘመን ጀመረች፡፡ መቶ እና ሺህ ሆኖ በአንድ ቦታ መሟሟቁ ቀረና አንዷ አጥቢያ በአስር፣ ሃያ፣ ሰላሳም ጓዳዎች (የቤት ውስጥ አምልኮዎች) ውስጥ መሸገች፡፡ የስደቱ እምቢልታ ከመጎሰሙ አንድ ዓመት ያህል ቀድሞ ዘማሪ ደረጀ ከበደ፡-

*ሲያፍኑት ይብሳል፣*
*ሲያጠፉት ይነዳል፣*
*ገና በእኛ ወንጌል ዓለም ይዳረሳል፤*

ሲል እንደዘመረው ወንጌል የተዳፈነ መሰላቸው እንጂ ይብሱኑ መቀጣጠሉን አሳዳጆቹ ፈፅሞ አልተገነዘቡትም ነበር፡፡

እንግዲህ እዚህ የታሪክ አጋጣሚ ላይ ቤተ ክርስቲያን ወደ ህቡዕ ገባች፡፡ ዘመኑም የራሱን የወንጌል አርበኞችና ሐዋርያትን ፈጠረ፡፡ ስለ ጌታ ሥራ ሲሉ መስዋዕት ለመሆን ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ የወንጌል ባለ አደራዎች እጥፍ ድርብ ሆነው ተነሡ፤ ጌታ መንፈስ ቅዱስ አስነስቷቸዋልና፡፡ እናም የወንጌል አገልግሎትን ያህል ታላቅ ኃላፊነት ተሸክመውና ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀው የጨለማውን ጊዜ ተሻግረው አሻገሩ፡፡ የራሳቸዉን ነፍስ አድነዉ ሌሎችን እንዴት እንደ አሸጋገሩ የዶክተር ብርሃኑ ሕይወትና የአብነት ጉዞ ዉስጥ የምናይበት ምዕራፍ ወደ ፊት ይጠብቀናል፡፡

ለጥቂት ደቂቃዎች አንባቢው ወደ እዚህ ምዕራፍ የመንደርደሪያ ማስታወሻ ልቡናውን እንዲመልስ እንጋብዛለን፡፡ ክርስቲያን ሰው ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን ሕብረት የተሞላች እውነት ነች፡፡ በዜያ ዙሪያ ገባው

በተበታተነና መያዣም መቋጫም ባልነበረው የአገራችን አጠቃላይ ዐውድ ውስጥ የአለፉ ሰዎች ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ተነክተው አልፈዋል፤ በግልም በቡድንም። በመሠረቱ የማንኛውም ማሕበራዊ ዐውድ የተፅዕኖ አሻራውን የሚያትመው ደመ ነፍሳዊ በሆነ ረቂቅ ሥነ ልቡናዊ ሂደት ነው። ስለሆነም ተፅዕኖው የአረፈባቸው ሰዎች ከተግባራቸው ወይም ከአመለካከታቸው ጀርባ ‹‹የሆነ›› ዐውድ ጥላ እንደሚያጠላባቸው እንኳን በእውቀት አይገነዘቡትም። ሳይገነዘቡት ግን ‹ሆነውት› ይገኛሉ። በነፃነት ማግሥት የነበረችውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእነዚያ ክፉ ቀናት ጥላ - እንዴቱን አጥልቶባት እንደነበር በዶ/ር ብርሃኑ ፈለግና በክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ ጥቂት - በጥቂት እናያቸዋለን።





# 6. በጥቂቱ የታመነ

## 6.1. ባሌ - በጥቂቱ (1967 — 1970)

ከአናብስት አፍ - ከሞት መንጋጋ፣
ከቀትር ጋኔን - ከሌት አደጋ፣
ከሚዘገንን - ከሞት ሸለቆ፣
የሚያወጣ አምላክ
    ከክፋት ልጆች - ልጁን ፈልቅቆ፡. . .
    እንዴት ድንቅ ነው!? *(ባልታተመ የመዝሙር ጥራዝ)*



*ዶ/ር ጥበቡ (መካከል) ዶ/ር ሚልኪያስንና ዶ/ር ብርሃኑን ለመጎብኘት ጎባ መጥተዉ በነበረበት ጊዜ የተነሱት ፎቶ*



ዶ/ር ጥበቡ (መካከል) ዶ/ር ሚልኪያስንና ዶ/ር ብርሃኑን ለመጎብኘት ጎባ መጥተዉ በነበረበት ጊዜ የተነሱት ፎቶ

በ1967 መጨረሻ ላይ የተማሪነትና የአገልግሎት ሀ - ሁ ዘመኑን ደመደመ:: ወጣትነትንና የአፍለኛ እድሜ ፈተናዎችን፣ ትምህርትን፣ የትርፍ ጊዜ ሥራን፣ የቤተሰብ ኑሮን መደገፍን፣ የትርፍ ጊዜ አገልግሎትን አጣጥሞና አቻችሎ በሁሉም መስክ ዉጤታማ ሆኖ ነዉ እዚህ የደረሰዉ:: በዚህ ሰብዕናዉ ከሚደነቁት አንዱ ከመሠረቱ የሚያውቁት አቶ ሚናስ ብሩክ ናቸዉ:: ስኬቱን እንዲህ ይመሰክሩለታል:-

> *‹‹ብርሃኑ ከዊንጌት እኔ ከሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት አልፈን እንደገና ዩኒቨርስቲ ተገናኘን:: በዚያን ጊዜ የክርስቲያን ተማሪዎች ቁጥር በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መበራከት የጀመረበት ወቅት ነበር:: ነገር ግን ወጣትነትን፣ መንፈሳዊነትንና ትምህርትን ጎን ለጎን ይዞ አጣጥሞ መሄድን የአወቀበትና እንደ አርዓያ የሚቆጠር ሰዉ ከመካከላችን ቢኖር ብርሃኑ ነዉ::*
>
> *እንዲያዉም ሚዛን መጠበቅ አቅቷቸዉና ወደ መንፈሳዊነቱ በጣም አጋድለዉ፣ ሚዛን በመልቀቃቸዉ በዩኒቨርስቲ ጥሩ ዉጤት ማምጣት የአልቻሉ፣ የተባረሩም አይጠፉም:: እሱ ግን በትምህርቱም ፊተኛ ሆኖ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱም ምንም ሳይጎድልበት፣ ከሁላችን በላይ ጊዜ ሰጥቶና አገልግሎ ዉጤታማ ሆኖ ተመረቀ:: በሁሉም ነገር አርአያ ሆኖ ኖረ... ብቻ ያዉቅበታል!››*

የአቶ ሚናስን ምስክርነት ከሚያጸኑልን ቅርብ ሰዎች መካከል ታዋቂዉ የሕክምና ባለሙያ እና የሕክምና ሳይንስ መምህሩ የነበሩት ፕሮፌሰር ጀማል አብዱልቃድር ናቸዉ::

> *‹‹ብርሃኑ ትኩረቴን ከሚስቡ፣ ከማልረሳቸዉና ሞዴል (አርዓያ) ከነበሩ ተማሪዎቼ አንዱ ነበር:: በመምሕራኑ ዘንድ የተወደደ፣ በተማሪ ጓደኞቹ የተከበረ ነበር:: ሃይማኖተኛ እንደነበረም*





> *አዉቃለሁ፤ በሃይማኖቱ ዙሪያ የሚጠበቅበትን ለማሟላት ብዙ ጊዜ እንደሚሰጥ ሁላችን እናዉቃለን:: ትምህርት አቀባበልን በተመለከተ ግን የተሟላ ሰዉ ነበር:: አሁን አሁን ሳስበዉ እንዴት በአምላክ የታደለ ሰዉ ነዉ ነበር? እላለሁ::››*

የፕሮፌሰር ጀማል አብዱልቃድርና የአቶ ሚናስ አባባል ጆን ሊትል የተባሉ አፓሎጀቲክ'ን ሀሳብ ያስታዉሰናል:: እኚህ ምሁር እደሚሉት አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ የሕይወት ልምምድ ሲጀምሩ ጭልጥ ብለዉ ይወሰዱና የራሳቸዉን አዕምሮ በገዛ ራሳቸዉ ይገድሉታል፤ (ሂደቱን (Intelecetual sucied ይሉታል) አኗኗራቸዉም ደመነፍሳዊ ይሆናል:: በመሠረቱ እግዚአብሔር የሰዉን ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ ከፍ-ከፍ ይል ዘንድ የቸረዉ ድንቅ ስጦታ ቢኖር አዕምሮ ነዉ:: ይህንን ድንቅ ሀብት ማስተኛት (ማደንዘዝ) ወይም ያለመጠቀም ወይንም መግደል እግዚአብሔርን መበደል ነዉ:: በተፃራሪዉ አዕምሮን ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎች ጥቅም በትክክል መጠቀም የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ከማስፋፋት እኩል ነዉ::

የጆን ሊትልን ትንተና እንደ ቱንቢ (መለኪያ) አድርገን ብንወስደዉም የተሟላ የሰብዕና ቁመና የነበረዉ ያ ወጣት ገና በሃያ ሦስት ዓመት ዕድሜዉ በሕክምና የመጀመሪያ ዲግሪውን በ1967 ዓ.ም ተቀበለ:: ከዕንቦቃቅላነቱ አንስቶ የባሪያውን ሕይወት ከውጭም ከውስጥም የአበጃጀውን ጌታዉን እያመሰገነ በሠለጠነበት ሙያ አገሩን ለማገልገልም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ራሱን ለአዲስ የሕይወት ምዕራፍ አዘጋጀ:: (ጸሐፊዉም ወደ እርሰዎታዉ ተመለሰ)::

***

ወቅቱ ታዋቂው ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን በግለ ታሪኩ ‹‹ማሕበራዊ እብደት›› ከሚለው እንቅስቃሴ ጋር የሚነጻጸረው አብዮት የፈነዳበት ጊዜ እንደነበረ ያስታውሷል። ነውጥ ነበር፤ ማዕበል ነበር። በፊቱ ቆሞ ያገኘውን ኃይል ያለ ምንም ማመንታት የሚጠራርግ የውክቢያ ዐውሎ ነፋስ የታጠቀ ዘመን ነበር።

ለዘመኑ ክፋት ላለመጋለጥ ሁሉም ሀበሻ በስጋትና በሰቀቀን የሚኖርበት ወቅት ነበር። ከአዲስ አበባ ወጣ ባሉ ቁጥር ሽብሩ የበረታ ይሆናል፤ ለአደጋ የመጋለጡም ዕድል የሰፋ ይሆናል። ስለሆነም ከየትምህርት ተቋሙ የሚመረቁ ወጣቶች ከከተሞች በተለይም ከአዲስ አበባ ርቆ ላለመሄድ የተቻላቸውን ያህል ይጥራሉ። የውሸት የሐኪም ምስክርነት የሚያቀርቡ፣ የዘመድ አዝማድ አማላጅ የሚልኩ ወይንም የፖለቲካውን ሥርዓት የሚጠቀሙ በርካቶች ነበሩ። ላቅ ያለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ወይም እንደ ሕክምና ያሉ ተፈላጊ ሙያዎች ለአጠኑት ደግሞ ይህ መንገድ ፈጽሞ ዝግ አልነበረም።

ዶ/ር ብርሃኑ እና የቅርብ ጓደኞቻቸዉ የሆኑት ዶ/ር ጥበቡና ዶ/ር ሚልኪያስ የመረጡት ግን *ጠባቢቱንና ቀጥተኛዋን* መንገድ ነበር። ያም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚያወጣውን የዕጣ ድልድል በጸሎት መጠባበቅን ነበር። ጠቢቡ ሰሎሞን እንዳለዉ ‹‹ዕጣው በጉያ ተጣለ፤ መደቡ/ምደባው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ (ምሣ 16፡ 33)። ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር ጥበቡ ኃ/ሥላሴ ዕጣ ያወጡት በአንድ ቀን ነበር። ዶ/ር





ብርሃኑ ባሌ ክፍለ ሐገር ጎባ ሆስፒታል ደረሳቸው። ከቀናት በኋላ ደግሞ ዶ/ር ሚልኪያስ ተቀላቀሏቸዉ። የቅርብ ጓደኛቸዉና በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውም ለተወሰኑ ጊዜያት አንድ ቤት አብረዉ የኖሩት ዶ/ር ጥበቡ ቀብሪ ደሐር ደረሳቸው። (በነገራችን ላይ ዶ/ር ጥበቡ ኃ/ሥላሴ ከባሌ ጎባ ከተመለሱ ከወር በኋላ ነበር በኢትዮጵያና በሱማሌ መካካል በነበረው ጦርነት ተማርከው ለ11 ዓመታት በሱማሌ ምርኮኛ ሆነው የቆዩት)።

ወደ ተነሳበት እንመለስ። ዶ/ር ብርሃኑ ውለው ሳያድሩ ሐምሌ 11 ቀን 1967 ዓ.ም ጎባ የሚያደርሳቸዉን አዉቶብስ ተሳፈሩ።

### ባሌ - በመንገደኛው ብዕር

እዉነትም ዶ/ር ብርሃኑ ከማንኛዉም ነገር፣ በማንኛዉም ጊዜና ሁኔታ አዳዲስ እዉቀቶችን ለመቅሰም የተዘጋጀ ክፍትና ብሩህ አዕምሮ የታደሉ ሰዉ ናቸዉ። ይህንንም ሰዎች ከመሰከሩላቸዉ በላይ ከተግባራዊ ሕይወታቸዉ ለመረዳት ከሚያስችሉን አሻራዎቻቸዉ መካከል የአዉቶብስ ጉዞአቸዉን ወደ ሕይወት ትምህርት ቤት የለወጡበት ጥልቅ ተሞክሮ ነዉ።

ዶ/ር ብርሃኑ በአዉቶብስ ሲጓዙ በተመለከቷቸዉ የባሌ መልክዓ ምድርና ተፈጥሮአዊ ትዕይንት ተመሰጡ። ከዚያ ወዲያ፦ ተራራዉ - ተራራ፣ ሸለቆዉ - ሸለቆ፣ እንስሳቱም - እንስሳት ብቻ ... ሆነዉ አልታይ አሏቸዉ። ከተፈጥሮ ትዕይንት የተማሩትን ሥጋዊና መንፈሳዊ ትምህርት

ከህይወታቸዉ ማዋኸዱም ሆነላቸዉ። እስቲ በራሳቸዉ ብዕር የመዘገቡትን እናንብብ፡-

***ወደ ባሌ . . .***

*...የመንገዱ ግራና ቀኝ በእግዚአብሔር ፍጥረታት ሕያው ሆኗል። የቁጥቋጦዎች ቅጠል ለምልሟል፤ አብበዋልም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፍሬ እንደሚያፈሩ ተስፋ ያደርጋሉ። ጌታ ሆይ! እኛም እንዲሁ በሜዳ እንዳንቀር እርዳን!*

*. . . ቀስ በቀስ ወደ ተዋበዉ ሸለቆ መግባት ጀመርን፤ በዚ፤ ስፍራ የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ መጣች። እንዴት በተፈጥሮ ዉበት የበለጸገ ሸለቆ ነው!! ከሸለቆዉ የግራና ቀ፣ ጅረት እየፈለቀ እጅግ የጠራና የሚያስጎመዥ ዉኃ ያለ አንዳን ድምፅ በየአቅጣጫው ቁልቁል ይሽሎከሎካል።*

*በዚህ ጊዜ፡- ‹There shall be peace in the valley› የሚለው መዝሙር በደምብ ገባኝ። በልቤ ዜማ ጨማመርኩበት። በቁሜም በእንቅልፍም ልቤም ስዘምረው ለብዙ ቀናት ቀጠልሁ። . . .*

*. . . በአበባ የተዋቡ ዕፅዋት ለምለሙን ሜዳና መስኩን አሳምረውታል። ሣሩ አረንጓዴ ነው። ምድሪቱ ላይ ከአረንጓዴ በስተቀር የሚታይ ነገር የለም። አቤት! የታደሉ ከብቶች በዚህ ባማረና በውኃ በበለጸገ ሸለቆ ውስጥ ተዘልለው ተሰማርተዋል። እኛስ ጌታ ሆይ መቼ ነው እንደ መንጋ በለምለም መስክ ላይ የምንሰማራው?*

*. . . ከብቶቹ የሚበሉት በቂ ሣር ስላላቸው በጸጥታ ተሰማርተዋል። አንዱ ከሌላው ጋር አይዋጋም፤ ለምንስ ይጣላሉ? ለያንዳንዳቸው የሚያስፈልጋቸው አላቸዋ!!*

*እኛ ሰዎች ግን እርስ በርሳችን እንራኮታለን። ምክንያቱም ሸለቆአችን ደረቅ ነው። የምንሠማራበትና የምንመገበውም*





*በበቂዉ የለንም። ስለዚህም የወገኖቻችንን ሥጋ ልንበላ እንታገላለን! . . .*

*. . . አቤት! ማሣው ሁሉ ታርሷል። ገበሬዎችም ዘርን ዘርተዋል። እነዚህ ገበሬዎች የሕያዉያን አምላክ እግዚአብሔር ዝናብ ያዘንብልናል ብለው ተስፋ በማድረጋቸዉ ነዉ ዘራቸዉን የዘሩት። ወደ እነዚህስ ተዘልለው ወደ ተቀመጡት (የባሌ ሰዎች) የምሥራቹን ይዞ የወረደ ማን ይኖር ይሆን?!*

*ረባዳዉን መሬት ጨርሶ (በኩራት) ወደ ተከፈሰዉ ተራራማ የመሬት ወገብ እየተጠመጠመ ለመዉጣት መኪናው ሲያዘግም የእግዚአብሔር ታላቅነትና ግርማ ወደ ሃሳቤ ይመጣልኝ ነበር። (እግዚአብሔር የተራሮች ላይ ተራራ! ያለዉ ማን ነበር!?)*

*ዲንሾ የምትባለው አነስተኛ ከተማ በዚህ በተዋበው ሸለቆ ውስጥ ነው ያለቻው። በዲንሾ አንድ ክርስቶስን አምኖ ‹የዳነ› ቤተሰብ መኖሪያ ቤት አየሁና ተባረክሁበት። ይህ ቤት አሰራሩ ለቡና ቤት እንደሚመች ሆኖ ነበር፤ አሁን ግን በአዉራ መንገዱ ትይዩ ያሰውን በርና በረንዳው በሙሉ ታሽጎ ሰዎች ከጀርባዉ በኩል ያለዉን በር እንዲጠቀሙ ተደርጓል። ማነው ይሆን ጀርባውን ከዓለም መልሶ ፊቱን ለጌታ የሚያሳይ? (ሐምሌ 11 ቀን 1967 ዓም)*

የዶ/ር ብርሃኑ ልብና አዕምሮ ለመማር ምን ያህል ክፍት እንደ ሆነ ከሚያሳዩን የብዕራቸዉ ጠብታዎች የላይኛዉ የዐዉደ ዕለት ማስታወሻ አንዱ ነው። (ለመሆኑ ለሥነ ጽሑፍ ጥበብ ታስቦ ቢጻፍ ምን ያህል የተራቀቀ ድርሰት ይወጣዉ ነበር?)

እግዚአብሔር ግራ ቀኙን ለማያውቁት ፍጡራኑ ለእንስሳቱ ጭምር በሚያደርገው ቸርነት እንዲህ እየተመሰጡ ኅባ ገቡ። የወንደ ላጤ ኑሮአቸውን ጀመሩ።

## *6.2. ኑሮ በባሌ*

ኑሮአቸውን እንደ አልባሌ ሰዉ ግልፅና ቀላል አድርገዉ ለመጀመር ደፋ ቀናዉን ጀመሩ። በጊዜዉ ከነበረዉ ማሕበራዊ ዐዉድ የተነሣ ከጥቂት ቀናት በላይ ሆቴል ማረፍና መመገብ አልፈለጉም ነበር። እና...

> *«. . .እንደ ደረስኩም ቤት ኪራይ እንዳልተገኘልኝ ሰማሁ። ልቤ ለመስመጥ ጀመረች። በውስጤ 'ግን እግዚአብሔር መንገድ ይኖረዋል የሚል እምነት ነበረኝ። አዎን መንገድ ነበረው።*
>
> *በሆስፒታሉ የሚሠራ አንድ ሰው ስለ ከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች በተነገረው አዋጅ መሠረት የነበረበትን ቤት ባለቤቱ አስለቅቆት ራሱ ወደ ነበረበት ቤት ዞሮ ነበር። ከዚህ ቤት ጋር ተለጥፋ የተሠራች ሁለት ክፍል ቤት እንድገባ ወደ ማታ ጊዜ መጣና ነገረኝ። በዚህ ጊዜ እንደገና ተፈታሁ። ሃርሞኒካ ድንገት አንስቼ ያለ ዓላማ ሳዜም ራሴን አገኘሁት። ተመልሼ ሳስተውል «I know He cares for me ...» የሚለው ዜማ ነበር። ጌታን በጣም አመሰገንኩ።*
>
> *. . .ሐምሌ 23 ቀን 1967 ዓም ጌታ ለጊዜው ወደ አዘጋጀልኝ ቤት ገባሁ። አሁን ለራሴ ምግብ ማዘጋጀት ይገባሁ። ውድ እህቴ አበባ አዘጋጅታ ያስያዘችኝ ስንቅ እንዴት ብዙ በረከት ሆነኝ!! ጊዜ ሲጠብበኝ ዳቦ ቆሎ እበላለሁ። ትንሽ ሰፋ ያለ ጊዜ ሲኖረኝ በሶ እበላለሁ።. . . ድርቆሽና ብዙ ኪሎ ቅንጬም አለኝ። በችግሬ ጊዜ እነዚህ ሁሉ ሲደርሱልኝ እግዚአብሔርን በጣም አመሰግናለሁ።*





> *. . .እኔ እንኳን ምን ያደርግልኛል ብዬ ልተወዉ የነበረው የዕቃ ማጠቢያ ሸቦ ምን ያህል ጠቀመኝ። ለካንስ መጥበሻዬ አንድ ነገር ከጠበስኩበት በኋላ በሌላ በምንም ሊነጻ አይችልም ነበር። (ዐውደ ዕለት ሐምሌ 1967)*

**ሲጥ በላሁ!**

> *«ዛሬ ዳቦ ሱቅ ሊገኝልኝ ስላልቻለ ሲሞሊና ለመጥበስ ሞከርኩ። ከዚያም አመስግኜ ለመብላት አንገቴን ሳቀረቅር በእጄ የያዝኩት ሹካ አምልጦ ሊወጋው ሊጡ በአንድ በኩል ወጣ። ለካንስ ሊጡን ሳቦካ በደንብ ስላላቀጠንኩት በደንብ አልበሰለም ነበር። እኔም በጸሎቴ ውስጥ በትክክል እንዳልሠራሁትና ሊጡንም ቢሆን እንድበላ በጸጋው እንዲረዳኝ ጌታን ጠየቅሁ። ከዚያም ሊጡን በደስታ ተመገብኩ። ጥቂት ቆይቶ ሊያቅለሸልሸኝ ሲጀምር በጌታ ስም ገሰጽሁት። ረጋልኝም።» (ነሐሴ 6ቀን 1967)*

**መኮረኒ በላሁ**

> *«ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ መኮረኒና ምስር ቀላቅዬ ለመሥራት ሞከርኩ። ሽንኩርቱን ከመጠን በላይ ስላበሰልኩት በሙሉ እንደገለባ ደረቀ። ይህንንም እግዚአብሔርን አመስግኜ በላሁት!» (ነሐሴ7 ቀን 1967)*

**ወጥ እየሠራሁ ሳነብ**

> *«ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ወጥ ሠራሁ። ወጡ እስኪበስል ድረስ ዘካርያስ ምዕራፍ አንድን አነብ ነበር። ‹. . .ለሕዝቡ ንገር፤ እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ ወደ እኔ ተመለሱ ይላል፤. . . እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል፤ እግዚአብሔር ጸባኦት› (ዘካ 1:2 — 3) የሚለው ቃል ባረከኝ። እኛንስ ‹‹ለሕዝቡ ስበኩ (ንገሩ)› የሚለን መቼ ይሆን? ወጡ በሚገባ ነበር የተሠራው። የሚጥም ወጥ፤ የሚጥም ጊዜ። (ነሐሴ 9 ቀን 1967)*

በእንደዚህ ዓይነቶቹ በርካታ ልምምዶች ውስጥ ሳሉ ዶ/ር ሚልኪስ ነሐሴ 1967 ዓ.ም ጎባ ሆስፒታል ተመድበው መጡ። የሁለቱ ሐኪሞች ጓደኝነት የተመሠረተው የጄነራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሳሉ ነው።

ሚልኪያስም እንደ ብርሃኑ በዕጣ ድልድል ነው ወደ ባሌ የሄዱት። አሁን ብቸኝነቱ ቀለላቸው። አብረውም መኖር ጀመሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰፋ ያለ ቤት ሲከራዩ የዶ/ር ሚልኪያስ እህት መጥታ ምግብ ዝግጅት ስለረዳቻቸው የኑሮው ክብደት ተቃለለላቸው። ከጎባ ክርስቲያኖች ጋር ከተዋወቁ በኋላማ ባይተዋርነታቸው ቀስ በቀስ አከተመ።

## *6.3. ክርስቲያናዊ ሕብረት - በጎባ*

ዶ/ር ብርሃኑ ወደ ጎባ ከመሄዳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እስከ 1970 ዓም ድረስ ከክርስቲያኖች ሕብረት ጋር እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ተቋም/ድርጅት ጋር በአባልነት የተያዙ አይመስልም። በእርግጥ የአገልግሎት ሀ - ሁ የቆጠሩት በበቅሎ ቤት ሙሉ ወንጌል የጸሎት ቤት እንደ ነበር ይታወቃል። በሌላ በኩል የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ግልፅ መረዳትና የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን ሲጠባበቁ እንደቆዩ የዕለት ማስታወሻዎቻቸው ይመሰክራሉ።

‹የአገልሎት ሀ - ሁ› በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው በሳሪስ ጸሎት ቤት ከነበራቸው ቋሚ ተሳትፎ ውጭ 1966/67 ዓ.ምን ምናልባት 1968 ዓ.ምን ከፊል ወራት ከወገኖች ህብረት ጋር እንጂ ከተቋማት ጋር ስለነበራቸው ቅርርብ ብዙ ማብራሪያ አልተውልንም። በጎባ ቆይታቸውም እስከ 1968 አጋማሽ





ድረስ እንዲሁ ገለል ማለትን የመረጡ ይመስላል። ነገር ግን የአዳር ጸሎቶችና የተለያዩ መንፈሣዊ ፕሮግራሞች ቤታቸው ውስጥ የአካሄዱ ነበር። ይህን ገለልተኛ ዝንባሌአቸውን የጎባ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ ዶ/ር ሚልኪያስም አልወደዱላቸውም ነበር። አልፎ አልፎም ቢሆን *እንዲህ ስለሆነ ነው፤ ወይም እንደዚያ ለሚል አሉባልታ* በር መክፈቱ አልቀረም። ሁለቱ ሐኪሞች ጉዳዩን አንስተው አንድ ምሽት ሙሉ ተነጋገሩበት ብርሃኑም መዘገቧት።

> *‹‹በዚች በተባረከች ዕለት. . . ከወንድም ሚልኪያስ ጋር ስለ እኔ የሕይወት መንገድ አነሳን። ወንድሜም በሁሉ ነገር ተመሳሳይ እንደሆንን ነገር ግን ጸሎት ቤት አለመሄዴ ቅር እንደ ሚያሰኘው ነገረኝ።*
> *እኔም ሕይወቴ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም አለመሄዴ ጭምር የእግዚአብሔር ፈቃደኝነት ስላለበት ያለ ኪሣራ እንደሆንኩ ነገርኩት። በዚህ ነጥብ ላይ ወንድሜ በራሉት። ደስ አለው።*
>
> *እሱም. . . ‹የሕይወትህ ክፍል ከሆነማ እንዲሁ እንዳለህ ልንቀበልህ ይገባል› አለኝ። አምን በጌታ ፈቃድ ውስጥ እንዳለሁ መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ። ጌታ ይቺን ጊዜ ከወንድሜ ጋር ሰጥቶኛል። ወደ ፊት ግን ጌታ ከአሳስገደደኝ በስተቀር ስለዚህ ጉዳይ አውጥቼ አልናገርም። (ዐውደ ዕለት ታህሳስ 26 ቀን 1968)*

ከሦስት ወራት በኋላ አንድ የጎባ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረቡላቸው። ከበፊቱ ጠንከር ያለ ምላሽ ሰጡ።

> *‹‹. . .በብዙ ነጻነት ምክንያቴን አስረዳሁ። . . .በአገልግሎትም ሆነ በአምልኮ መካፈል እጅግ ቀላል መንገድ መስሎ ቢታያችሁም ለእኔ የሚከለክለኝ እጅ በላዩ እንዳለ*

*ይታወቀኛል። ይህን እጅ ልጠራጠረው አልችልም። ምክንያቱም የምበላውን፣ የምጠጣውን፣ የምተነፍሰውን፣ የምለብሰውንና ሌላም በሕይወቴ የሚያስፈልገውን ሁሉ የማገኘው ከዚህ እጅ ነው። ከጌታ እጅ ሕይወቴን ልሰርቅ አልችልም፤. . .*

*ዝም ብዬ የጌታን ፈቃድ እጠባበቃለሁ። ይልቁንም በጭለማ ውስጥ ሊተወኝ የማይወድ ጌታ እያለኝ ለምን በችኮላ በማላውቀው መንገድ ውስጥ ገብቼ እደናበራለሁ?!›› (ዐውደ ዕለት ሚያዚያ 8 ቀን 1968)*

በጭለማ ውስጥ ሊተወኝ የማይወድ የሚለው አባባል ትዕዛዝ ሆኖባቸው እንጂ የአሉበት ሁኔታ ለእሳቸውም ቢሆን ከባድ እንደሆነ ይጠቁማል።

በሌላ በኩል የጎባ ቤተ ክርስቲያን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደምትዘጋ በተለያዩ መንገዶች ተረድተው ነበር። ዉሎ ሳያድርም በየጎዳናው፣ በየአደባባዩና በየመሥሪያ ቤቱ አማኞችን ማዋከቡ የካድሬዎቹ የዕለት ተግባር እየሆነ መጣ። ስለሆነም ወደ ፊት ሊከሰት ስላለው የከፋ ስደትና መከራ እያሰቡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለ እረኛ እንዳይበተን ውስጥ ለውስጥ የሚደራጅበትን መንገድ ከሚቀርቧቸው አገልጋዮች ጋር መመካከር ጀመሩ።

በእሳቸው እምነት የወቅቱ የጎባ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ስብሰባ ከዚህ በፊት በነበረው ቅርጽና ይዘት መቀጠል የለበትም። ሊቀጥልም አይችልም። ከዚያ ይልቅ በትናንሽ ቡድኖች የተለያዩ የቤት ውስጥ ስብሰባዎች የሚደረጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል።





ይህ በእንዲህ እያለ በጎባ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ላይ ቁርጠኛው ቀን መጣ። ሰኔ 2 ቀን 1968 የጎባ ሙሉ ወንጌል ጸሎት ቤት ተዘጋች። በዚያው ዕለት ምሽት ክርስቲያን ሠራተኞች በእነ ዶ/ር ብርሃኑ ቤት የመጀመሪያውን የምክክር ስብሰባ አካሄዱ። እሳቸዉም የልባቸዉን አወጥተዉ በሚዘረግፉባት ዐዉደ ዕለት ማስታወሻቸዉ፦

*‹‹ፀሐይ በዝርክርክ ኑሯችን ላይ ጠለቀች። ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ መዝረክረክ ነበር። ምን ያህሉ እውነተኛ ፍሬ እንደሆነ የሚያውቀው ጌታ ብቻ ነው።*

*ማንም የማይሠራበት ሌሊት መጣ። አሁን ስደት በሚበዛበት በዚህ ጊዜ የበለጠውን እውነተኛው የእግዚአብሔር ሥራ ይሠራል ብዬ አምናለሁ። ከስደቱ ጋር አዲስ የመንፈሣዊ በረከት ጊዜ እንደመጣ አምናለሁ። ፀሐይ በዝርክርክ ኑሮአችን ላይ ጠለቀች። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን!›› አሉ።*

በምዕራፍ አምስት የተገለጸው ‹ፈታኝ› መንፈስ የጎባን ምድርና አየር ሞላው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ወንጌላውያን፣ አንጋፋ አማኞች ወደ ወኅኒ ወረዱ። ምዕመናኑ የተለያየ የግፍ ፅዋ እንዲጎነጩ ተደረገ። የቆመው ተንበረከከ። የተናቀው በረታ፣ የበረታ የመሰለው ራደ። የጎባ ክርስቲያኖች ወደ አዲስ የአገልግሎት አሰጣጥ ስልት ተሸጋገሩ።

ምን ያደርጉ ዘንድ እንደሚገባቸው የጌታን ፊት ፍለጋ የመጀመሪውን የሕብረት የጸሎት አዳር ነሐሴ 1 ቀን 1968 ዓም በእነ ዶ/ር ብርሃኑ መኖሪያ ቤት አካሄዱ። ሁለቱ ክርስቲያን ሐኪሞች መኖሪያ ቤታቸውን ለጸሎትና ለቤት ውስጥ የአምልኮ ስብሰባዎች ክፍት ቢያረጉም የመሪ

አገልጋይነት ድርሻቸው ግን እስከ 1969 መጨረሻ ድረስ የተፍታታ አልነበረም።

## 6.4. የሕቡዕ አገልግሎት ማዕከል በጎባ

ማን ይናገር - የነበረ...

የመከራው ዶፍ ሲወርድ ደመናው በሚስያገመግምበት ወቅት ሁለት ክርስቲያን ዶክተሮች ጎባ ተመድበው መምጣታቸውን ሰማን። ልክ የእግዚአብሔር መላእክት የመጡ ያህል ደስ አለን። ያኔ ‹ዶክተር› ተብለው የሚጠሩ ክርስቲያኖች ማየት ብርቅ ነገር ነበር። በዚህ የተነሣ የአሉብንን ችግር ሁሉ መጥተው ይካፈሉልናል፣ ብዙ ሁኔታዎችንም ከባለ ሥልጣናቱ ጋር እየተነጋገሩ ያቃልሉልን ይሆናል ብለን ስለ አሰብን ሁላችንም ተስፋ አደረግን።

በዶክተሮቹ በኩል ለወዲያዉ ያገኘነዉ ምላሽ ግን የጠበቅነውን ያህል አልሆንልን አለ። ምዕመኑም አገልጋዮችም ግር ተሰኘን። እነሱ ባይመጡ እኛ ሄደን እናግኛቸው ተባባልንና መኖሪያ ቤታቸው ድረስ እየሄድን ተዋወቅናቸው። ከሁኔታቸዉ ጥሩ ሰዎች መሆናቸውን ተረዳን። በደንብ እየተግባባን ስንሄድ ወደ ቤተ ክርስቲያችን መጥተው እንዲገለገሉና እንዲገለግሉም ጋበዝናቸው።

በግብዣዉ መሰረት ዶ/ር ሚልኪያስ መምጣት ጀመረ። ዶ/ር ብርሃኑ ግን ፈቃደኛ ያለመሆኑ ቅር አሰኘን። ምንም ዓይነት የተለየ መንፈስ፣ የሐሰት ትምህርት ወይም ነቀፋ እንደ ሌለበት እንረዳለን። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለምን አይሳተፍም? እያልን በተደጋጋሚ ተነጋገርንበት። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን አይምጣ እንጂ በመኖሪያ ቤቱም ሆነ በሌሎች ወንድሞች ቤት በሚደረጉ ሕብረቶች በትጋት ይሳተፍ ነበር።






በዚህ ሁናቴ ላለን ቤተ ክርስቲያን ተዘጋ። ሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎቶች ወደ ሕቡዕ ገቡ። የቤት ውስጥ ፕሮግራም ለማካሄድ ሲጀመር ከሁላችንም ይልቅ ከፍትና ምቹ ሆኖ የተገኘው የዶ/ር ብርሃኑ ቤት ነበር። ሄደን ስናነጋግረው ፈቃደኛነቱን አረጋገጠልን።

የዶ/ር ብርሃኑ ቤት በአንድ የአምልኮ ፕሮግራም ጊዜ ከመቶ እስከ ሁለት መቶ የሚሆኑ ሰዎችን ማስተናገድ ጀመረ።

ለስብሰባ ስንሄድ አንዳንድ ሆነን ተራ በተራ መግባት ነበረብን።



ጎባ ከተማ ተከራይተው የሚኖሩበት ቤት

እያንዳንዱ ሰው መቼ? በስንት ሰዓት? እንዴት እንደሚመጣ ይነገረዋል። በአንዱና በተከታዩ ሰው አመጣጥ መካከል የግማሽ ሰዓት ያህል ክፍተት እንዲኖረው አደረግን። ስለሆነም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ለሚደረግ ስብሰባ ሰው መግባት የሚጀምረው ከቀኑ ስድስት



ጎባ ከተማ ተከራይተው የሚኖሩበት ቤት

ሰዓት አካባቢ ነው:: አስቀድሞ የገባው ሰው ሁሉ ለጸሎት ይንበረከካል:: መጽሐፍ ቅዱሱን ያነባል፣ በሹክሹክታ ይፀናናል::

ፕሮግራሙ ሲካሄድም ጮሆ መዘመር፣ መናገርና ሌሎች ድምፆች ማውጣት ለማንም አንፈቀድም ነበር:: ከጥንቃቄያችን ሳይ የእግዚአብሔር ጥበቃ ታክሶበትና ትልቁ የመጽናናችን ምሽግ ሆኖልን ከረመ::

የመሰብሰቢያ ማዕከላችን ከመሆኑም ባሻገር በስደት የነበሩ እህቶችና ሁለት ወንጌላውያን (ጻድቁ አብደና ባደግ በቀለ) ተጠልለው የኖሩት በዶ/ር ብርሃኑ ቤት ውስጥ ነበር:: እነዚህ ወንጌላውያን ወደ ከርቸሌ ከወረዱ በኋላም ከአገር (ከባሌ) እንዲወጡ ሲደረግ ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑ ተሳትፎውን ከፍ አደረገ:: ሰዎችም የበለጠ እየተረዱት መጡ::

መችም ዶ/ር ብርሃኑ በእግዚአብሔር እውነት የተጠቀጠቀ ሰው ነው:: አገሩን ለቆ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በነበረው አገልግሎት ውስጣችን የተከለው ነገር የዓመታት ስንቅ ሆነልን:: በዚያ አስቸጋሪ ጊዜ ራሱንና ቤቱን ለእግዚአብሔር ሥራ አሳልፎ በመስጠቱም ተገልሎ የቆየበትን አንድ ዓመት በእጥፍ ካሠን:: *(ቃለ ምልልስ ፓስተር ሰለሞን ገዛኸኝ ናዝሬት ቁጥር 1 ሙሉ ወንጌል የመሪዎች ጉባዔ ሰብሳቢ)*

*ስደቱ እየተጠናከረ ሄደ አብዛኞዎቹ ወንጌላውያን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወኅኒ ቤት ከተጣሉ በኋላ ግን የአገልጋዮች ብዛት ከአዲሱ የአገልግሎት ዘይቤ ጋር ፈጽሞ አልመጣጠን አለ:: አሁን ‹‹እጠባበቀዋለሁ›› ያሉት የጌታ ምሪት ለዶ/ር ብርሃኑ በግልፅ መጣላቸው:: እንዴት? በሚከተለው መልክ:-*





*‹‹ዕለተ እሁድ 23/4/70 ዓም ወንድሞች ስለ ጌታ ሥራ እንድነጋገር ወደ ቤት መጥተው ነበር:: አንዱን ክፍል ጨረሰንና ወደ ሁለተኛው ርዕስ አለፉ:: ጉዳዩ ቀላል አልነበረም:: በኅባ ሳለሁ በጌታ ሥራ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖረኝ በእርግጥ ልቤ ተዘጋጅቷል:: በመንፈሣዊ ኑሮዬ በከፊልም ቢሆን ባሌ ተስማምቶኛል:: ነገር ግን ከጥቂት ጊዜያት በፊት ወንድሞች ስለ እኔ አቋም ለጥቂት ወንድሞች ገለጻ አድርገው ነበር:: ይኼም በአዕምሮዬ ጥቂት/ጥቁር ነጥብ ጥሎብኝ ነበር:: ይህ ነጥብ እያለ ደግሞ ጉባዔ ፊት መቆም ከበደኝ::*

*በሌላ በኩል ወንጌላውያን ያሉት እስር ቤት ውስጥ ነው:: በዚያው ልክ የእግዚአብሔር ሥራ በዝቷል:: ከእስር ቤት ውጭ ያሉት ወንድሞችም ሸክሙ እንደበዛባቸው ይሰማኛል:: በልቤ ፈቃደኝነት አለ፤ ያቺን ነጥብ ግን (የወንድሞችን) እንዴት ላድርጋት?!*

*ከጭንቀቴ የተነሣ አለቀስኩ:: ወንድሞችም ከእኔ ጋር አለቀሱ:: . . . ወንድሞች በድጋሚ አጽንተው ተናገሩኝ፤ ኃይል ቃል ጭምር:: . . . ከወንድሞች ጋር ከተለያየን በኋላ እራት በላንና ሕይወቴን ለጌታ አስረክቤ ተኛሁ:: ምን ያህል ጊዜ እንደተኛሁ አላውቅም ጌታ የመጀመሪያውን መልእክት ሰጥቶኝ ነቃሁ::. . .*

*በመንፈሴ ደግሞ መንጋው በረገገ መንጋው እረኛ አጣ ወይ? ምነው? የሚለው መዝሙር ይመላለስ ነበር::›› (ዐዉደ ዕለት 24/4/70)*

በዚያ የመገለጥ ሌሊት የተቀበሏቸው መልዕክቶች ሦስት ነበሩ:: ሦስቱም ተለጣጣቂና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ናቸው:: በአንድነት ሲጨመቁ *‹‹አሁን መንጋውን አገልግል!››* የሚል ቀጥተኛ ትዕዛዝ ይወጣቸዋል፤ እናም ታዘዙ:: ፓስተር

ሰለሞን ገዛኸኝ እንዳሉት ዶ/ር ብርሃኑ ተገልለዉ በቆዩበት ወራት በጎባ ክርስቲያኖች ዘንድ ተፈጥሮ የነበረዉን የጥርጥር መንፈስ ያስረሳ ጸጋቸውን በሙላት አካፈሉ።

## 6.5. ሥራ በባሌ

እነ ዶ/ር ብርሃኑ ጎባ ከመሄዳቸው በፊት በሆስፒታል ውስጥ ሲሠሩ የነበሩት ሐኪሞች ከምሥራቅ አውሮፓ - የመጡ ነበሩ። ሀበሾች ለዚያውም ዕድሜያቸው በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ወጣቶች ሲመደቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ስለሆነም በቆዳቸው ንጣት የተለዩ ሞገስ የሰጧቸው ‹‹ፈረንጆች›› ሲለቁ ጎባዎች ቅር ተሰኝተው ነበር። በሌላ በኩል ጎባ ሆስፒታል የባሌ ክፍለ ሀገር ብቸኛዋ ሆስፒታል ነበረች። ከበድ ያለ ሕመም ለደረሰባቸው ሰዎች የመጨረሻው ቅርብና በጥሩ ሁኔታ የተደራጀው የሕክምና ተቋም ሻሸመኔ (ኩየራ) ሆስፒታል ነው። ከባድ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞችም የሚላኩት ወደዚያው ነው። ለምሣሌ፡- በቀዶ ጥገና መገላገል የሚገባት እርጉዝ ሴት ሻሸመኔ እስከምትደርስ ድረስ ሕይወቷም ሊያልፍ ይችላል። የሚደርስባት ስቃይ ግን የሰው ልጅ ከሚሸከመው በላይ መሆኑ የታወቀ ነው።

ለወገኖቻቸው ተቆርቋሪ የሆኑት ሁለቱ ክርስቲያን ሐኪሞች በተደጋጋሚ ያጋጠሟቸው ይህ የሕሙማን ስቃይ ዕረፍት ነሳቸው። ሁኔታውን ለመለወጥም የጎባ ሆስፒታል ተቋማዊ አቅም ከሚፈቅደው በላይ የሆኑ ሙያዊ ውሳኔዎችን በድፍረት መውሰድ ጀመሩ። አስፈላጊ የሕክምና መስጫ ግብዓቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ከባድ ከባድ የሚባሉ በተለይም ከወሊድ ችግሮች ጋር የተያያዙ ቀዶ ጥገናዎችን





አከናወኑ። የሐሜተኞች አንደበት ተዘጋ። ለእነሱ ግን ዝና ወጣላቸው። እንደ ብርቅ መታየት ጀመሩ። ይህ ሙያዊ ድፍረታቸው ሊመሰገኑበት ሲገባ ኋላ ላይ ከዚህ ተፃራሪ ለሆነ ክስ ዳርጓቸዉም ነበር። ክሱም በጦር ሜዳ ቆስለው የሚመጡ ወታደሮች እግር ያለ አግባብ እየቆረጡ አካለ ጎዶሎ አርገዋቸዋል የሚል ነው።

በተረፈ ግን የወንጌል አማኞች ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ የተለያዩ ተግዳሮቶችን እንደ አመጣጣቸዉ ማስተናገድ ግድ ሆኖባቸዉ ነበር። አንዳንዶቹ ተግዳሮቶች ተራና ግለሰባዊ ናቸው። አንዳንዶቹ የክህደት/የኮሚዩኒዝም መንፈስ መንሰራራት መገለጫዎች ናቸው። ሌሎቹም ከማሕበራዊ እሴቶች መናድ እና የፖለቲካዊው ሥርዓት ያሰፈነው የመጠላለፍ አባዜዎች ዉጤት ናቸው። ጥቂቶቹን በዕውደ ዕለት ማስታወሻቸው ውስጥ መዝግቧቸዋል።

> *‹‹ሥራዬን በቀጥታ እየሠራሁ ነው፤. . . በቀበሌ የተመደቡት የእድገት በሕብረት ዘማቾች መካከል ብዙዎቹ ባለጌዎች ናቸው። በሩን በርግደው እየገቡ ተራችን አልደረሰም እንዴ? እያሉ ይደነፋሉ። ውጪ ሆነውም ስሜን እየጠሩ ያፌዛሉ።*
>
> *አጥብቄ አሰብኩበት። እነዚህ ልጆች ፈጽሞ የማይገባውን ለማድረግ ልባቸውን ሰጡ። ይህንን በማድረጋቸው ራሳቸውን አቃለሉ። እኔ ግን ሳልነዋወጥ የሚገባውን በቅንነት መፈጸም አለብኝ.›› (ዕውደ ዕለት ነሐሴ 6 ቀን 1967)*
>
> *‹‹በዚህ ቀን (የአብዮት በዓል ዋዜማ) በምድራቱ ብዙ ጭፈራ፣ ብዙ ድምፅ ተሰማ። ይህም የሆነው አንዳንድ ለሥጋ የሚመቹ ነገሮች መደራጀት ስለጀመሩ ነው።. . .*

*. . .ነገር ግን ሕዝቡ በነፍስ በሽታ ታሟል። ትዕቢት፣ ዝሙት፣ ስርቆት፣ ውሸተኛነት፣ ስካር፣ መደባደብ፣ መገዳደል፣ ቅናት፣ ሀሜት፣ ቸልተኝነት፣ ጥላቻ፣ ንዴት፣ ብስጭት፣ ሚርት፣. . . ይታያል። ለመሆኑ ማን ነው ይህን ጉዳይ ጉዳዬ ብሎ የሚይዘው?! እኔ መሆን አይገባኝምን?›› (ዐውደ ዕለት ወስከረም 1 ቀን 1968)*

*‹‹በሙዚቀኛነት የሚያገለግል አንድ የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ ነበር። ሰውዬው ከሙዚቀኛነት ለመውጣት አመልክቶ የሐኪም ምስክርነት እንዲያወጣ ተነግሮት ነበር። ወደእኔም መጥቶ የሐኪም ሰርተፍኬት እንድሰጠው ጠየቀኝ። ለዚህ ሰው ምን አይነት ምስክርነት ማድረግ እንደሚገባኝ እርግጠኛ አልነበርኩም። ስለ ጉዳዩ መጸለይ ጀመርኩ። እየጸለይሁ እንዳለ ቁርጠኛ ሀሳብ በውስጤ ገባ። ይህም የሕክምና ባለሙያ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም አስተያየት መስጠት እንደማይችል ልነግረው መወሰኔ ነው።›› (ዐውደ ዕለት መስከረም 6 ቀን 1968)*

የሰርተፍኬት ነገር የዶ/ር ብርሃኑን የሙያና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በመፈታተን ከፍተኛውን ድርሻ ሳይዝ አይቀርም። ጦር ሜዳ ላለመሄድ፣ ገጠር ላለመመደብ፣ ከእድገት በህብረት ዘመቻ ለመገላገል፣ ከወንጀል ክስ ለማምለጥ ልብ ወለድ ምክንያት የሚሹ ሁሉ ሰላም እንደነሱአቸው አያጠራጥርም። ከዚያ በበለጠ ግን የባለሥልጣኖቹ ዕብሪተኛና ትዕዛዝ መሰል አቀራረብ በተደጋጋሚ የሚጋፈጡት የሙያ ሥነምግባራቸዉንና ሰብዕናቸዉን የተገዳደረ ብርቱ ፈተና ሆኖባቸዉ ነበር።





አንዱን አስደንጋጭ አጋጣሚ በወቅቱ ከእሳቸዉ ጋር ይኖሩ የነበሩት ታናሽ ወንድማቸዉ ከሌላ የዓይን ምስክር የሰሙትን እንዲህ ይተርኩታል፡-

*አንድ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ እኔም ብርሃኑም ሳሎን ቁጭ ብለን ሳለን ስልኩ ይጠራ ነበር። አንስቶ ‹አቤት ብርሃኑ ነኝ› አለ። ከወዲያኛዉ ጫፍ የሆነ ትዕዛዝ እየተላለፈለት እንደ ነበር ያስታዉቃል። በመጨረሻም፡- ‹ጊዜ ሲያገኙ ወደ ሆስፒታል ይምጡ እኔ ሰዎችን በየቤታቸው እየሄድኩ አላክምም› ብሎ ስልኩን ይዘጋና ተመልሶ ይቀመጣል። ጉዳዩን ስጠይቀው ሻለቃ አሊ ሙሳ ናቸው አለኝ። ብርሃኑ ድሆችንና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ብዙ ምስኪኖች ዝቅ ብሎ ይጎበኛል። ለትዕቢተኞች ግን የማያወላደ ተገቢ መልስ መስጠት ይችልበታል።*

***

በእንዲህ ያለ መንፈሣዊና ሥጋዊ ሰልፍ መካከል እያሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስቸኳይ ቴሌ ግራም ላከላቸው። መልእክቱ በአጭሩ የከፍተኛ ትምህርት ለመማር የሚስችላቸውን ማመልከቻ (ቅፅ) ጽፈዉ እንዲያስገቡ የሚያሳስብ ነበር። ጥሪው ባልጠበቁት ጊዜ ከመምጣቱም ሌላ በወቅቱ በቤታቸው ውስጥ የሚገለገሉትን ምዕመናን በትኖ መሄዱ ከበዳቸው። ነገር ግን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ትዕዛዝ መታዘዝ ነበረባቸው። ጉዳዩን ከወንድሞች ጋር መከሩበትና ወደ አዲስ አበባ ለመጓዝ አውቶቡስ ተሳፈሩ።

ከነፍሳቸው ጋር እየታገሉ የጀመሩት ጉዞ ኋላ ላይ የበለዓም መንገድ ሆነባቸው። የዚህንም ዝርዝር ብዕራቸው ቢነግረን ይመረጣል።

*«በመልካም ሕይወት መንገዴ ሁሉ ተወስኖልኝ ስኖር ሳለሁ ባላሰብኩት ቀን ለውጪ አገር ትምህርት ማመልከቻ እንዳስገባ ከአዲስ አበባ አስቸኳይ የቴሌ ግራም ጥሪ ደረሰኝ፡ ለጊዜው የምመልሰው መልስ አጣሁ። የደወለልኝ ሰው በነገሩ አሰቦበት ስለነበር በቀላሉ ተቃራኒ መልስ ለመስጠት አዳገተኝ።*

*የጥሪው አመጣጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንስ የሚል ጥርጥር መጣብኝ። ለማንኛውም ወደ አዲስ አበባ መሄዱ ይሻላል ብዬ ተነሳሁ። ለጊዜው መንገዴ የተሳካ መሰለ። መንፈሴን ስመረምር ግን በድን የሆነ ነገር ነበር የሚሰማኝ። ከ100 ኪ.ሜ በኋላ ፖሊሶች አዳባ የምትባል ከተማ ውስጥ አቆሙኝ። ለካንስ «ከሥራው ላይ ጠፍቶ ሄዷል» የሚል መልዕክት ደርሷቸው ወደ ጎባ እንዲመልሱኝ ትዕዛዝ ተቀብለዋል። ከተጠራሁበት ምክንያት ይልቅ አዲስ አበባ ያሉትን ወገኖቼን ለማየት ጓጉቼ ስለነበር ለጊዜው ከፋኝ።*

*በዚያች ከተማ ውዬ ለማደር ተገደድሁ። ስለ ሁኔታው ስመረምር በሰዓም ከመንገዱ እንደ ተመለሰ እንደዚሁ ጌታ እኔን ከመንገድ እንደ መለሰኝ አስተውዬ እግዚአብሔርን አመሰገንሁ። እርግጥ እንድመለስ ያደረገኝ ሰው በተንኮል አድርጓል፤ መብቴንም ያለአግባብ ተጋፍቷል። በአዕምሮ ቢሄድ መብቴን ለማስከበር እርምጃ መውሰድ ይቻለኝ ነበር፤ ነገር ግን «በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራትን እከፍላለሁ» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ከሮሜ 12 ውስጥ ታወሰኝ። በርሱ ተፅናናሁ፣ ተጠገንሁ፣ እንዲያውም ክፍሉን በቃሌ አጠናሁ።*

*እዚያ በቆየሁ ጊዜ ከፍተኛ መስተንግዶ ተደረገልኝ። በመንገዴ ከ0.50 ሳንቲም በስተቀር ምንም ገንዘብ አልከፈልኩም። ለመጣሁበት ሎንቺን እንኳን ገንዘብ እከፍላለሁ ስል ሰውዬው ከለከለኝ። ስሄድ በድን መሆን ጀምሬ ነበር፤ ስመለስ ግን*





*መንፈሴ ተፈትቶ ተመለስሁ። ለጌታ ክብር ይሁን አሜን።» (21/5/70)*

እርግጥ ነዉ ዶ/ር በዐውደ ዕለት ማስታወሻው ያልመዘገቡት አንድ ኪሣራ ነበር። ፓስተር ሰለሞን ገዛኸኝ ግን ሁሌም ያስታውሱታል፡-

> *ቤተ ክርስቲያናችን በተዘጋበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተገኙ ንብረቶች ሁሉ ተዘርፈውብን ነበር። የክርስቲያኖችም ቤት እየተፈተሸ ብዙ ንብረት ተዘርፏል።*
>
> *በአጋጣሚ እኔና አንድ ወንድም አዲስ አበባ ሄደን ለመዘምራን ቡድን የገዛናት አንድ ጊታር ተርፋ ነበር። ዶ/ር ብርሃኑ ወደ አዲስ አበባ ሲሄድ ‹እባክህ ይህችን የቀረችልንን ንብረት ቀኑ እስኪያልፍ ድረስ አዲስ አበባ ወስደህ አስቀምጥልን› ብለን ሰጠነው። ያቺን ጊታር አዳባ ላይ ሲያስሩት ወሰዷት። (ቃለ ምልልስ)*

ዶ/ር ብርሃኑ ከአዳባ እንደ ድንገት መመለሳቸው ትልቅ ማትረፊያ ሆነላቸዉ። ይህም በወቅቱ ከተዘጉት የወንጌላዉያን ቤተ ክርስቲያናት (አብዛኛዎቹ ከሙሉ ወንጌል) የተውጣጡት ሁለት መቶ ያህል የሕቡዕ አምልኮ ተሳታፊዎችን በትናንሽ ቡድኖች በእርጋታ ለማገልገል ፋታ ማግኘታቸው ነው። ሆኖም ኃባን የሚለቁበት መንገድ እንጂ ከጎባ የመልቀቃቸው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ ጉዳይ ነበር። ይህም ሁለት ወር በማይሞላ ጊዜ ከታላቅ የእግዚአብሔር ማዳን ጋር ተፈጸመ።

## *6.6. ከሕናብስት ሕፍ*

*ይህንን የእግዚአብሔር ማዳን ትረካ ከባለ ታሪኩ በላይ ማን ሊናገረው ይገባል? ‹‹እግዚአብሔር ግን እንደ ኃያልና ጨካኝ ከእኔ ጋር ነው›› ሲሉ በጽሑፍ ያስቀመጡት ማስታወሻ እነሆ!*

… ይህ ዕለት የሐዘንና የመሰበር ዕለት ነበር። ከሐምሌ 1967 ጀምሮ በመልካም የዕረፍት ኑሮ የቆየሁበትን ስፍራ ለቅቆ መውጣቱ በጣም ልብ የሚሰብር ልምምድ ነበር። በተለይም በዚያ መቆየቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ነበር ከአገሩ ክርስቲያኖች ጋር በጣም ተዋህደን ነበር። በጥልቀት የምወዳቸውና የሚወዱኝ ወገኖቼ ሲሸኙኝ አውቶብስ ተራ ድረስ ሲመጡ አካባቢው ሁሉ የልቅሶ መድረክ ሆነ። ምን እናድርግ፣ የእግዚአብሔር ሰዓት ደረሰች። ከዚያ ስፍራ መውጣቴ ግድ ስለ ሆነ ብቻ ወጣሁ።

በባሌ ያሳለፍኩት ጊዜ ለእኔ የበረከት ጊዜ ነበር፤ አብረውኝ ለነበሩትም ክርስቲያኖች እጅግ መልካም ነበር፤ ለጠላታችን ለሰይጣን ግን መራራ ጊዜ ነበር። ሐኪም ሆኜ እሠራለሁ፣ ይህ የሥራ ደረጃ በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ወደ አናቱ ገደማ ነው። ሥራዬን በንጹህ ሕሊና እከታተላለሁ፣ ከሥራዬ ውጪ ግን እግዚአብሔን አመልካለሁ። ይህ የኑር ፕሮግራም ገና ከመጀመሪያው በአካባቢዬ አንዳንድ ጥያቄ መፍጠር ጀምሯል።

ንጹሕ የሕክምና ሥራ እየሰራሁ ጥቂት እንደቆየሁ ‹‹የሕክምና ኃላፊ›› የሚባል ሹመት ተሰጥቶኝ የአስተዳደርም ሥራ መሥራት ጀመርሁ። ይህ የኃላፊነት ቦታ ከብዙ ሰዎች ጋር ያገናኘኝ ጀመር። በሥራም ሆነ ከሥራ ውጪ እኔ የማውቀው አዛላቂ መንገድ ቀጥና





የህይወት መንገድ ስለሆነች በሰፊ መንገድ ከሚሄዱት ሰዎች ጋር መጋጨት ጀመርን። በተለይም በሥልጣን መከታ ያለ አግባብ መሄድ የለመዱ በሆስፒታሉ በኩል እንደ ልብ መዝናናት ስለ ጠበበባቸው ይተክዙና ይቆጡ ጀመር። በዚህ ሁሉ ላይ በአምላኬ ባለኝ እምነት የተነሳ በሙሉ ነፃነትና ድፍረት ስለምኖር ለጠላት እንደማይነቀል እሾክ ሆንሁ።

በብዙ ሁኔታ የምጠመድበት መንገድ ይዘጋጅ ጀመር፤ በአንዳንድ ስፍራም የእኔን ይዞታ የሚያጠኑ ኮሚቴዎች ተቋቋሙ። በርካታ የሀሰት ምስክሮችም ተዘጋጁብኝ። እንዲህም በመሰለት ክስ አቀነባበሩብኝ፡-

- በሽተኞችን ማከም ትቶ መጽሐፍ ቅዱስ ነው የሚሰብከው፣
- በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ላለው የሃይማኖት እንቅስቃሴ ኃላፊ ነው፣
- በሕክምና ላይ ለሃይማኖቱ ሰዎች ያደላል፣
- ለሕክምና የሚመጡ ወታደሮችን ሞራል ይሰብራል፣
- ወደ አዲስ አበባ ተልከው የተሻለ ሕክምና ሊያገኙ የሚችሉትንና መለዮ ለባሾች እንዳይላኩ እየከለከለ አካለ ስንኩል እንዲሆኑ ያደርጋል።

ይህንና ይህን የመሳሰሉ ከእውነት የራቁ ጨርሶ ማረጋገጫ የማይገኝላቸውን ክሶች ይደረድሩ ጀመር።

ጉዳዩ በዚህ ሁኔታ እየተካሄደ ሳለ ህዳር 24 ቀን 1970 ዓም፣ በአርዕስቱ ላይ የጠቀስሁት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ሳለሁ በልቤ ውስጥ መጣ ቃሉ ልቤን እየሰነጠቀ ሲመጣ አለቅስ ነበር።

‹‹የብዙ ሰዎች ስድብ ሰምቻለሁ፤ ማስፈራሪትም ከቦኛል፤ መውደቂን የሚጠብቁ፣ የሰላሜ ሰዎች ሁሉ ምናልባት ይታለል እንደሆን፣ እናሸንፈውም እንደሆነ፣ እርሱንም እንበቀል እንደሆነ፣ ....... እኛም እንከሰዋለን ይላሉ:: እግዚአብሔር ግን እንደ ኃያልና ጨካኝ ከእኔ ጋር ነው፤ ስለዚህ አሳዳጆቼ ይሰናከላሉ አያሸንፉም::. . .›› ይህንን ቃል ስተናገረው ለሕምላኬ ነፍሴን አደራ ሰጠሁ::

ነገሩ እየበረታ ቀጠለና የካቲት 29 ቀን 1970 ዓም እመጨረሻው ነጥብ ላይ ደረሰ::

ሰሞኑን በባሌ ክፍለ ሐገር ከፍተኛ የጦር እንቅስቃሴ ሲደረግ ታቅዶ ስለነበር ሁኔታውን በቅርብ ለመከታተል አንድ የደርግ አባል የሆነ መቶ አለቃ ወርዶ ነበር:: ይህ ሰው ከሚሊሻዉ ጦር ጋር አብሮ ስለሚሠራ ቀደም ሲል የተዋወቃቸዉና ሚሊሻ ጦር ውስጥ ያገለግሉ የነበሩ መኮንኖች ስለእኔ ያላቸውን ልብወለድ አስተያየታቸውን ያቀረቡለት ይመስለኛል::
መጀመሪያ ይህ መቶ አለቃ የካቲት 28 ቀን ከሰዓት በኋላ ሆስፒታል መጥቶ በኃይለኛ ቃል ስለ አንዳንድ ቁስለኞች ሲናገረኝ ሞከረ:: ከሕመምተኞች መካከል ወደ ቢሮዬ ወሰድሁትና አነጋገርሁት:: በተለይም ዶ/ር ብርሃኑ የወታደሮችን እግር ያለ አግባብ ይቆርጣል የሚል ስሞታ ደርሶት ስለ ነበር በዚህ ነጥብ ላይ ሰፋ ባለ ጊዜ ተነጋገርን:: የቁስለኞች እግር የሚቆረጠው በሙያው በሰለጠነ ቀዶ ጠጋኝ እንጂ እኔ ያለ መሆኔን አስረዳሁ፣ እግር የሚቆረጠውም የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ እንደሆነ አስረዳሁና የተግባባን መሰሉኝ ተለያየን::





በማግስቱ የካቲት 29 ቀን (ቀኑ የበአል ቀን በመሆኑ ሆስፒታሉ እንደ ተዝረከረከ እጅ ከፍንጅ እይዘዋለሁ ብሎ አስቦ የመረጠው ይመስለኛል) የክፍለ ሐገሩን የደርግ አባል፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪዉንና የፖሊስ አዛዡን እንዲሁም የክፍለ ሀገሩን የጤና ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ይይዝና ሆስፒታሉን ይጎበኛል፤ በማለት ያስጠራኛል:: የተዘጋጀውን ድግስ አላወቅሁም!

የዋሁ ብርሃኑ ስለ ሆስፒታሉ ጥቂት መግለጫ ሰጠሁና ለማስጎብኘት ስጀምር ከሳሼ መቶ አለቃ የደርግ አባል ‹‹አንዳንድ በሽተኞችን ከማየት በስተቀር ሌላ ከሆስፒታሉ የምንፈልገው የለንም›› አለና ቀደም ብሎ ቡድኑን መምራት ጀመረ:: ከወንዶች ክፍል ሦስተኛው ስንደርስ አንድ ከወገቡ በታች በድን የሆነ ሰው ላይ እንድናተኩር የለበሰውን ገለጠ:: ሰውዬው ሰውነቱ ስለ ማይታዘዝ ቁስለት አሳይቷል:: ይህ ሰው እንደዚህ ሲቆስል የቻለው ዶ/ር ብርሃኑ ሠራተኞችን ስለ ማይቆጣጠርና ስለ ማያሠራ ነው በማለት በሰዎቹ ፊት ከሰሰኝ::፤
በዚህ ክፍል ውስጥ ቀደም ብዬ የጠቀስሁት እግሩ እንዲቆረጥ የተወሰነው ልጅ ተኝቷል:: እሱ አጠገብ ስንደረስ በትናንትናዉ ዕለት ተነጋግረን የተግባባንበትን ሁሉ በመካድ እንደ አዲስ እኔው ራሴው እግሩ እንዲቆረጥ የወሰንሁ አስመስሎ ከሰሰኝ:: በተጨማሪ የማይሸተውን ቤት ይሸታል በማለት፣ ንፅሕናው የተጠበቀውን ሕንፃ ቆሻሻ ነው በማለት እያጋነነ ክሱን ቀጠለ::

ጉብኝቱ ወደ ማብቃቱ ሲቃረብ የክፍለ ሐገሩ ቋሚ የደርግ አባል ስለ ሆስፒታሉ የፅዳት ሥራ እያያዘ ጥያቄ አቀረበልኝና ያለውን ትክክለኛ ይዞታና የሚያጋጥሙትንም ችግሮች አስረዳሁ:: ከሳሼ

አመሳሰሴን ሲታገሰው ባለመቻሉ ጣልቃ ገባና የመጨረሻውን መራራ ቃላት ተናገረብኝ::

የክሱ ውርጂብኝ ሲዠገደገድ ጌታ የመጽናናት መንፈስ በልቤ ውስጥ ሰጠኝ:: ጌታ እየሱስ በጲላጦስ ፊት በተከሰሰ ጊዜ የነበረውን ትዕግስት በመካፈል ላይ እንደነበርሁ መንፈሴ ይመሰክርልኝ ነበር::

ከከሳሺ ጋር ከመጡት መኮንኖች መካከል አንዱ ቀጠል አደረገና:- ሕክምና በመስጠት ፈንታ ወንጌልን የምሰብክ መሆኔን ተጨባጭ መረጃ ያገኝ አስመስሎ ይናገር ጀመር:: የእምነቱ ጉዳይ በመነሣቱ ደስ አለኝ፣ ምክንያቱም ይህ የተነሳብኝ ነገር ሁሉ በሥራ በኩል የተደረገ ጥፋት ሳይሆን በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ አምኜ ስለቆየሁ ጠላቴ ሰይጣን በመንገዱ እንቅፋት ለማድረግ መፍጨርጨሩ መሆኑ ይገባኛል::

ማስረጃ አለኝ ለማለት የሞከረውን መኮንን ከዚያን ቀን በፊት አይቼውም አላውቅ፣ ቡና ቤት ስለእኔ የሚያወራውን ወሬ ይዞ እንዲያው ተናገረ:: ሆስፒታሉ ሕክምና እንጂ ሃይማኖት እንደማይሰብክ አስረድቼ አንዳንድ ግለሰቦች ግን ቢመሰክሩ ይህንን አድራጎት የሚከላከል ሕግ ባለመኖሩ ሆስፒታሉን የሚያስጠይቀው ምንም ነገር እንደሌለ አስረዳሁ፤

‹ጉብኝቱ› አለቀና ወደ ሆስፒታሉ መግቢያ በር አንድ ላይ ሄድን በመጀመሪያ የክፍለ ሐገሩ የደርግ አባል ተሰናብተውኝ ወደ መኪናቸው አመሩ፤ ቀጥሎ የክፍለ ሐገሩ አስተዳደሪ ተሰናበተኝ:: ከዚህ በኋላ ከሳሺ የደርግ አባል ቀደም አለና በቁጣ ቃል ጠራኝ - አጠገቡ የነበረውን አንዱን ወታደር እንዲፈትሸኝ ትዕዛዝ ሰጠው፤. .
.





ለመፈተሽ እጁን እንዳነሳሁ የክፍለ ሐገሩ የደርግ አባል ቀረብ አለና:- ‹‹በሕግ አምላክ!›› ብሎ በመጮህ የሚወስድብኝን እርምጃ ተቃወመ:: ሊያስረኝ የተነሣው የደርግ አባል ተቆጣና ‹‹ለምን እንደዚህ ትሉኛላችሁ፣ እንደዚህ አይነቱ ወንጀለኛ ይተዋል ወይ?!›› ብሎ ጮኸ:: ‹‹በሕግ አምላክ! ትክክል አይደለህም›› ብሎ በጽናት ተናገረውና ወደ እኔ መለስ ብሎ ‹‹ዶክተር ወደ ሥራህ ሂድ›› አለኝ::

ከመካከላቸው ወጣሁና ወደ ሆስፒታሉ በረንዳ ተመለስሁ:: ሁለቱ ሰዎች ተፋጠጡ ሌሎችም አዲሱን የደርግ አባል ከበው የወሰደው እርምጃ ትክክል አመለሆኑን ገለጹ:: ሁሉም በቁጣ ተሞልተው ወደ መኪናቸው ገብተው በሩን በኃይል በመዝጋት ከግቢ ወጥተው ሄዱ::

የጤና ጥበቃው ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ በታላቅ ድንጋጤ ሁኔታውን ይከታተል ነበር:: ጉብኝቱ በዚህ ዓይነት ሲያልቅ ፊቴን ለማየት እንኳን የደፈረ አልመሰለኝም፣ ሳይገላመጥ መኪናው ውስጥ ገባና መኪናውን አስነስቶ በፍጥንት ሄደ:: ከሳሾቹ ሁሉ ግቢውን ለቅቀው ሄዱ:: እኔም ነፃ ሆኜ በእግዚአብሔር የክብር መንፈስ ተሞልቼ ብቻዬን ቀረሁ. . . ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን::

በማግሥቱ የድል ነፃነት በሕይወቴ ውስጥ እየተሰማኝ ወደ ሥራ ገባሁ:: ረፈድ ሲል ስለ እኔ ጉዳይ ከክፍለ ሐገሩ አስተዳደር ቴሌግራም ተደርጎ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሲያዛዉረኝ እንደተዘጋጀ ከጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ጋር በስልክ ሲነጋገር የሰሙ ሰዎች መጥተው ወሬውን ነገሩኝ:: እነሱ የመሰላቸውን ያድርጉ:: እኔ ግን መንገዴን ለሚጠብቀው ለአምላኬ ነፍሴን አደራ ሰጠሁ እንጂ ስለሆነብኝ ነገር ለየትኛውም ባለሥልጣን አልተናገርኩም::

ደህንን ምክንያት በማግኘቱና እኔንም ለማስተማር ባለዉ ዕቅድ የጤና·ጥበቃ ሚኒስቴር ዝውውሩን ለመፈጸም ምንም አላስቸገረውም ነበር፡፡ ለእኔ የተቀጠረልኝ የእግዚአብሔር ጊዜ አልቆ ለለ ነበር ደህ ሁሉ ነገር በአንድነት ተከናወነ፡፡ ቀና መንፈስ ያላቸው ዓለማዉያን ሰዎች ሳይቀሩ እግዚአብሔር ያደረገልኝን ሲሰሙ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡ ክርስቲያኖች ምስክርነቴን ሲሰሙ በብዙ ተፅናኑ፡፡


ጎባን ትቼ የወጣሁበት ቀን ግን የደመና ቀን ነበረች፡፡ የሲቃም ቀን ነበረች፡፡ የዋቢን ወንዝ እኩለ ቀን ላይ ተሻገርን፡፡ የአርሲና የባሌ ድምበር የሆነዉን የዋቢ ወንዝ ስሻገር አንድ የሕይወቴ ምዕራፍ ተዘግቶ ሌላው እንደ ተከፈተ ታወቀኝ፡፡ ስላደረገልኝ ነገር ሁሉ ጌታን እንዴት እንደ ማመሰግነው አላውቅም፡፡ ከጌታ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ሚቀጥለው የሕይወት ምዕራፍ እገባለሁ፡፡ አምላኬ ታማኝ ነውና በሚመጣብኝ ነገር ሁሉ አብሮኝ እንደሚሆን አምነዋለሁ፡፡ (ፀውደ ዕለት መጋቢት 15 ቀን 1970)





# 7. ከጠርዝ ወደ ጠርዝ

## *7.1. መሸጋገሪያዉ - አዲስ አበባ*




*ግላስጎ ትምህርት ላይ ሣሉ*

ከባሌ ወደ ስኮትላንደ፣ ከጎባ ወደ ግላስጎ፣ ከአንድ የሕይወት ጫፍ ወደ ሌላው የመሸጋገር ያህል ነው፡፡

ከአንድ የኢትዮጵያ ሠፈር-ታክል የገጠር ከተማ ወደ ዘመናዊቷና የታላቋ ብሪታኒያ ግዛት፡፡

ከኮሚኒስቱ የአብዮት ንዳድ - ፍጹም ካፒታሊስት ሥርዓት ወደ ሰፈነበት ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ የሕይወት ዐውድ፡፡ ‹‹አብዮት ልጆቿን ትበላለች›› በሚል ፈሊጥ ሕዝቧን በሰቀቀን ቀንበር ስር ጠምዳ ከነበረችቱ የያኔዋ ኢትዮጵያ፣ ልጆቿ ተዘልለው እንዲቀመጡ ወደ አደረገች አገር ተሻገሩ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ሐምሌ 23 ቀን 1971 ዓም ወደ ሎንደን ከዚያም



ግላስጎ ትምህርት ላይ ሣለ

ግላስን ሲበሩ ጠቅላላው ሁኔታ ከአንድ ከጠርዝ ወደ ሌላዉ ጠርዝ የመተላለፍ ያህል ሆነላቸው፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ወደ ባህር ማዶ ከመሄዳቸዉ በፊት እግዚአብሔር የመሸጋገሪያ ጊዜና ሥፍራ ሰጥቷቸዉ ነበር፡፡ ይህም ከመጋቢት 17 ቀን 1970 ዓም እስከ ሐምሌ 23 ቀን 1971 ዓ.ም አዲስ አበባ የቆዩበት ወቅት ነዉ፡፡ ይህ የአንድ ዓመት ተኩል የአዲስ አበባ ቆይታ ትላልቅ እና መሠረታዊ የሆኑ የአገልግሎትና የኑሮ ይዞታቸውን ኹነኛ አቅጣጫ እንዲያሲዙ ፋታ ሰጣቸው፡፡

በምዕራፍ ስድስት እንደ ተገለጸዉ ዶ/ር ብርሃኑ ከባሌ የወጡት ወደዉ ፈቅደዉ አልነበረም፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወደ አዲስ አበባ ያዛወራቸዉ በሕይወታቸዉ ላይ አደጋ እንዳይደርስባቸዉ በመስጋት ነበር፡፡ በእግረ መንገድም እሳቸውንና በጊዜው ትግራይ ክልል አዲግራተ ሆስፒታል ተመድበዉ የነበሩትን ደ/ር ሚልኪያስን ወደ ውጭ አገር ልኮ የማስተማር እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ነበር፡፡

ሁለቱ ጓደኞሞች ግን በታቀደዉ ጊዜ ወደ ዉጭ ለመሄድ አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም ከእነሱ በፊት የተመረቁና በሥራ ላይ የነበሩ ሐኪሞች የአንጋፋነት (Seniority) መብታችን ይከበርልን፣ በማለት ለበላይ አካል አቤቱታ በማቅረባቸዉና በጠየቁትም መሠረት ቅድሚያ ስለ ተሰጣቸዉ ነበር፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ሁኔታዉን እንደ እግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እንጂ በተራ አጋጣሚነት አላዩትም፡፡ ይልቁንም የቀሪ ዘመን አገልግሎታቸዉንና የኑሯቸዉን መደላድል የሚያጠባብቁበት





አጭር ነገር ግን ግሩም ጊዜ እንዲሆንላቸዉ ተግተዉ ሠሩበት፡፡

‹‹በቤተሰብ ሕይወት›› ትረካ ውስጥ በሰፊው እንደተብራራው ከወደፊት የትዳር ጓደኛቸው ጋር የቃል ኪዳን ቀለበት አሰሩ፡፡ ከሁሉም በላይ ለቅርብ ሰዎቻቸው ጥያቄ ሆኖ የከረመው ‹‹የቤተ ክርስቲያን አባልነት›› ጉዳይ በማያወላውል ሁኔታ ምላሽ የአገኘዉ በዚህ የመሸጋገሪያ ወቅት ነበር፤ በብርሃነ ወንጌል መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን በአባልነት ታቀፉ፡፡ ግልግል፡፡ እሳቸው በግላቸው ጥያቄ ከመሆን ተገላገሉ፤ ‹‹የእኛ ነው÷የእኛ!›› በሚልም ሽሚያ ውስጥ ተጠምደው የነበሩትም ተገላገሉ፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ የብርሃነ ወንጌልን ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን እንዴት እንደወሰኑ የተዉልን ዝርዝር ማስታወሻ የለም፡፡ ከዚያ ይልቅ አባል ከሆኑ በኋላ ስለ ተቀበሉአቸው የተከፈቱ ልቦችና ስለ ተዘረጉላቸዉ የፍቅር እጆች መመስከሩን መርጠዋል፡፡ ነገር ግን ለእሳቸው የመታሰቢያ ፕሮግራም ሥነ ሥርዓት ምክንያት በማድረግ የታተመ አንድ ጽሑፍ እንዲህ ይላል፡-

> *‹‹በሥራ ዝውውር ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ ነበር መንፈስ ቅዱስ በግልጽ ሁኔታ ወደ ብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ የመራቸው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ በመጡ ገና በሁለተኛው ሳምንት በአምልኮ ፕሮግራም መልእክት እንዲያቀርቡ ተጋብዘው ነበር፡፡›› (ገጽ4)*

ይህ ወቅት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚዘጉበትና የተዘጉበትም የስደቱ አፍላ ጊዜ ነበር፡፡ ብርሃነ ወንጌል ቤተ

ክርስቲያንም ገና አልተዘጋችም ነበር እንጂ በኮሚኒስቶች የማዋከብ ማዕበል እየተናወጠች ያለችበት ጊዜ ነበር። ከወቅቱ የጎባ ክርስቲያኖች መንፈሣዊ ይዞታ ትምህርት የቀሰሙት ዶ/ር ብርሃኑ ስደቱ ዓይኑን አፍጥጦ ሲመጣ በፅናት ለመቆም የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ከሰንበት ቀን ሰበካ በተለየ ጥልቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ያሰላስሉ ጀመር።

ይህንን በልባቸው ተሸክመው ቤተ ክርስቲያኗን እስኪላመዷት ድረስም ይመስላል ወራት ያህል በጸሎት አሳለፉ። በየመካከሉ የሚሰጣቸውን የመድረክ አገልግሎቶችን ግን በትክክል ይጠቀሙባቸው ነበር። የቀድሞዉ የጎባ ሙሉ ወንጌል አገልጋይ ፓ/ር ሰለሞን ገዛኸኝ እንዳሉት ‹‹በትልልቅ እዉነቶች የተጠቀጠቁት›› መልእክቶቻቸዉ ለብርሃነ ወንጌል ምዕመናንም መፍሰስ ጀመሩ። ከስብከቶቻቸው እኩል በጠንቃቃ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው አርአያነት የብዙዎችን አክብሮትና ፍቅር አተረፉ። ለመታሰቢያ ፕሮግራምየተዘጋጀው ጽሑፍ ይቀጥላል፡-

> *‹‹እስከሚቀጥለው ዓመት አጋማሽ ድረስ በዚህ ዓይነት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀደምት አባላትን በበለጠ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማሳተፍ ታቅደ በተጠራው ስብሰባ እንዲካፈሉ ተጋበዙ።››*

ይህ ዕለት በልባቸው ሲመላለስ የከረመዉንና ሲጸልዩበት የነበረውን ሸክም ለአገልጋዮቹ ለማካፈል በር ከፈተላቸው ዝርዝሩን ራሳቸው መዝግበውታል።

> *‹‹እስከ ሚያዚያ 14 ቀን 1971 ዓም ለአንድ ዓመት በብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ሳመልክ ቆይቻለሁ። ወደ ቤተ*





*ክርስቲያን መሄድ ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሸክም በልቤ አድሮብኝ ነበር፤ ይኸውም ለክርስቲያኖች የሚሆን ጥልቅ የትምህርት ጊዜ እንዲኖር ነበር። በነገሩ ከመጸለይ በስተቀር በተግባር አንዳች ነገር ለማድረግ ጊዜዉና ሁኔታውም አልፈቀደልኝም ነበር። ሆኖም ሸክሙ ሁልጊዜ እንደ አዲስ እየተሰማኝ እጸልይበት ነበር።*

*ጸሎቴ ፍሬ ሲያፈራ ጊዜዉ ሲቃረብ ‹ወደ ውጪ አገር ከመሄዱ በፊት የዝግጅት ጊዜ ያስፈልገዋል› ተብሎ ፈጽሞ ያላሰብኩት የእረፍት ጊዜ ተሰጠኝ።*

*በእርግጥ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ጊዜ ነበር። ዕለቱ የፋሲካ ምሽት ነው። በዕለቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች የሆንን ባለ ትዳሮችና ሠራተኞች እርስ በርሳችን ለመወያየትና የጋራ እራት ለማድረግ ተሰበሰብን። መጋቢው የስብሰባውን ምክንያት መተንተን ሲጀምር በጣም ተገረምሁ፡- መጋቢዉ ለተሰብሳቢዎች ለማቅረብ የያዘው የመነጋገሪያ ርእሶች በትክክል እኔ ስመኘዉና ስጸልይበት የነበረው ፕሮግራም ጉዳይ ነበር። በጉዳዩ ላይ ከተወያየን በኋላ ፀሎትና ዝርዝር ጥናት አድርገን ለመገናኘት ሚያዚያ 21 ቀን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።*

*የሕዝቡን ልብ እግዚአብሔር አነሳስቶት ስለ ነበር ሚያዚያ 21 ቀን የሚጠበቁት ተሰብሳቢዎች በሙሉ መጡ። በመጀመሪያ ነገሩ ያልገባቸው ሰዎች ግር እንዳይላቸዉ እውነተኛ ነገር ተብራራላቸዉና የብዙዎቹ ልብ አረፈ። ከዚያም ‹የትምህርት ፕሮግራሙ ይጀመር - አይጀመር› የሚለውን ሃሳብ በድምፅ ብልጫ እንድንወስን ሲደረግ ከተሰበሰብነው በግምት 60 — 70 ከምንሆነው መካከል ሁለት ሰዎች ብቻ ሲቀሩ ሌሎቻችን በሙሉ ልብ ለመጀመር ተስማማን።*

*ቀጥሎም ፕሮግራሞቹ እንደገና በዝርዝር እንዲጠኑ ስለ አስፈለገ ይህንን የሚያከናዉን ኮሚቴ ተመረጠ፡፡ ለኮሚቴዉ አባልነት ከተጠቆሙት ሰዎች መካከል እኔ የመጀመሪው ነበርኩ፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት መጀመሪያ ላይ (ሚያዚያ 28 ቀን) ኮሚቴዉ ተሰበሰበ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ደግሞ የኮሚቴው ሊቀ መንበር እንድሆን ተመረጥኩ ‹እንግዲህ እግዚአብሔር ያመጣውን ምን አደርጋለሁ› ብዬ ተቀበልሁ፡፡*

*ትምህርቱ በተጀመረ ጊዜ፤ አሁንም እኔ ሳላስበውና ሳልዘጋጅበት የመጀመሪያው ክፍለ ትምህርትና ርእስ ለእኔ ተሰጠ፡፡ ርእሱም ‹መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፣› የሚል ነበር፡፡ ትምህርቱን አዘጋጅቼ በብዙ በረከት በሦስት ረዣዥም ፕሮግራሞች ጌታ እንደ ሰጠኝ ጸጋ መጠን አስተላለፍሁ፡፡ ፕሮግራሞቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወደዱ ነበሩ፤ ሰዎች ሌላውን ጉዳያቸውን ወደ ጎን እያደረጉ መጥተው ለመካፈል ይተጉ ነበር፡፡*

*የመጨረሻውን መልእክት ባቀረብሁበት ሰሞን የመንገዴ ነገር እየተፋጠነ መጣ፡፡ ወደ ኋላ ተመልሼ የሆነውን ሁሉ ሳስብ እግዚአብሔርን ባረክሁ፡፡ ያ በልቤ ውስጥ የነበረው ሸክም ወደ ሥራ ስለ ተተረጎመ አሁን የለም፡፡ በፈንታው የእርካታ መንፈስ ይሰማኝ ነበር፡፡*

*መልካሙ የአምልኮና የአገልግሎት ዘመን ለጊዜው አብቅቶ ሐምሌ 22 ቀን 1971 ዓም ቤተ ክርስቲያኒቱን ተሰናበትሁ፡፡ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን - አሜን!››*

በዚህ ሁኔታ ከብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር በመንፈስ፣ በአዕምሮ፣ በስሜት በጥብቁ ተሳስረው፣ የአዘጋጁትን ትምህርት በፈጸሙ ማግሥት ወደ ስኮት ላንድ በረሩ፡፡





## *7.2. ስኮት ላንድ - ግላስኮ*

አሁን በዚያ በሶ ማበስበስ፣ ዳቦ ቆሎ መቆርጠም የለም፡፡ ‹‹ዛሬ ሊጥ በላሁ፣ ዛሬ እንጨት (ለማገዶ) አጋዝሁ፣ ውኃ ቀዳሁ. . . ወዘተ የለም፡፡ በዚያ የዘማቾች ስድብ የለም፡፡ አብዮት ከነጉዱ ከነጉዳንጉዱ የለም፡፡ ያ አስጨናቂ የባሌ ሚሊሺያ አዛዥ እና የደርግ አባሉም የሉም፡፡ የኮሚዩኒዝም ቀንበር የለም፡፡

ባይሆን የስደተኞቹ የጎባ ክርስቲያኖች ፍቅር፣ ስደት አፋፍ ላይ ያለችው የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጭንቀትና ‹‹የአልማዜ›› ነገር ከልባቸው ኀዳ ሆኖ አብሮአቸው መጓዙ አልቀረም፡፡ ይህንንም ደግሞ ሁሉን በሚችል አምላክ እጆች ውስጥ ከማስረከብ ወዲያ መድኃኒት የለውም፡፡ ሁሉን ለኤልሻዳይ አሳልፎ ሰጥቶ ማረፍ ብቻ፡፡

እያረፉ ክርስቶስን መኖር፤ ስደትና አሳዳጆች ባይኖሩም ሰይጣንና የክፋት ሠራዊት ስኮት ላንድ አገርም አሉና መንፈሣዊ ሕይወትን መጠበቅ፣ እያረፉ የኩላሊት ሕክምና ጥበብ መማር፣ ከወገኖች ጋር ሕብረት ማድረግ፣ በተከፈቱ በሮች ገብቶ ማገልገል፡፡ ይህ ነበር ጎባንና ግላስኮን የጠርዝና ጠርዝ ተፃራሪ የሕይወት መላመጃ የሚያደርጋቸው፡፡

ሁለት ሳምንት ያህል እንደ ቆዩ ይህንን አሁን የሚገኙበትን አጠቃላይ ዐውድ ሰብስበ ብለው *‹ገመገሙ›*፡፡ *መጀመሪያ* የዳሰሱት የተማሪነት ዘመናቸውን ነበር፤ ለትምህርት አይደል የሄዱትስ? ቀጥሎም የባሌ ክረምታቸውን ነበር፡፡ *‹ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፣ በኃጢያተኞችም መንገድ*

*ያልቆመ፤ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ!›* እያሉ ውሳኔ በተሞላበት ሕይወት ማዕበሉን እየተጋፉ የኖሩበትን ዘመን አስታወሱ፡፡

ሌላም በጽሞና ሲያስቡት የሚያስገርማቸዉ ግጥጥሞሽ ነበራቸዉ፤ ለእሳቸዉ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚገርም፡፡ ዶ/ር ብርሃኑንና እና ዶ/ር ሚልኪያስን ጄነራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ጎባ/ባሌ እንደገና ግላስኮ፣ ከዚያም ጥቁር አምበሳ፣ ጭራሽ አንድ የመኖሪያ ቀበሌ ... ሕይወትን እንዲጋሩ እያጣመረ የሚልካቸው ለምን እንደሆነ የሚያውቀው ላኪዉ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑና እና ዶ/ር ሚልኪያስ ግላስኮ የሕክምና ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ስፔሺያላይዜሽን ትምህርት መከታተል ከመጀመራቸው በፊት የመጀመሪያውን ‹መለኮታዊ ሌክቸር› ስኮት ላንድ ሰማይ ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠዉ ወሰዱ፡፡ *‹‹ለካንስ ከደመናት በላይ ሁልጊዜ በጋ ነው››* ተባባሉ፡፡ ትምህርቱን ያስቀሩበት ማስታወሻ የሚከተለዉ ነበር፡፡

> *በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከሰዓት በኋላ ወደ ከፍታዎች በቦይንግ ጀት አውሮፕላን መጠቅን፡፡ ከደመናዎች በላይ እየሄድን ሳለን አንድ ሃሳብ ወደ ውስጤ ገባ፡-. . .*
>
> *ከደመና በታች ጭፍግግ ያለ የአየር ጠባይ ነበር፡፡ ደመናውን መጥቀን ከፍ ከፍ ካልን በኋላ ግን ከበላያችን የሚታየን ቁልጭ - ጥርት ያለ ሰማይ ብቻ ነበር፡፡ ከበታቻችን ግን ደመናውም እንደ ባዘቶ ጥጥ ምንጣፍ መስሎ ተዘርግቶ ነበር፡፡ እኔም አሰብሁ፤ ለካስ ከደመና በላይ ለሚኖር ሰዉ ሁልጊዜ በጋ ነው! ታላቅ መንፈሣዊ ትምህርት ተማርሁበት፤*





> *ይህንንም አጠገቤ ተቀምጦ ከነበረው ከሚልኪያስ ጋር ተጨዋወትን፡፡*
>
> *ከለንደን ግላስጎ የአንድ ሰዓት ያህል በረራ ነበር፡፡ ሰዓቱ የመሸ ቢሆንም ወቅቱ በጋ ስለ ነበር ፀሐይ ገና አልጠለቀችም፡፡ እግዚአብሔርን አመሰገንሁ፡፡ እነሆ. . .እኔ እዚች ከተማ ውስጥ ለሁለት ዓመታት ልኖር መጥቻለሁ፡፡*
>
> *ቀደም ሲል ተዘጋጅቶልን ወደ ነበረው ማረፊያ ክፍል በታክሲ ሄድን፡፡ እንደ ደረስንም እንደ ገና የምስጋና ጸሎት አደረግን፡፡ ከጸሎታችንም በኋላ ቋሚ የሆነ ፕሮግራም እንድናደርግ ተወያየን!*

ሁለቱ ሐኪሞች በስኮትላንድ ባይተዋርነት አልተሰማቸውም፡፡ በተለይም ደግሞ አፍሪካውያን እንግዶች አብዝተው የሚማረሩበት የዘርና የቀለም መድሎ ሰለባ የመሆን ስሜት አልተጫጫናቸውም፡፡ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ ዶ/ር ሚልኪያስ ከዓመታት በፊት ለአቶ ወርቁ ኃይለ ማርያም መስክረውላቸው ነበር፡፡

> *‹‹ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር ነው፡፡ እንደገናም፡- በምድር ተቀመጥ ታምነህ ተሰማራ፤ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል እውነት የዕለት ሕይወታችን መመሪያ አደረግነው፡፡ ይህም ማለት የትም ብንሆን የትም አባታችን እግዚአብሔር በሠራት ምድር ላይ ነው የምንኖረው፡፡ ኢትዮጵያም ብሪታኒያም የእግዚአብሔር ናቸው ተባባልን፡፡ ብሪታኒያን እንደ አገራችን፣ ስኮትላንዳውያንን እንደ ወገኖቻችን ስለ ቆጠርን ‹ቀና ብለን› ለመመላለስ የሚያስችለንን ውስጣዊ ነፃነት ተጎናፀፍን፡፡››*

ነፃነቱ ሙሉ ነበር፤ በትምህርት ገበታ፣ ለሕክምና ሥራ በተመደቡበት ቦታ፣ ከሕመምተኞችና ከሥራ አጋሮቻቸው ጋር ሁሉ በእኩል ደረጃ ያስማማቻው ነጻነት ነበር፡፡

## 7.3. መንፈሣዊ አገልግሎት - በስኮትላንድ

ዶ/ር ብርሃኑ በአካባያቸው በሚገኙት የስኮትላንድና የእንግሊዝ ቤት ክርስቲያናትና ክርስቲኖች ጋር ሕብረት ከማድረግ አንስቶ በተለያዩ አገልግሎቶች ይሳተፉ ነበር።



በእንግሊዝ አገር የኢትዮጵያውያን ክርስቲያናዊ ሕብረት መሥራቾች መካከል ጥቂቶቹ

ከሁሉም ጎላ ብሎ የሚታየው ግን በእንግሊዝ የኢትዮጵያውን ክርስቲያናዊ ሕብረትን ምሥረታ በማፋጠንና በማጠናከር የአደረጉት አስተዋጽዖ ነው።

ለዚህም አንድ ማስረጃ የሚሆነዉ ግላስጎ ከደረሱ ሦስት ወራት በኋላ የኢትዮጵያውያን ክርስቲያናዊ ሕብረት የመጀመሪያውን ስብሰባ ከጥቅምት 30 እስከ ሕዳር 1ቀን 1972 ዓ.ም ማድረጋቸዉ ነዉ። ቦታው ፕሪስተን ሲሆን በዚህ ክርስቲያናዊ ሕብረት የተካፈሉት ኢትዮጵያውያን ብዛት ዘጠኝ ብቻ ነበር። ኢትዮጵያውያኑ ጠንካራ ሕብረት





ለመፍጠርና በተቀናጀ ፕሮግራም ለመገናኘት መሠረት የጣሉባት ይህ የፕሪስተን የአንድነት ጊዜ ነበር።

ከስድስት ወራት በኋላ ከሚያዚያ 3 እስከ 5 ቀን 1972 ዓ.ም በሞቭካምብ አደረጉ። «ጌታ በመካከላችን ስለ ነበር በኮንፈረንስ እንደሚኖረው ዓይነት በረከት በመካከላችን ፈሰሰ» ይላል ዶ/ር ብርሃኑ በወቅቱ የያዙት ማስታወሻ። ከመንፈሣዊ ጉዳዮች በአለፈ ኢትዮጵያውያኑ በኑሮአቸው በሚያጋጥሙአቸው ችግሮች ለመረዳዳት ይችሉ ዘንድ አነስተኛም ብትሆን መነሻ በጀት የአስቀመጡት በዚህ ወቅት ነበር። ሦስተኛው የኢትዮጵያውያን ክርስቲያናት ኅብረት ከነሐሴ 2 እስከ 4 ቀን 1972 ዓ.ም በሳውዝ ፓርት ተካሄደ። ቀድሞ ከተደረጉት ስብሰባዎች ሁሉ የበለጠ በረከትና መጽናናት ሆነላቸው። «መቶ በመቶ እርካታ አገኘን፣ ወደ ፊት ስለ ምናደርጋቸው ፕሮግራሞች ተወያይተን በፍቅር ተለያየን» ሲሉ ዶ/ር ብርሃኑ በዕውደ ዕለት ማስታወሻቸዉ መዘገቡ።


ከታህሳስ 24 እስከ 26 ቀን በ1973 ዓም በሳውዝፓርት የተካሄው አራተኛው የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ኅብረት ከአለፉት ሦስቱ ይልቅ ኮስተር ያለ ነበር። የሕብረቱ ተሳታፊዎች አብዛኛውን ጊዜአቸውን የአሳለፉት በእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና ጸሎት ነበር። ዶ/ር ብርሃኑ እንዲህ ያስታዉሱታል፦

> *እንደሌሎቹ ጊዜያት ሳይሆን በዚህ ፕሮግራም አብዛኛውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ነበረን፤ ተራ እየወሰድን እርስ በርሳችን እንማማር ነበር።*



በእንግሊዝ አገር የኢትዮጵያውያን ክርስቲያናዊ ሕብረት መሥራቾች መካከል ጥቂቶቹ

*ከነበረን ድንቅ ጊዜ አንድ ድንቅ ሁኔታ ተረዳሁ:: መሰብሰባችንን እግዚአብሔር የፈለገውና ያዘጋጀው ስለነበር የጌታ መገኘት በግልፅ ታወቀኝና ጌታን ባረክሁ:: እዚህ አገር በምሄድበት ቤተ ክርስቲያን ዉስጥ የዚህ ዓይነት የጌታ መገኘት ታውቆኝ አያውቅም:: የአምልኮ ጊዜያችን በጣም የጣፈጠ ነበር፤ ከቃሉም በጥልቀት ተማርን::*



ከክርስቲያናዊ ሕብረት ተሳታፊዎች መካከል ጥቂቶቹ

ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር ሚልኪያስ እንግሊዝ አገር ቆይታቸውን ሊያጠናቅቁ እነሆ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ብቻ ቀሯቸው:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ደግሞ በአብዮት እሳት መንገርገብ ከጀመሩ ሰባተኛ ዓመታቸውን ይዘዋል:: ከዘህም የተነሣ ወቅቱ በውጭ የሚገኙ ኢትተጵያውያን ወደ አገራቸው የሚመለሱበት ጊዜ ሳይሆን ሰዎች ሁሉ በባሌም ሆነ በቦሌ ለመሰደድ አጋጣሚዎችን የሚያነፈንፉበት ነበር::





አሜሪካና ሌሎች ምዕራባውያንም ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ለማስተናገድ እምብዛም የማያንገራግሩበት ወቅት እንደነበረም ይታወቃል::

እነ ዶ/ር ብርሃኑ ግን ባሌም ነበሩ:: የባሌ ሹማምንት ያን ያህል እየገፏቸው በነበሩበት ጊዜ እንኳን በባሌ የመኮብለል/የመሰደድ ስሜት ለአንድ አፍታ ሽው አላለባቸውም:: እግዚአብሔር ቸር ነውና ለስደት ሳይሆን ለትምህርት በቦሌ እንዲወጡ እድል ሰጣቸው::

በማንኛውም ቦታና ሁልጊዜም እጅግ ተፈላጊ የሆነውን ሙያ በከፍተኛ ደረጃ አጠኑ:: መሰደድ ቢሹ በርካቶች እጆቻቸውን ዘርግተው በተቀበሉአቸው ነበር፤ አላደረጉትም:: የሚጠበቅባቸውን እንቶ ፈንቶ አብዮታዊ ዐውድ እያወቁ ወደ አገራቸው ለመመለስ ተዘጋጁ::

ዶ/ር ብርሃኑ በግላስጎ ሆስፒታል የተሰጣቸውን ሥራ በሚያከናውኑበት የመጨረሻ ዕለት ሰኔ 19 ቀን 1973 ዓ.ም አምስተኛው የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ኅብረት ስብሰባ በሳውዝ ፓርት ተካሄደ:: የዕለቱ ስብሰባ አመሻሽ ላይ የሚጀምር ሆኖ እስከ ሰኔ 21 ቀን የሚቀጥል ነበር::

ዶ/ር ብርሃኑ የሆስፒታሉ ባልደረቦቻቸው በአጭር የሽኝት ሥነ ሥርዓት ከአሰናበቷቸው በኋላ ከሌሎች ወንድሞች ጋር ሆነው ወደ ሳውዝፓርት አቀኑ:: ይህኛዉ ስብሰባ በተካፋዮች ብዛት፣ በፕሮግራም ዓይነትና የይዘት ጥራት ከቀድሞ ይልቅ የተቀናበረ ነበር:: እግዚአብሔር በዚህ ኅብረት በሕይወታቸው



ከክርስቲያናዊ ሕብረት ተሳታፊዎች መካከል ጥቂቶቹ

/ር ብርሃኑና ዶ/ር ማለኪ ደስ እንግሊዝ አገር ቆይታቸው

የአደረገላቸውን ለመመስከር ብዙዎች ይሽቀዳደሙ ነበር። ዶ/ር ብርሃኑም በማስታወሻቸው ይህን አሰፈሩ፡-

*‹‹በጣም ልብ የሚነካ ስብሰባ ነበር፤ . . .አንዲት እህት ስትመሰክር እንዲህ አለች፤ ‹ከዚህ በፊት የተለያዩ ስብሰባዎች ተካፍያለሁ፤ እንደ እዚህ ስበሰባ ግን የእግዚአብሔርን መገኘት የተለማመድሁበት ስብሰባ አልገጠመኝም።›. . .*

*ለሚልኪያስ፣ ለተናኜ ለማና (በተመሳሳይ ጊዜ ለከፍተኛ ትምህርት እንግሊዝ አገር የነበሩ) ለእኔ የዚህን ዓይነት ስብሰባ ለመካፈል የመጨረሻችን ስለሆነና ወደ ውድ አገራችን ልንመለስ ስለሆነ ወደ ጉባዔው ፊት ወጥተን እጅ በመጫን ጸሎት ተደረገልን። ጊዜው ብዙ ስለ ቲራመደ·በበረከትም ስለ ተጥለቀለቅን በጊዜ መጥበብ ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የምስክርነት ፕሮግራም ሊቀጥል አልቻለም።*

*. . .ታማኙ አምላክ የተባረከ ይሁን። በዚህ አገር ለሚቀሩትም፣ ወደ አገራችን የምንመለሰውም፣ ጌታ በምን ዓይነት መንገድ እንደ መራንና በምን ዓይነት ፍቅር እንደ ተንከባከበን በፅዮን ስንገናኝ እናወራዋለን።››  (ዐውደ ዕለት ሰኔ 2 ቀን 1973)*

ከሃያ ስምንት ዓመት በፊት ያንን የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ኅብረት ከተካፈሉት መካከል ስንቶቹ ወደ ዘለዓለማዊ ቤታቸው (ፅዮን) እንደ ተሰበሰቡ ይህ ጸሐፊ መረጃ የለውም። አዲስ አበባ፣ ባሌ፣ ግላስጎ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ ሳይለያዩ የኖሩት ሁለቱ ሐኪሞች ግን አሁን ያሉት እዚያ ነዉ። የእነሱ ነፍስ ስንቱን ትዝታ እያነሳች ስንት ጊዜ ሐሴት አድርጋ ይሆን?!





## 7.4. ወደ አገር ቤት

**የምድርና መሳዋ ፈጣሪ - ከዓለማት መሐል ለይቶ፣**
**እኔን ከአፈርሽ ቀምሞ - ኑሮዬን ለኑሮሽ ሰጥቶ፣**
**በእናትና ልጅ ምሣሌ - እንደ'ዚህ ካስተሳሰረኝ፣**
**ገበናሽን እየሸፋፈንኩ፣**
**ትቢያሽን በእንባዬ እያበስኩ፤**
**ወድጄሽ ከመኖር በቀር**
**ከቶስ ምንድን ምርጫ አለኝ?**
**አንቺማ ባለ መብት ነሽ**
**እኔም ሌላ አገር የለኝ!!**

*(ያልታተመ ጥራዝ)*

ዶ/ር ብርሃኑ ግላስጎ በገቡበት ልክ በሁለተኛው ዓመት ሐምሌ 23 ቀን 1973 ዓ.ም በጣሊያን በኩል አድርገዉ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞ ጀመሩ። ሐምሌ 24 ቀንን ሮም ከተማ አሳለፉ። አጋጣሚዉን በመጠቀም የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ለአናብስት እየተወረወሩ የሞቱበትን ‹‹ኮሎሲየም› የሚባለውን ታሪካዊ ሥፍራ ጎበኙ። ሰማዕታቱ ስለ እምነታቸዉ የከፈሉትን መስዋዕትነትና የተፈጸመባቸዉን ግፍ በልቡናቸዉ ሁለት ሺህ ያህል ዓመታት ወደ ኋላ ተጉዘዉ አሰቡት፤ እንደ ትኩስ መርዶ በእንባ ዘከሩአቸዉ።

*‹‹የማልረሳው የሕይወት ልምምድ ነው። ሮሜ አስገራሚ ከተማ ናት፤ ቅዠት እንጂ እውነት አትመስልም። ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በፊት የተሠሩ ሕንፃዎች በከተማው መካከል ይታያሉ። በመንገዱ አንዱ ወገን የጥንቱ ከተማ ሲታይ፣ መንገዱን ተሻግሮ ደግሞ አዲሱ ከተማ ይታያል። ሮሜን የሚጎበኝ ሁሉ በከተማዋ ልብ ውስጥ በሚገኘዉ በጥንቱ ሥልጣኔ ይከበብና ወዲያዉ በራሱ ተመስጦ ውስጥ መግባት ይቻለዋል። ካየሁት ሁሉ ግን ኮሎሲየም (Colosseum) የሚባለዉ ቦታ ነበር ልቤን በጣም የነካው።*

ኮሎሲየም በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተሠራ አሁንም ሮም ከተማ ውስጥ ግዙፍ ሆኖ ቆሞ የሚታይ ትልቅ ስታዲዮም የሚመስል ሕንፃ ነው፡፡ የተለመደው ኳስ ጨዋታ የሚታይበት ስታዲዮም ሳይሆን ሰዎች ከተራቡ አውሬዎች ጋር የሚዋደቁበትና የብዙዎቹ ደም የፈሰሰበት ቦታ ነበር፡፡

በተጨማሪም ሲፈልጉ በውኃ ሞልተውት የመርከብ ላይ ጦርነት ትርዒት ያሳዩበት እንደ ነበረም ይነገራል፡፡ ብዙ ጊዜ ለቱሪስቶች የማይነገር ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ገንኖ የሚጠቀስ ሌላም ታሪክ አለ፡፡ ያም የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ክርስቲያን በመሆናቸዉ ብቻ ለተራቡ አውሬዎች የሚጣሉት በዚህ ቦታ የመሆኑ ታሪካዊ እዉነት ነው፡፡

በኮሎሲየሙ ውስጥ ገና እንደ ገባሁ የጥንቱ የወገኖቼ ስቃይ ወረረኝ፤ በሃሳቤ ሁለት ሺ ዓመታት ወደ ኋላ ተመለስሁ፤

‹‹ምንኛ በአሰቃቂ ጭንቀት ዉስጥ አልፈዉ ይሆን? የአውሬ ጥርስ በጭካኔ ሰውነታቸውን ሲቦጫጭቀዉ እንዴት ተሰምቷቸው ይሆን? . . . ያው ማዶ ላይ ቀዳዳ ይታየኛል፡፡ አንበሳው የሚለቀቅበት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ... ወንድሜ ክርስቲያኑ ደግሞ ተወርውሮ የሚመጣበትን አውሬ ቆሞ የሚጋፈጠዉ በዚያኛዉ በኩል ሆኖ ነዉ፤ . . .›› እያልሁ ተመስጦ ውስጥ ገብቼ አለቅስሁ፡፡ እንደዚህ እያለቀስሁ የራሴንም ልብ እየመረመርሁ፣ በሀገሬም ስላለው ስደት እያሰብሁ ኮሎሲየሙን ዞርኩ፡፡

ጳውሎም በእየሩሳሌም ተይዞ በተደበደበ ጊዜ ጌታ በሁለተኛ ቀን ምሽት አጠገቡ ቆሞ ‹‹ጳውሎስ ሆይ፣ በእየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ›› ያለው በዚሁ ሕንፃ እንደሆነም አስታወስኩ፡፡





ይህ መልእክት በሕይወቴ ዘልቆ ስለ ገባ፤ ለጌታ አገልግሎት መስዋዕት ከመሆን ይልቅ ሌላ የመኖር አላማ ሊኖረን እንደማይገባ ተረዳሁ፡፡ ጌታ ፅናቱን ይስጠኝ አሜን!››

በከፍተኛ ትምህርት ሳቢያ ለሚገኝ ሹመትና ጥቅማ ጥቅም ሳይሆን ራሳቸዉን ለመስዋዕትነት አዘጋጅተዉ ሐምሌ 25 ቀን አዲስ አበባ ገቡ፡፡ የአረፉት በእምነት መንትያዬ ከሚሏቸው አቶ ሚናስ ብሩክ ቤት ነበር፡፡ ከሥልጡኑ ዓለም ኑሮ በተቃራኒ የሰፈነውን ውጣ ውረድ የሞላበትን የሀበሻ ሕይወት በተላቀቁት በ733ኛ ቀን ተመለሱበት፡፡ ከሀበሻው ሕይወትም የሀበሻን ዶክተር (የኩላሊት ስፔሺያሊስትና ሌክቸረር) ኑሮ ለመኖር አልመረጡም፡፡ ይልቁንም ራሳቸውን ወደ ተራው ኢትዮጵያዊ የሕይወት ቁመና (አቋም) ዝቅ አርገዉ ከረከሙት፡፡ እስቲ የራሳቸው ብዕር ይንገረን፡፡

ለጊዜው ያለሁበት ሁኔታ ወደ ውጭ ከመሄዴ በፊት ከነበረዉ ምንም አልተለወጠም፤ ነገር ግን የእኔ ሕይወት ከአካባቢዬ ጋር እንዲስማማ ሆኖ ተለወጠ፡፡

ሻንጣዎቹን አልጋ ስር አስገባሁ፤ የማያስፈልጉትንና ያረጁትን መጽሐፎች ገለል አድርጌ ለጊዜዉ የምጠቀምባቸውን መጻሕፍት መደርደሪያ ላይ ደረደርኩ፡፡

ቢንቢን በፍሊት መዋጋት ጀመርኩ፣ አካላቴን ለመታጠብ ደግሞ በብረት ምጣድ ላይ ተቀምጬ ተወጣሁት፡፡ (የውዴ አልማዝ ስጦታ የሆነችዉ በርጩማ ዋናዋ መሣሪያዬ ነች) ደጋግሜ በዚህ አይነት ስታጠብ ዘዴዉን አቀላጠፍሁት! በቤት ኪራይ በኩል ምንም ነገር ፈቀቅ አላለም፡፡ ስልኩም አይቻልም ተባለ፤ ‹‹ጌታ ባሳካው ጊዜ ይሆናል›› ብዬ ተውኩት፡፡ ተሽከርካሪም ለማግኘት ሞከርሁ፤ መንገዱ ሁሉ ዝግ ሆኖ አገኘሁትና ተውኩት፡፡

*ይህ ሁሉ በር ተዘግቶ ግን እኔ በግሩም መጽናናት ውስጥ ቀጠልሁ። ጌታ ይባረክ!›› (ዐውደ ዕለት ሐምሌ 28 ቀን 1973 ዓ.ም)*

ከግል ሕይወታቸው መጨናነቅ ይልቅ የከበዳቸው የክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነበር። የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ተዘግታ ነበር የጠበቀቻቸው። የተበተነውን ምዕመን ለማስተባበርና በየሠፈሩ በተቋቋሙት የቤት ውስጥ ሕብረቶች ለማያያዝ መሪ አገልጋዮች ሌት ተቀን የሚዋትቱበት ወቅት ነበር።

አርፎ በከረመው ጉልበታቸው እኒህን አገልጋዮች ማገዝና ማጽናናት የመጀመሪያው መንፈሣዊ አገልግሎታቸው ነበር። በመካከልም በታላቅ ስደት ላይ የነበሩትን የባሌ ወገኖቻቸው ያሉበትን ሁናቴ ሄዶ ለማየት ወደ አዳባና ጎባ ተጓዙ። በአጋጠማቸው ነገርም ፈጽሞ ተፅናኑ።

*‹‹ከዚህ ክፍለ ሀገር በወጣሁ በሦስት ዓመት ተኩል ተመለስኩ። ጌታንም ባረክሁ። በሰልፍ ተነስተውብኝ የነበሩት ሁሉ አሁን ወዴት ይሆኑ? እኔ ግን ሁሉ ተሟልቶልኝ፣ ምንም ሣልፈራ ተመለስኩ።. . .*

*. . .ሁኔታዎች ምቹ በማይሆኑበት ጊዜ እንኳን የጌታ ሥራ ፈጽሞ እንደ ማይታገድ አስተዋልሁ። አገልጋዮች ርቀው በተሰደዱበት ይህ ወቅት ‹እዚህ ግቡ› የማይባሉ የነበሩት ክርስቲያኖች እሳት ለብሰው ለማገልገል ተነስተዋል። . . ምቹ የመሰብሰቢያ ቤታቸዉ ሲዘጋባቸዉ፣ ሌላው ያልተጠበቀው በር ተከፍቶላቸው አየሁ። የማይረታ መንገድ ላይ ነን። ግዳጅ ላይ ያሉ ወገኖቻችንም አየሁ። ልቤ ተነካ! ጌታ ይጠብቃቸሁ።›› (ዐውደ ዕለት ነሐሴ 23 ቀን 1973 ዓም)*





# 8. ፍቅርና ትዳር

## *8.1. እህልና - ውኃ አገጣጣሚ*

እንደገና ወደ ባሌ መመለሳችን ነው። ወደዚያም የሚያሸጋግረን የኢንጂኔር ደሜ ‹የእህልና - ውኃ አገጣጣሚነት› ትረካና ምስክርነት ነው። እንዲህ ይላሉ፡-

እኔና ብርሃኑ የምንተዋወቀው ሁለታችንም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሳለን ነው። የአዋሬና የበቅሎ ቤት ጸሎት ቤቶችን አጣምሮ በሚመራዉ የሽማግሌዎች ኮሚቴ ዉስጥ ሚናስ ብሩክንና ሌሎች ጓደኞቻችን ጨምሮ ሁለታችንም እንሳተፍ ነበር። አብረን እናገለግል ነበር ልበል እንጂ መችም በአዕምሮ ፍጥነት፣ በጭምትነት፣ በሕይወትና በአገልግሎት መሰጠት ሁልጊዜም እሱ ፊተኛችን ነበር ለማለት እችላለሁ፤ ይህን ለማለት የደፈርኩት አብረን ማገልገላችን ልብ ለልብ ለመግባባትና የበለጠ እንዳውቀዉ ዕድል ስለ ሰጠኝ ነዉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ፋኩሊቲ የቅድመ ሙያ ትምህርታችንን ስንጨርስ እኔ ወደ ኢንጂነሪንግ እሱ ጥቁር አምበሳ ሆስፒታል ወደ ሚገኘዉ የሕክምና ፈኩሊቲ ገባን። ግንኙነታችን ግን ቀጠለ። ለጥቂት ጊዜ የተለያየነው በረብሻ ምክንያት ዩኒቨርሲቲው በተዘጋበት 1965 ዓ.ም ለአንድ ዓመት በመምህርነት ተቀጥሬ አዳባ (ባሌ) በሄድኩበት ወቅት ነበር። አዳባ በቀየሁባት አንድ ዓመት ጊዜ ብዙ ወዳጆችን አፈራሁ። አንዷ እና በልዩ ትኩረት ስከታተላት የነበረችዉ ተማሪዬ አልማዝ ታረቀኝ ነበረች።

ለአልማዝ ልዩ ትኩረት እንዳደርግ የጋበዘኝ ደብተሮቿን ስማረም በወስድኩበት አጋጣሚ ሳታስበው ሊሆኝ ይችላል ደኽተሯ ጠርዝ ላይ

የምትጽፋቸው ቃላትና ሐረጎችን ደጋግሜ በማንበቤ ነበር፡፡ እዉቃም ሆነ ሳታውቅ የጻፈቻቸዉ ቃላትና ሐረጎች ሃሳቦቹ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነበር፡፡ እኔም ይህችን ወጣት እግዚአብሔር ልቧን ለወንጌል ቃል እያዘጋጀ መሆኑን በመረዳት እጸልይላት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከወቅቱ ሁኔታ የተነሳ የሚገባኝን ያህል ሳልቀርባት ዓመቱ ሲጠናቀቅ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ በ1966 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ቀጠልሁ፡፡

ወቅቱ የተማሪዎች ንቅናቄ ተፋፍሞ አብዮት የሚባለውም ነገር የፈነዳበት ጊዜ ነበር፡፡ በ1967 ዓም የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የስራ ዘመቻም ታወጀ፡፡ እኔም ግዳጄን ለመወጣት እንደገና ወደ ባሌ ተመለስኩ፡፡ የሕክምና ፋኩልቲ ተማሪዎች የሚማሩት በጥቁር አምበሳ ግቢ መሆኑ ጠቅሚቸው ነው መሰለኝ እንደ ሌሎች ፋኩልቲዎች የመዘጋትና የመከፈት ሰበባዎች አልነበሩም፡፡ ስለሆነም ብርሃኑና ሚልኪያስ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት እንደ እኔ ዓመታት ሳያባክኑ ነበር፡፡ ሁለቱ ሐኪሞች እንደተመረቁ ባሌ ጎባ ሆስፒታል ተመድበው መጡ፡፡ የትምህርት ቤትና የጸሎት ቤት ግንኙነታችን ባሌ ላይ ቀጠለ፡፡ እኔም በአገኘሁት አጋጣሚዎች ሁሉ እየሄድኩ እገበኛቸው ነበር፡፡

በ1968 ዓም መጀመሪያ ላይ ጎባ ከተማ ስዘዋወር ሦስት እህትማማቾች የሚከራይ ቤት ፍለጋ ሲንከራተቱ ተገጣጠምን፡፡ አንዷ ያቺ ከዕድሜዋ በላይ እርጋታ የሚታይባት ተማሪዬ አልማዝ ነበረች፡፡ አልማዝ ከአዳባ ወደ ጎባ የመጣችዉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመከታተል ነበር፡፡

‹‹አባትሽ የሰሩት ቤት እያለ?›› አልኳት፡፡
‹‹አባታችንማ ከቤት አባረረን፣ ልጆቼ አይደላችሁም! አለን››





‹‹ለምን አባረራችሁ!?››
‹‹ታሪኩ ረዥም ነው፤ በእርጋታ ብንነግርህ ይሻላል›› አሉኝና ነገሩን ከመሠረቱ አጫወቱኝ፡፡

***

**ከዚያስ?**

አቶ ታረቀኝ ወልደየስ በአዳባና በጎባ አካባቢ በብዙ ምክንያቶች የታወቁ ሰው ናቸው፡፡ ባለ ብዙ ከብቶች፣ ባለ ብዙ መሬት፣ ባለ ብዙ የከተማ ቦታና ቤቶች ባለቤት መሆናቸዉ በአካባቢው የሐብት ደረጃ ‹ባለጠጋ› ያሰኛቸዋል፡፡ በዚያ ላይ የታወቁም ጠበቃ ናቸው፡፡ አብዮት ሲመጣ መሬታቸውንና ቤታቸውን ወረሰባቸው፡፡ የጥብቅና ሙያቸዉን ግን አልተነጠቀባቸውም ነበር፡፡ እስከ 83 ዓመት ዕድሜያቸው ድረስ ፍርድ ቤት ጠፍተዉ አያዉቁም፡፡ በዚያዉ ልክ ጥብቅና የቆሙላቸውን ሰዎች ሁሉ ወዳጅ አድርጎ የማስቀረት ከፍተኛ ችሎታ እንደ ነበራቸዉ ይነገርላቸዋል፡፡

በ1967 ዓም የእኒህን አዛውንት ዝና የሚነካ ነገር ቤታቸው ውስጥ ተፈጠረ፡፡ ሦስቱም ሴት ልጆቻቸው በወቅቱ አነጋገር ‹‹ጠረ ማርያም›› የመሆናቸዉ ነገር ተሰማ፡፡ *(ጠረ ማርያም)* የሚለዉ ቃል የወንጌል አማኞችን አንገት ለማስደፋት ተቃዋሚዎች የሚጠቀሙበት አገላለፅ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ እናም በወቅቱ ከተነሳዉ ስደት ጋር ተደማምሮ ጉዳዩ የአዳባ ከተማ ኗሪዎች የመቦዘኛ ወሬ ማሟሻ ሆነ፡፡

አዛዉንቱ አቶ ታረቀኝ ከባድ የእርምት ርምጃ ወሰዱ፡፡ ሦስቱንም ልጃገረዶች በመጫኛ አሥረው በአኮርባጅ ገረፉ፡፡

‹‹ግርፋቱ ሞትን የሚያስመኝ ቅጣት›› ነበር ይላሉ ወ/ሮ አልማዝ አባታቸዉ ያደረሱባቸዉን ድርጊት ሲያስታውሱ፡፡

ይህም አልበቃቸው፤ ‹‹ትምህርት ለሴት ልጅ ከዚህ በላይ አያስፈልግም፤ ለባል መዳር አለባቸው›› ሲሉ ወሰኑባቸዉ፡፡ ስለሆነም ሦስቱም ልጃገረዶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው አዳባ ቤት ዉስጥ እንዲውሉ ፈረዱባቸው፡፡ ጎባ ወደ ሚባል ከተማ ድርሽ እንዳይሉም አደረጉ፡፡

ልጃገረዶቹ አባታቸዉ በወሰዱት እርምጃ ተከፉ፡፡ ከአሉበት ጭንቀት ለመገላገል ሲሉ ሥራ አፈላልጎ ለመቀጠር ሲያደቡ ሰንብተዉ አመቺ በመሰላቸዉ ቀን ወደ ጎባ ከተማ ሄዱ፣ ኮበለሉ ማለትም ይቻላል፡፡ እንደ አሰቡት ባይሆንም ቀናቸዉ፡፡ ሦስቱም በመሠረተ ትምህርት (የድጎማ አስተማሪ ይባል ነበር) መምህርነት በወር አሥር ብር ተቀጠሩ፡፡ እየተራቡም ቢሆን እግዚአብሔርን ለማምለክ ጨክነዉ ነበርና ይህንን ደመወዝ በወሩ መጨረሻ ላይ ለማግኘት ተስፋ አድርገው ቤት ለመከራየት ሲንከራተቱ ነበር ከቀድሞ መምህራቸው አቶ ደሜ ጋር ድንገት የተገናኙት፡፡

‹‹አንተስ ለምን መጣህ ጋሽ ደሜ?››
*‹‹ጓደኞቼን ለመጎብኘት፡፡››*
‹‹እነ ማን የሚባሉ?››
*‹‹ዶ/ር ብርሃኑ እና ዶ/ር ሚልኪያስ ይባላሉ፤ ሁለቱም ክርስቲያኖች ናቸዉ፡፡››*
‹‹የእነሱንማ መምጣት ሰምተናል፡፡››





*‹‹እንዲህማ ከሆነ ለጊዜው ቤት ፍለጋውን አቋርጡና ጓደኞቼ ከሥራ በሚወጡበት ሰዓት እነሱ ቤት እንገናኝ፡፡ እንደ ሚያከራዩ አላውቅም እንጂ የሚኖሩበት ግቢ በርካታ ትርፍ ክፍሎች አሉት፡፡››*

በዚህ ተግባብተው ተለያዩና አሥራ አንድ ሰዓት ከአለፈ በኋላ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ቤት ተገናኙ፡፡

ወቅቱ በጎባ ክርስቲያኖች ላይ ከባድ የስደት ደመና ያንዣበበት ጊዜ ነበር፡፡ የአንድ ታዋቂ የአገር ሽማግሌ ልጆች የሆኑትን ሦስት ልጃገረዶች ማስጠለል የባሰ ነገር ይቀሰቀሳል የሚል ስጋት ወገኖችን ማሳሰቡ አልቀረም፡፡ በሌላ በኩል ከጎባ ክርስቲያኖች መካከል እንደ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ምቹ፣ ሰፊና በርካታ ትርፍ ክፍሎች ያላቸው ወገኖችም አልነበሩም፡፡ ለማንኛውም በአቶ ደሜ መካከለኛነት ጉዳዩን ከወገኖች ጋር ከመከሩበት በኋላ ሦስቱም ልጃገረዶች በእነ ዶ/ር ብርሃኑ ሰርቪስ ቤቶች እንዲጠለሉ ተደረገ፡፡ በጋራም ቤተሰባዊ ሕይወት መምራት ቀጠሉ፡፡

በክርስቲያናዊ ሕይወት ብስለት፣ በትምህርት ደረጃ፣ በማሕበራዊ ኑሮና በሰብዓዊ ግንኙነት እንዲሁም በአመለካከት በሚራራቁት ሰዎች የተፈጠረው ‹‹ቤተሰባዊ ግንኙነት›› አልጋ በአልጋ አልነበረም፡፡ ከሰፊና ‹‹ፊዉዳላዊ›› ዓይነት የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ ተወልደው የአደጉት ልጃገረዶች ከእርሳስና ብዕር ደብተርና ወረቀት በስተቀር ‹‹አለቀብኝ፣ ይገዛልኝ›› ብለው አያውቁም፡፡ አልባሳትና መዋቢያ የመሳሰሉትንም ቢሆን ወላጆቻቸው አስበውና ፈቅደው ያሟሉላቸዋል እንጂ

እነሱ አይጠይቁም፣ ሲደረግላቸው ማየት ብቻ። ከዚያም አባትን እጅ ነስቶ ማመስገን።

እነዚህኞቹ ‹‹ዶክተሮች›› ሙሆናቸዉ ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወታቸዉ ጥንቁቅና ትጉህ፣ በገዛ ጥረታቸው ራሳቸውን ለዚህ ቁም ነገር ያበቁ ወጣቶች ናቸው። በወቅቱ የደመወዝ እርከን ቢመዘን ምናልባት ጎባ ላይ ከፍተኛዉን የወር ገቢ ከሚያስገቡት መካከል የሚመበደቡም ናቸዉ።

ይሁን እንጂ ‹‹ሙክቱን ከጉረኖ፣ ሰንጋው ከበረት፣ እህሉን ከጎተራ፣ ቅቤውን ከጓዳ፣ እሸቱን ከማሣ›› ከሚል የአኗኗር ዘይቤ ጋር አይተዋወቁም። ከተሜዎች ናቸዋ! ስለሆነም አስቤዛም ሆነ ሌላዉን ወጪ እስኪጠየቁ ይጠብቃሉ። በሌላ በኩል በደም ባይገናኙም ቤታቸው ያስጠለሏቸው ሴቶች በክርስቶስ እህቶቻቸው እንደ መሆናቸዉ እህቶቻቸው በትምህርታቸው እንዲበረቱ፣ በክርስትና ሕይወታቸው እንዲተጉና ፍፁም ሥነ ምግባር ተላብሰዉ እንዲመላለሱ ይመኙ - ይጠብቁባቸዉም ነበር። ስለዚህም ሳያውቁትም ቢሆን በእህቶቻቸው ላይ ከበድ ያለ ምናልባትም ያልለመዱት ዓይነት የሕይወት ሥነ ሥርዓትና የአኗኗር መርሆ/ዘይቤ የጣሉባቸው ይመስላል። ይህን አገላለፅ የሚያመላክተንን ሁለት የዶ/ር ብርሃኑን ማስታወሻዎች እንጥቀስ፦

> *በዚች ቀን (10/4/68) ለእህቶቼ ፌዝ የማይገባ ነገር እንደ ሆነ አሳሰባቸው ዘንድ ጌታ ጸጋዉን ሰጠኝ። . . . እንግዲህ በቀጥታ የሰዎችን ስሜት ‹ደስ የማያሰኝ› መልእክት በማሕበር ሳይሆን በግል ስናገር ይህ የመጀመሪያ ቀኔ ሊሆን ነውና ጌታዬን በጣም አመሰግናለሁ። አስቀድሞ በግል ሲሆን ሰዎችን ከማጽናናት በስተቀር የግሣጼ ቃል ስለ ማልናገር*





> *‹ራሴን የማከብር ሀሰተኛ አገልጋይ ነበርሁኝን?› ብዬ አሰብኩ። እግዚአብሔር በጣም ዝቅ ዝቅ ያደርገኝም ዘንድ ጸለይኩና የተሰማኝን ተናገርኩ።*
>
> *ይኼዉ ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ በእራት ጊዜያችን ላይ የፌዝ ጨዋታ አልነበረም። (ዐዉደ ዕለት ታህሣስ 10 ቀን 1968)*
>
> *በዚች (15/4/68) ቀን አብረውን ለሚኖሩት እህቶች ስለ ትምህርት ያላቸው ሃሳብ ላላ ያለ ስለሆነ በማስተዋል እንዲራመዱ እንድመክራቸው እግዚአብሔር አዘዘኝ።*

ሁኔታዎች ሳይለወጡ አራት ያህል ወራት አለፉ፤ ነገር ግን እህቶችም ሆነ ወንድሞች የሚመኙትንና የጠበቁትን ሰላምና ደስታ አላገኙም። በዶ/ር ብርሃኑ አነሳሽነት አንድ ሁለት ጊዜ እንደ ገና ተሰብስበው ተወያዩ፤ ተወቃቀሱም።

> *አብረውን የሚኖሩ እህቶች በአንዳንድ ነገር ቅሬታ እንዳላቸው በግልጽ ይነበባል። በዚህ ምሽት የጸሎቱን ፕሮግራም እመራለሁ ብዬ መናገር ልጀምር ስል ጨርሶ አልተቻለኝም። በመካከላችን ትልቅ ገደል እንዳለ መንፈስ ያስረዳኝ ነበር። ጸሎቱን ለመጀመር መታገሌን ትቼ እህቶችን ቅሬታ እንዳላቸው እንዲናገሩ ጠየቅኋቸዉ።*
>
> *ብዙ ካቅማሙ‹ በኋላ አንዲቱ፦ ቅሬታ እንዳላቸው ለመናገር ጀመረችና ዝርዝሩን ግን መናገር እንደማትፈቅድ አስታወቀች። በዚህ ጊዜ በማቴዎስ 5:23-24 እና በማቴዎስ 18:15-17 ያለው የጌታ ቃል ትዝ አለኝና አነበብኩላቸው። ለዚህም የጌታ ቃል የነበራቸው አመላለስ መልካም አልነበረም። ሆኖም በመጨረሻ ሊናገሩ ሲጀመሩ ነገሮችን የሚመለከቱበት መንገድ እንደ ሥጋዊ ሰው ዓይን እንደ ነበረ አስተዋልን። ይህም በጣም አሳዘነን። (ለምሳሌ) በቀላሉ የማያምኑበትንና የማያደርጉትን ነገር እሺ ይላሉ። ነገር ግን የተነገራቸውን*

*ቃል ዓላማ አይረዱትም፣ ወደ ሥጋዊ ሐሳብም ይተረጉሙብን ነበር።*

*ብዙ የሚያስቸግራቸው እና የሚጎድላቸው ነገር እያለ ስለ ማይተማመኑብን አይነግሩንም ነበር። ከኛ ይልቅ የሥጋ ዘመዶቻቸው ይሻሏቸው ኖሯል!!*

*... ውይይታችን 5 ሰዓት ያህል ፈጀ። በመጨረሻም ሁላችንም ከመቀመጫችን ተነስተን ጸለይን።... እንባዬም ያለ ችግር ይወርድ ነበር። በጸሎት መልክ የምናገረውና በውስጤ ያልፍ የነበረው ቃል ኃይለኛ የደኅንነት ወንጌል ቃል እንደ ነበር ትዝ ይለኛል።*

*ከዚች ቀን በኋላ እህቶች የሚቸግራቸውን ሁሉ እንደሚጠይቁን ቃል ገቡልን። አሁን መልካም መሠረት ተጥሏል...። (ዐዉደ ዕለት ሚያዚያ 21 ቀን 1968)*

አዎ! መሠረቱ ተጥሎ ነበር፤ እያንዳንዳቸዉ ግን እንዴት መገንባት እንደ ሚገባቸዉ ያወቁበት አይመስልም።

ጊዜዉን ደግሞ ያስታውሷል፦ አብዮታዊ አጉራ-ዘለልነት (አናርኪዝም) የነገሠበት ወቅት ነበር፤ የዉክቢያና የስደት ጊዜ ነበር። በቀላሉ ዓይን ለሚገቡትና ኮሚዩኒዝምን ገሸሽ አርገዉ ለሚኖሩ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ዓይነት ባለሙያዎች እረፍት የሚነሣ ወቅት ነዉ። በዚህ ላይ የቤት ዉስጥ ችግር ሲደመርበት የሁለቱን ወንድሞች ትእግሥት ቢፈታተን አያስደንቅም። በዚያዉ ሰሞን (ሐምሌ 30 ቀን 1968 ዓ.ም) ዶ/ር ብርሃኑ እንዲህ ብለዉ ነበር፦

*በዚህ ሰሞን ከበድ ያለ የትግል ቀናት አሣለፍኩ። በቤት ዉስጥ እህቶች ብዙ የግድ የለሽነት ተግባር ይፈፅማሉ።*






*ጌታ ጸጋ ሰጥቶን ብዙ ታገሥን። በመሥሪያ ቤት የጤና ጥበቃው ጽ/ቤት ባለሥልጣኖች በሆስፒታሉ ንብረት ላይ ያለ አግባብ ያደርጋሉ። ለእነዚህ ጉዳዮች ሁሉ ዓይን ለዓይን - ለጥርስም ጥርስ መመለስ በተቻለኝ ነበር። ነገር ግን ይህ የጌታ መንገድ አይደለም።*

ዶ/ር ብርሃኑ በዉጭ የሚያጋጥማቸዉን ትግል ከእህቶች ጋር እያስተያዩ መግለፃቸዉ ኑሮ ምን ያህል እንደ ከበዳቸዉ ያስረዳል። ጳጉሜ 1 ቀን በያዙት ማስታወሻ፦ ‹‹በሥጋ ያለው ኑሯችን ከደረጃው በጣም ዝቅ ያለ ነዉ። ... በዓለማውያን እንኳ መካከል እንዲህ አይነት የማንጓጠጥ ነገር ደርሶብኝ አያውቅም፤ መታገሥ ባቃተኝ ጊዜ ልገሥፃቸዉ ስሞክር ትንሽ ደንገጥ የምትለዉ አንዷ እህት ብቻ ነች፤›› ብለዉ ነበር። ይህም አለመግባባቱ ውስጣቸዉን እማሳመም ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ ያመላክታል።

በጠቅላለዉ በመንፈሳዊም ሆነ በምድራዊ ሕይወታቸዉ የሚጋሩት ቁም ነገር መኮሰሱን የተገነዘቡት የጎባ ሙሉ ወንጌል ሽማግሌዎችና ሁለቱ ሐኪሞች ጉዳዩን እንደገና ተመካከሩበትና ሦስቱም እህቶች ቤቱን ለቀዉ እንዲወጡ ወሰኑ። ነገር ግን የሚከራይ ቤት ተፈልጎ እስከሚገኝና ተረጋግተዉ የሚወጡበት ቀን እስከሚመቻች መታገሥ ያቃታቸዉ ሁለቱ እህቶች ድንገት ተነሥተዉ እቃቸውን ጠቅልለው ቤቱን ለቀዉ ወጡ።

በሁለቱ እህቶቿ ፈጥኖ መሄድ የተደናገረችዉና እግዚአብሔርን ባለችበት ለመጠበቅ የወሰነችዉ እህት



ሲስተር አልማዝ ታረቀኝ

ይመስገን - ብለዉ:: በዚህ የመጠበቅ ድባብ ውስጥ እንዳሉ አባታቸው የአሥር አለቃ ሀብቴ ወልደ ማርያም በፅኑ ታመው ሆስፒታል መግባታቸውን ሲሰሙ ወደ አዲስ አበባ መጡ:: በመጡበት ምሽት ጥቅምት 26 ቀን 1969 ዓም አባታቸው አርፈው ኖሮ በማግሥቱ የቀብር ሥነ ስርዓታቸው ተፈጸመ::

ቀደም ሲል የሦስተኛ ዓመት የሕክምና ተማሪ ሳሉ እናታቸውን አስታመው፣ ራሳቸዉ ገንዘዉ በመሪር ሃዘን የቀበሩት ዶ/ር ብርሃኑ የሁለቱም ወላጆቻቸው ማለፍ የፈጠረባቸውን ክፍተት እግዚአብሔር ሲሞላው ጊዜው ቅርብ እንደሆነ ተሰማቸው፣ምስጢራቸውን ለማስታወሻ ደብተራቸው አካፈሏት፤ እንዲህ ሲሉ፦ *‹‹አሁን የኄዋኔ መምጣት እየቀረበ ነው››::*

ሦስተኛው ወር ላይ ‹‹ለምን እኔን. . . ?›› በሚል ሰበብ ሲፈስ የከረመው የአልማዝ እምባ ተገታ:: ታህሳስ 28 ቀን 1969 ዓም ዶ/ር ብርሃኑ ይህን ማስታወሻ ጻፉ:: *‹‹አሁን ኄዋኔ መጣች››* ቀኗም የቀሪ ዘመናቸውን ውጣ ውረድ እየተደጋገፉ ለማለፍ የተስማሙባት ቀን ሆና ተመዘገበች::

ከዚያ በኋላ የዶ/ር ብርሃኑ ዐውደ ዕለት ስለ አልማዝ የሚያስነብበው በተለያዩ የፍቅርና የቁልምጫ ስሞች አልማዜ፣ የኔ ውድ፣ ውዴ፣. . . እያለ ሆኑ:: ከአሥራ አምስት በላይ በሆኑት የዐውደ ዕለት ማስተወሻዎቻቸዉ ውስጥ ከእግዚአብሔር ስም/ስሞች ቀጥሎ በብዛት የተነሳው





የሲስተር አልማዝ ስም መሆኑን ይህ ጸሐፊ ያረጋግጣል:: ይሁን እንጂ መጠኑን ያለፈ መንሰፍሰፍ እንዳይጫናቸው ፍፁም ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፤ የአጅሬ ልጅ አይደሉ?!
አንድ ቀን ራሳቸውን ሲመዝኑ እንዲህ አሉ፦

> *‹‹ሕይወቴን ስመረምር በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንዳለሁ አሁንም እርግጠኛ ነኝ:: (ቀደም ሲል) በኑሮ በሎል ብቸኛ ነበርኩ:: አሁን ኄዋኔ መጥታለች:: ራሴን የሚያስገርመኝ ነገር ምንም እንኳን ትልቅ ጉዳይ በሕይወቴ ውስጥ ቢፈጸም ከጌታዬ ጋር ያለውን ግንኙነት አልነካብኝም:: ኄዋኔ ጌታ ለእሷ የሰጣትን የሕይወቴ ክፍል ይዛለች እንጂ በእኔና በእርሱ መካከል ግድግዳ አልሆነችም:: እግዚአብሔር መንገዳችንን በንጽህና እንዲሚጠብቀው አምናለሁ::››*

የሁለቱ ወጣቶች ለጋብቻ መፈቃቀድ ቀደም ሲል የነበራቸውን ቤተሰባዊ ነፃነታቸዉን አሳጣቸው:: ለነገሩ የዚያን ዘመኑ የጎባ የክርስቲያን ኅብረተሰብና አጠቃላይ ማሕበራዊው ዐውድ የነፃነት ንፍገት ቢንጸባረቅበት ድንቅ አይደለም:: ከቅርቦቻቸው ጋር ምክር ተደረገና ‹‹አልማዝ አሥራ ሁለተኛ ክፍልን አዲስ አበባ ብትማር ይሻላል›› ተባባሉ:: ለምን? ለወገኖች ህሊና ሲባል:: በ1970 ዓ.ም ልክ የሃያ ዓመት ወጣት ሳለች ሺመልስ ሃብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባች:: ከወገኖች ቤት - ወደ ዘመዶች ቤት፣ ከዚያም እንደገና ወደ ወንድሞች ቤት እየዘተዋወረች ተማረች::

ቆይታዋ የተደላደለ አልነበረም:: ስለሆነም የማትሪክ ውጤቷ እንደ ጠበቀችው ወይም እንደ ምትመኘው አልመጣላትም:: ‹ስንት› እንደሆኑ የማይታወቁ ሌላ የመጠበቅ ጊዜያት ለማሳለፍ ተገደደች::

ደግነቱ ዶ/ር ብርሃኑ በአላሰቡበት ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው መምጣታቸው የኑሮ ፈተናዋን አሳጠረላት እንጂ። ሆኖም በአንድ ሠፈር ወይም ቤት ውስጥ ሳይሆን በአንድ ከተማ የአሳለፉት ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ብቻ ነበር። ሐምሌ 23 ቀን 1971 ዓም ዶ/ር ብርሃኑ ለትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር ሄዱ። ከመሄዳቸው በፊት ግን ‹ከውዳቸው› ጋር የቃል ኪዳን ቀለበት አሠሩ።

ወይዘሪት አልማዝ የእግዚአብሔርን ቸርነት በሙላት፣ የእጮኛዋን ፍቅር ያለ ስስት የምታገኝበትን ቀን እየተጠባበቀች ለመኖር ሰባት ዓመታት መቁጠር ግድ ሆነባት።

## 8.4. ጋብቻ

የሰባት ዓመት እጮኛሞች ጋብቻ ከመፈጸማቸዉ በፊት አቅጣጫ ቀያሽ የሆኑ የሕይወት ጉዞዎችን አሳልፈዋል። የዶ/ር ብርሃኑ ርምጃዎችና ስኬቶች ቀደም ብለዉ የተጀመሩና የሚጠበቁም ነበሩ። ለወይዘሪት አልማዝ ግን ሁሉም ነገር ድንገተኛ ነበር።

አንዱ ‹የመጠባበቅ› ምዕራፍ በድንገት ተዘጋ። በርካታ የትምህርት ዕድሎች፣ ሥልጠናዎች፣ የስራ ዕድሎች በየተራ ሲመክኑባት የከረመችው አልማዝ የሥራ ማስታወቂያ መውጣቱን በድንገት ሰምታ ጎባ ወረደች። ከብዙ ተማሪዎች ጋር ተወዳድራ በነርስነት ለመሠልጠን ነቀምት ሆፒታል ገባች። ከዚያም ተመርቃ ዶዶላ (ባሌ) ተመደበች። ዶዶላ ሲስተር አልማዝ ከተወለደችበት አደባ ጥቂት ኪሎሜትሮች





ብቻ ነው የሚርቀው። አዎ በስደት ዕምባዋን እያፈሰሰች ከወጣችበትና ዘመድ አዝማድ አይንሽ ከአፈር በአላት ቦታ ተመደበች፣ ዘመዶቿን፣ አሳዳጆቿን ልታገለግል። እንግዲህ እኛም ‹ሲስተር አልማዝን በእርሰዎታ ልንጠራቸው ነው።

አዎ ሲስተር አልማዝ የዶዶላ ቆይታቸው ባለ ብዙ ምርኮ አድርጓቸዋል። ሁለቱ ፈፅሞ መረሣት የሌለባቸው ናቸው። አንደኛው ከክርስቲያን ወገኖቻቸዉ ጋር ሕብረት መመሥረታቸው ነው። በተጨማሪም የተሰማሩበት የሕክምና ሙያ ለአካባቢዉ ህብረተሰብ እጅግ ጠቃሚና ክቡር ከመሆኑ ባሻገር እሳቸዉም ከሚያሳዩት ትጋት የተነሳ በወቅቱ በዶዶላ ከተማ ውስጥ በስደት ላይ ለነበሩት ወገኖች የመጠለያ ድንኳን ለመሆን ዕድል ማግኘታቸዉ ነዉ።

ሁለተኛው ምርኮ በተማሪነት ዕድሜያቸው ስለ ወንጌል ሲሉ የአሳደዱአቸውንና የራቁአቸውን ዘመዶቻቸውን መልሰው ‹ገንዘብ› ለማድረግ አመቺ አጋጣሚ ማግኘታቸው ነው። አሁን አባታቸውም ሳይቀር ሠርጋቸው ላይ እንዲገኙ ሲጋበዙ ላያንገራግሩ ይችላሉ። በእውነትም የሆነው እንዲሁ ነው።

***

ዶ/ር ብርሃኑ ከእንግሊዝ አገር መልስ የኩላሊት ሕክምና ስፔሺያሊስትና በተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ የዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው አገራቸውን እያገለገሉ ነው። አገራቸው ግን መጽሐፎቻቸውንና የግል መጠቀሚያ ዕቃዎቻቸውን የሚያስፍሩበት የኪራይ ቤት እንኳ ልትሰጣቸው ልቻለችም። ይህንን ለማግኘት የህሊና ዳኝነትን ገሸሽ አርጎ በአቋራጭ የመሽሎክለክን ችሎታ ይጠይቃል። እሳቸዉ ግን ለዚህ

የሚመች ሰብዕና የላቸውም፡፡ በእምነት መንትያቸዉ ሚናስ ብሩክ በሰጧቸው አንድ ጠባብ (ሰርቪስ) ክፍል መኖር ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ ሁኔታውን አቶ ሚናስ ያስታውሱታል፡፡

*‹‹በዚያን ጊዜ የኔም ቤት ቢሆን ገና ተሠርቶ አላለቀም፡፡ እንግሊዝ አገር ከመሄዱ በፊትም አርፎበታል፡፡ ይህንን እያወቀ ከእኛ ቤተሰብ ጋር ለመኖር ወሰነ፡፡*

*ሻወር፣ ባኞ ብሎ ነገር የለውም፡፡ ታዲያ ብርሃኑ ምን ቸገረው ውኃ በባልዲ ቀድቶ ብረት ምጣድ ላይ ሆኖ ይታጠባል፡፡*

*ክረምት ሲሆን ሰፈሩ ይጨቀያል፡፡ ብርሃኑ ደግሞ መኪና አልነበረውም፡፡ ቦት ጫማ ተጫምቶ፣ ዣንጥላ ይዞ ይሄዳል እንጂ አገልግሎት አይሰርዝም፡፡ ዣንጥላ የሚይዘው ለዝናብ መከላከያ ብቻ አይደለም፡፡ ፀሐይ ሲከርበትም ይጠቀማል፡፡*

*ታዲያ አንድ ቀን አንድ ዘመናዊ ወጣት ዣንጥላውን አስታኮ አሽሟጠጠው፡፡ ‹ወዳጄ እኔ የሚጠቅመኝን አውቃለሁ!› ሲል መለሰለት፡፡ ብርሃኑ ያመነበትን ያደርጋል፣ የይሉኝታ እስረኛ ሆኖ አያውቅም፡፡››*

የኑሮ ምቾትን በተመለከተ ዶ/ር ብርሃኑ አዲስ አበባ፣ ሲስተሯ ነቀምት ወይም ዶዶላ ከመሆናቸው በስተቀር ያው የተለመደው ‹‹ሀበሻዊ›› ነበር ማለት ነው፡፡ ስድስተኛ ዓመቱን የያዘው ፍቅራቸው ግን ውጣ ውረዱን ሁሉ አልፎ፣ በመከራ ቅጥልጥሎሽ ተፈትኖ ነጥሮ ይበልጡን እየረጋና ስር እየሰደደ ሄደ፡፡ እንግዲህ በጋብቻ አንድ ሥጋ ለመሆን ምን ይከለክላቸዋል? ምንም፡፡ ሲስተሯ ለእረፍት በመጡበት አጋጣሚ ጥር 11 ቀን 1974 ዓም የጋብቻውን ቀን ቀረጡ፡፡





ይህንኑም በየወገናቸው ለሚቀርቧቸዉና ለሚመለከታቸው ሰዎች ለማብሰር ተስማምተው ተለያዩ፡፡

ሲስተር አልማዝ ዘረ ብዙ ናቸው፡፡ ወንድምና እህት ብቻ ሃያ አንድ አላቸው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ግን በጊዜዉ በድፍን አዲስ አበባ የቀራቸው የሥጋ ዘመድ አንድ እህት ብቻ ነበር፡፡ ታናሽ ወንድማቸው አዲስ አበባ አልነበረም፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ



ከእንግሊዝ አገር መልስ ሲስተር አልማዝ ነቀምት (ወለጋ) የነረሶች ት/ቤት ሄደው በጎበኟቸው ወቅት

የልባቸውን ነገር ለማንም የሚናገሩ ቦልባላ ሰው አይደሉም እንጂ ከሥጋ ዝምድና በበለጠ በክርስቶስ ፍቅር የሚቀርቧቸዉ ብዙ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች አሏቸዉ፡፡ ከእነዚህ ወገኖቻቸዉ መካከል ጋብቻቸዉ ዋዜማ ላይ መድረሳቸዉን ለማብሰር የመጀመሪያዉ የአደረጓቸዉ አቶ ሚናስ ብሩክን ነበር፡፡ አቶ ሚናስ ሁኔታውን የሚያስታውሱት ራሳቸዉን በሳቅ አጅበዉ ነው፡፡



ከእንግሊዝ አገር መልስ ሲስተር አልማዝ ነቀምት (ወለጋ) የነረሶች ት/ቤት ሄደው በጎበኟቸው ወቅት

*‹‹በቀጠሮአችን ቀን እሱ በሚኖርባት ክፍል ዉስጥ ተገናኘን:: አንገቱን ዘምበል አድርጎ እጆቹን እያፍተለተለ ትዕግሥትን የሚፈታተኑ ጥቂት ደቂቃዎች ፀጥ አለ:: እኔም ምን ሆኖ ይሆን? ምን ደርሶበት ይሆን?. . . ምናልባት ሳናውቅ አሳዝነነው ይሆን?. . . እያልኩ በሃሳብ ናወዝኩ:: መጨረሻ ላይ የሚነገረዉን ቃል አምጦ - አምጦ:- አሁን አንተን የፈለግሁበት ጉዳይ ሠርጌ . . . ማለት እኔና አልማዝ ልንጋባ መሆኑን ልነግርህ ነው. . . ሲል እኔ በሳቅ ፈነዳሁ::››*

ታዲያ ይኼ መርዶ አይደለ! የምሥራች እንጂ፤ ታዲያ ይህንን ለመናገር ምን አስጨነቀህ!? ከአልኩት በኋላ ዘና ብለን ስለ ፕሮግራሙ ማውራት ቀጠልን (ረዥም ሳቅ):: ድግሱንና ሌሎች የሠርግ ቅድመ ዝግጅቶች የማስተባበሩን ሥራ እኔና ባለቤቴ በኃላፊነት እንደምንወስድ ነገርኩትና ‹‹ነፃ ለቀቅሁት››:: በጣሙን ተደሰተ::

የዶ/ር ብርሃኑ ድርሻ የጀመሩትን ቤት አጣድፎ መጨረስ፣ በቤተክርስቲያን የሚፈጸመዉን ሥነ ስርዓት መልክ ማስያዝ፣ ሚዜ መምረጥ፣ የጥሪ ካርድ ማዘጋጀት፣ ዋና ዋና የቤት ዕቃዎች ማሟላት:: ከሁሉም በላይ ቤት!

## 8.5. የጎጆ ነገር

እንደ ሌሎች ጓደኞቻቸዉ በትርፍ ሰዓታቸዉ ሠርተዉ ገንዘብ የማጠራቀም ፍላጎት የሌላቸዉ ዶ/ር ብርሃኑ የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ቦታ ተመሩ:: ቤት ለመሥራት የሚያስችል ጥሬ ገንዘብ ግን በኪሳቸው አልነበራቸውም:: እግዚአብሔር ግን በመልካምነቱ ልዩ የባንክ ሂሳብ ከፍቶላቸዉ ነበር:: ታሪኩ እንዲህ ነዉ:: ስኮትላንድ በነበሩበት ጊዜ እጮኛቸዉ ገና





ተማሪ እንደ መሆናቸዉ ለግል መጠቀሚያቸዉ በየወሩ የተወሰኑ ብሮች ይልኩላቸዉ ነበር:: ሲስተር አልማዝ ደግሞ በሚላክላቸዉ ገንዘብ እንደ አቻዎቻቸዉ መሽቀርቀር ሳያምራቸዉ የተላከላቸውን ገንዘብ ሽርፍራፊዎቹ ሳይቀሩ ባንክ ያስቀምጡ ኖሯል:: በሲስተሯ የባንክ አካውንት ውስጥ የተቀመጠዉ ገንዘብ ወለዱ ብቻ ከሁለት ሺህ ብር መብለጡን ያወቁት ቦታዉን ከተመሩ በኋላ ነበር:: የቤት መሥሪያው እርሾ ተገኘ ማለት ነው::

ነገር ግን ወቅቱ የስደት ዘመን እንደ መሆኑ በሁሉም የከተማዉ ማዕዘናት የተበተኑትን የቤት ዉስጥ ኅብረቶችን የመከታተሉ ሩጫ ለመሪ አገልጋዮች ፋታ የሚሰጥ ሥራ አልነበረም:: ዶ/ር ብርሃኑ ደግሞ የቀረው ይቀራል እንጂ ከተጣለባቸው አገልግሎት ይልቅ ለራሳቸው ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጡ ሰው አይደሉም:: እና ቤቱን ማን ቆሞ ያሠራው ይሆን?!

በእርግጥም ሥራውን ለኮንትራክተር ሰጡ:: ባለቤት ያልቆመበት ሥራ ግን ኪሣራው ብዙ ነው:: ቢሆንስ? የጌታን ቤት ይሥሩ? ወይንስ የራሳቸውን ቤት ቆመው ያሳንፁ! ለዚህም እግዚአብሔር መውጫ አለው:: ዊንጌት፣ ዩንቨርሲቲ፣ ጎባ፣ ግላስኮ፣ እንደገና ዩኒቨርሲቲ (ጥቁር አንበሳ) ሳይለያዩ የቆዩት የቅርብ ጓደኛቸው ዶ/ር ሚልኪያስ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ጠይቀው ኖሮ ዶ/ር ብርሃኑ ቦታ ጎን ደረሳቸው:: የሁለቱም ቤት ግምባታ ጎን ለጎን ተጀመረ:: ቀጥሎም ቤቱ በሚሠራበት የቅርብ ርቀት ዶ/ር ሚልኪያስ ቤት ተከራይተው ገቡ:: የሁለቱንም ቤቶች ሥራ

ለመከታተል ተመቻቸው። ያለ ብዙ ንብረት ብክነት ሥራው ቀጠለ።

የሲስተር አልማዝ አካውንት ተሟጠጠ። በባሕርያቸዉ ደግሞ መበደር አይወዱም። ለጋብቻ የተቆረጠዉን ቀን ግን ወደ ፊት መግፋት አልፈለጉም፤ ስለሆነም እያንገራገሩም ቢሆን ከባንክ በተበደሩት ገንዘብ በከፊል ተጠናቀቀ። እሳቸዉ ደግሞ ከመሥሪያ ቤታቸቸዉ የዓመት እረፍት ፈቃዳቸዉን ወስደዉ ከአባታቸዉ በወረሱት ሁለ ገብ ሙያ የመስኮቱን መጋረጃና ጥቃቅን የዉስጥ እነፃዎችን በሚወዱት መልክ ሠሩ፤ እና ሰኔ 25 ቀን 1975 ዓም ገቡበት።

በአዲሱ ቤታቸው ሐምሌ 10 ቀን 1975 ዓም ከአልማዝ ጋር በጋብቻ አንድ ሥጋ ለመሆን ገና አሥራ አምስት እንደ መጫኛ የረዘሙ ቀናትን መቁጠር ነበረባቸው።

## 8.6. ሰባት ዓመት እንደ 7 ቀን

ሰባት ዓመት!! በእጮኝነት መቆየት አይከብድም? የሚሉ ሰዎች አይጠፉም። «የእጮኝነት ዘመን ሁለት የማይተዋወቁ ሰዎች አንድ ላይ ለመኖር ባላቸው መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ የመጠናናት፤ የማቀድና አብሮ ለመኖር የመወሰኛ ጊዜ ነው።

የጊዜው ርዝመት እንደ ሰዎቹና በህይወት ጉዟቸዉ እንደሚገጥማቸው ሁኔታ ሊወሰን ስለሚችል አንድ ወጥ ቀመር /ፎርሙላ የለውም» ይላሉ ሲስተር አልማዝ። አክለዉም፦ «እኔና ባለቤቴ በእጮኝነት የሕይወት ጉዞ ሰባት ዓመታት አሳልፈናል። ይህንን ያህል ጊዜ ቢወስድብንም





ሁለመናችንን ተጠናንተን አብቅተን ነበር፤ ለማለት አልደፍርም፤ ምክንያቱም የሰው ባህርይ ጥልቅና ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም በቀላሉ ሊያዉቀውና ሊረዳው የማይችል ባህር ስለሆነ ነው፤ በዚህ ረገድ የደረስኩበትን መረዳት የእግዚአብሔር ቃልም ይደግፈኛል።

የእጮኝነት ዘመኔን ሠላሳ አራት ያህል ዓመታት ወደ ኋላ ሄጄ በዓይነ ሕሊናዬ ሳስበዉ በጣም የሚናፈቅና የሚወደድ ጊዜ እንደነበር እመስክራለሁ። ሁለታችን ለመገናኘት የምንይዛቸዉን እያንዳንዱን ቀጠሮዎች የምንጠብቀዉ በጉጉት ነበር። የወደ ፊት ሕየወታችን ፍጹም መከባበርና መቀባበል የሰፈነበት፤ በእግዚአብሔር ፍርሃት ስር ትዳራችንን ለመምራት የምንጓጓበት፤ አንዳችን ስለ ሌላችን የጸሎት ሸክም የምንለዋወጥበት ጊዜ ነበር። በሌላ በኩል አንዳችን ለሌላችን ከነበረን ስስት የተነሣ የአንዳችን እንከን ለሌላችን የማይታይበት፤ ምናልባት ማጋነን ባይሆንብኝ የመንግሥተ ሰማያት ኑሮን ቅምሻ በምድር የተለማመድንበት ሕይወት ይመስል ነበር ማለት ይቻላል።»

አባባላቸዉን የሚያጠናክር አንድ ነጥብ አላቸዉ - ሲስተሯ። «የሁለታችን የትዳር ግንኙነት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተጀመረ እንደሆነ ፈጽሞ አምን ነበር። ስለሆነም የአንዳችን ድካም ለሌላችን እንደ ሸክም ሳይሆን ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ እርስ በርስ በመደጋገፍ በእግዚአብሔር ፍርሃት የታነጸ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ በመመሥረት ክርስቲያናዊ ሕይወትን የምንለማመድበት ኑሮ እንደሚሆን አምኜና ምኞቴም እዉን የሚሆንበትን በጋብቻ አንድ የምንሆንባትን

ዕለት በጉጉት የምጠባበቅበት ወቅት ነበር። በነገራችን ላይ ይሄ ስሜት ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰው ይመስለኛል።››

## *8.7.ትዳርና - ኑሮ*



ሙሽሪት አልማዝ

ሰባት ዓመታት በትግዕሥት፣ በጸሎት፣ በንፅህና ነገር ግን በናፍቆት ሰቀቀን የጠበቋት ማለዳ መጣች። እዉነተኛዉ *አባ-ወራና* እዉነተኛዋ *እማወራ* በገሃዱ ዓለም የሕይወት ዐዉድማ በትዳር ምዕራፍ የሚፈተሹበት ቀን ከተፍ አለ። ዋዜማው ፍፁም ጸጥተኛ ነበር። ጥሎሽ መጣል - አለመጣል ብሎ መጨነቅ የለ፣ ግርግር የለ፣ ምስጋናና ጸሎት ብቻ!

ከጥቂት ቀናት በፊት ከዶዶላ መጥተው የነበሩት ሲስተር አልማዝ በማለዳው በአቶ ሚናስ ቤት ከሚዜዎቻቸው ጋር ‹መፈሸን› ጀመሩ።

የወንድ ሚዜዎች በየቤታቸው ተዘጋጅተው አምረው ደምቀዉ ዶ/ር ብርሃኑ ቤት ደረሱ፤ ደረሰባቸው! ማለቱ ይሻል ይሆን? ዕለቱን ሲናፍቁት እንዳልነበረ በግድ የደረሰባቸውን ያህል ዘንጋ ያሉ ይመስላል።

*‹‹ቶሎ በል እንጂ! ፈጠን ፈጠን!›› ዶ/ር ሚልክያስ ነበሩ።*





*‹‹ቶሎ እያልኩ ነው!››*

*‹‹የታለ የለባበስከው!›› ሌላው ሚዜ ዶ/ር አታላይ።*

*‹‹ይኸው! ልለብስ እኮ ነው›› አሉና የሆነ ቤዥ ቀለም ኮትና ሱሪ ሱፍ ከቁም ሳጥን አወጡ።*

*‹‹እህ! ይኼንንማ ለመልሱ አድርገው፤ ያኛውን አዲስ አለኝ ያልከውን››*

*‹‹ይኼ እኮ ነው! አሪፍ አይደል!?››*



*ሙሽራው ከሚዜዎቹ ጋር። ከግራ ወደ ቀኝ ዶ/ር አታላይ ዓለም፣ ዶ/ር ሚልኪያስ፣ ሙሽራው ዶ/ር ብርሃኑ፣ አቶ ግርማ*

በመሠረቱ ልብሱ ጥራት ያለው ሱፍ ነው። ነገር ግን በዘመኑ ፋሺን መሠረት ጥቁር ወይም ጥቁር ሰማያዊ ሱፍ ቢሆን ይመረጥ ነበርና በአንደኛ ሚዜአቸዉ በዶ/ር ሚልክያስ ውትወታ ከሳምንት በፊት የገዙትን ሱፍ ቀየሩ። ‹‹እሺ! በቃ!

ይሁን! ልበስ! ልበሰው!›› በሰዓት ገደብ ምክንያት የአሰበውን ለማድረግ ባለ መቻሉ እየተቆጨ ሚዜው ሁሉ ተንጫጫ:: ሙሽራዉ ቦላሌአቸውን አጠለቁ:: ሊለብሱ ያሰቡት ሸሚዙ ሲታይ የባሰ ሆነ:: በሚዜዎቹ ሚዛን ለሱፉ አላባሽ የማይሆን የተለበሰ ሸሚዝ ነበር፡-

*‹‹ሌላ ሸሚዝ የለህም?›› አሉ ዶ/ር አታላይ::*

*‹‹ምልቷል እንጂ! እንካ ምረጥ::››*

ቢመዘዝ - ቢመዘዝ የሚዜዎቹን ምርጫ የመጠነ የሠርግ ሸሚዝ አልተገኘም:: ጊዜው እየከነፈ ነው:: ሱቅ ሄዶ ለመግዛት ጊዜ የለም:: ምን ይደረግ!? የሚዜዎች ስሜት ድፍርስርስ አለ:: የሙሽራዉ ፊት በአሻንጉሊት



*ከጋብቻ ሥነ ስርዓት ፍፃሜ በኋላ-በልደታ መካነ ኢየሱስ ቤ/ክ*

እንደሚጫወት ጨዋ ሕፃን በፈገግታ ስሜት ተወረሰ:: ‹‹ግን ዛሬ ጠዋት አንድ ሰዉ ያመጣልኝ አዲስ ሸሚዝ አለ›› አሉ በፈገግታ:: ይህኛዉም ቢሆን ከአዲስነቱ በስተቀር በጥራቱ






ቤት ከነበሩት የተሻለ አልነበረም:: ዕድምተኞችና ምዕመናን መጉላላት የለባቸውም፤

*‹‹በቃ! ይሁን - ይሁን! ይህንኑ ልበሰው!›› አሉ*

ሚዜዎች ተደራርበዉ እየተናገሩ::

*‹‹Yes! አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሳለህ እግዚአብሔር ቀድሞ የአዘጋጀልህ ምርጫ እሱ ውብ አማራጭ ነው!››*

አሉ ሙሽራው:: ከፊተኛዉ በበለጠ በፈገግታና በደስታ ስሜት ተውጠው::



*ሙሽሮችና የሙሽሪት አባት አቶ ታረቀኝ ወልደየስ*


ጉዞ ወደ ሙሽሪት ቤት:: ከዚያም ወደ ልደታ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን:: የሰባት ዓመቱ ናፍቆት በዚያ ተደመደመ:: ሕይወት ግን ይቀጥላል:: ...




ከጋብቻ ሥነ ስርዓት ፍፃሜ በኋላ-በልደታ መካነ ኢየሱስ ቤ/ክ



ሙሽሪት አልማዝ



*ሙሽራው ከሚዜዎቹ ጋር። ከግራ ወደ ቀኝ ዶ/ር አታላይ ዓለም፣ ዶ/ር ሚልኪያስ፣ ሙሽራው ዶ/ር ብርሃኑ፣ አቶ ግርማ*



ውባለም ታፈስ

አዲሱ ጎጆ ሲጀምር ሦስት የቤተሰብ አባላት ነበሩት፡፡ ሦስተኛዋ ውባለም ነች፡፡ ውባለም በልጅነት ዕድሜዋ ዘመድ ለመጠየቅ ወላጆቿ ከሚኖሩበት የሐረር ገጠር ወደ አዲስ አበባ መጣች፣ ዘመዶቿ ወደሱቅ ይልኳትና ስትመለስ የነበረችበት ቤት ጠፍቷት ስትባዝን፣ ሰዎች ድንገት አግኝተው በኋላ ወደ አሳደጓት ቤት ወሰዷት፡፡

በዚያም ቤት ለብዙ ዓመታት እየኖረች ሳለ እነዶ/ር ብርሃኑ ቤቱን ለፀሎት ቤት (የንፋስ ስልክ ፀሎት ቤት) ተከራዩት፡፡ ወንጌልን መሰከሩላት፡፡ በኑሮ በኩል ብዙ ባትደላደልም በእምነቷ ግን ጸንታ ኖረች፡፡ በኋላም ለዶ/ር ብርሃኑ ካላት ፍቅርና አብራ ለመኖር ከነበራት ፍላጎትም የተነሳ አብሮ ለመኖር ወስና፣ ሰኔ 25 ቀን 1975 ዓ.ም ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር አዲስ ወደ ሠሩት ቤት ገባች፡፡

እንደ አባትና ልጅ ሆነዉ ሊኖሩ ተስማምተዉ አዲሱን ቤት አደራጀች፤ ቆማ ዳረች፤ ጽንኤልና ቤርሳቤህን አሳደገች፡፡ ይኼው እስከ አሁን ድረስ ታማኝ የቤተሰቡ አባል ሆና ትኖራለች፡፡ ገና ከመጀመሪያው ኑሮው እግዚአብሔርን ማገልገል፤ አገልግሎቱንም ‹የመኖሩ ዋና ፋይዳ› አድርጎ





እንዲቀበል በአባወራው በተቀረፀዉ ቤተሰብ ዉስጥ የዉባለም ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

አንድ ምሳሌያዊ ድርሻዋን እንመልከት፡፡ አሁን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እጅግ ምርጥ ከሆኑት ሰፈሮች አንዱ የሆነው በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/05 በዚያን ጊዜ ገና አለማም ነበር፡፡ ፀጥታ የነገሠበት እና ጭር ያለ ነበር፡፡ ወቅቱ የስደት ዘመን እንደ መሆኑ ህቡዕ መንፈሣዊ ፕሮግራሞች ለማካሄድም የሰጠ አካባቢ ነው፡፡ ስለሆነም በእነ ሲስተር አልማዝ ቤት መደበኛ የሆኑና ያልሆኑ በርካታ ስብሰባዎች ማካሄድ የተጀመረው ወዲያው ነበር፡፡



የሚጉላ ሰምን

የጸሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የአምልኮ ፕሮግራም፣ ኮንፈረንስ፣ የቅዱስ ቁርባንና የጥምቀት ፕሮግራም... ዓይነቱ ብዙ ነው፡፡ ወጪ ገቢውን ማስተናገድ፣ የተዝረከረከውን መሰብሰብ፣ ወለሉን ወልወል፣ እንደገናም ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ውባለምና ሲስተር አልማዝ በውዴታ የተሸከሙት ኃላፊነት ነበር፡፡ ሽክሙ አንዳንድ ጊዜ ወደ ውባለም ያጋድላል፡፡ ሲስተር አልማዝ ይመሰክሩላታል፡፡

> *‹‹የበኩር ልጃችን ጽንኤል በደንብ ሳትጠነክር ነበር ቤርሳቤህን የወለድኩት፡፡ እራስ ቤት በተኛሁበት ሰሞን የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ይካሄድ ነበር፡፡ ቀደም ብሎ ስላልተነገረን በቂ ዝግጅት አላደረግንም ነበር፡፡ ብርሃኑ ግን ያውቅ ነበር፡፡*



ውባለም ታፈሰ



የጫጉላ ሰሞን

*አዳዲስ አማኞች የሚጠመቁትበት ገንዳ ለዚህ አገልግሎት ተብሎ ያልታሰበ በማንኛዉም ቤት የሚገኝዉ ዓይነት ያለ የገላ መታጠቢያ ገንዳ ነው፡፡*

*ተጠማቂዎቹ ወደ ገንዳው የሚሄዱት የመኝታ ክፍላችንን አቋርጠው ነበር፡፡ በዚያ ላይ መዝሙር አለ፣ ሃሌሉያ አለ፤ ሌላም ጩኸት አይጠፋም፡፡ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ውባለምን ባያዘጋጅልኝ ኖሮ ያ የአራስ ቤት ገመና እንዴት ይሸፈን ነበር?!*

*ብርሃኑ መቸም የሚያስፈልገው መሰዋዕትነት ሁሉ ተከፍሎ የጌታ ሥራ መሠራቱ ብቻ ነው የሚያረካው፡፡ እኔም ሆንኩ ለሌሎች አራሶች ግን ሁኔታዉን ‹እልል ብሎ› ለመቀበል የሚያስቸግር መሆኑን መገመት አያስቸግርም፡፡ሁለት አራስ ይዞ ያንን ሁሉ እንግዳና መንፈሳዊ ሥነስርዓት ማስተናገዱ ይታየችሁ! ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋና በዉባለም መሰጠት ሁሉን ችለን ሁሉን አሳለፍነው፡፡ በአጠቃላይ ዉባለም ለቤተሰቡ ልዩ በረከት ነበረች፡፡››*

ይህ መሥዋዕታዊ የቤተሰብ ሕይወት እስከ 1983 መጨረሻ ድረስ ዘለቀ፡፡ ከባልና ሚስቱ በስተቀር ውባለም፣ ጵኒኤልና ቤርሳቤህ ግን ሌላ መስዋትነት እየጠበቃቸው እንደሆነ ያለ መገንዘባቸው ደግ ነገር! ኋላ ላይ እንመለስበታለን፡፡





## 8.8. አባ ወራዉ ብርሀኑ

ስለ አባ ወራዉ ብርሃኑ ከእማወራዋ የበለጠ የሚያዉቅ ማንም የለም፡፡ ከትልልቅ ዓይኖቻቸዉ የባቄላ ቅንጣት የሚያካክሉ የዕንባ እንክብሎች እያስተንጎሏቸዉ እንጂ ለበዙ



*ዶ/ር ብርሀኑና ሲስተር አልማዝ በመኖሪያ ቤታቸው*

ትዳሮች ስብራት መጠገኛ የሚሆኑ ልምምዶችን ባካፈሉን ነበር፤ (በፊታቸዉ ከሚጠብቋቸዉ አገልግሎቶች አንዱ ይህ ሳይሆን አይቀርም)፡፡ ይህ ጸሐፊ የሲስተር አልማዝን ምስክርነት ቃል በቃል ለማቅረብ የወሰነዉም እዉነታቸዉ ሳትሸራረፍ (አርጂናሌዋ) ለአንባቢ ማድረሱን አምኖበት ነዉ፤

ስለ አባ ወራዉ ብርሃኑ ከመናገሬ በፊት ስለ እውነተኛው ትዳር በጣም አጭር ቃል ለመናገር ብሞክርስ? ትዳር ማለት ሁለት




ዶ/ር ብርሀኑና ሲስተር አልማዝ በመኖሪያ ቤታቸው

የማይተዋወቁ ሰዎች አንድ ላይ ለመኖር እንዲያውም በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንደተጻፈው ሁለት መሆናቸው ቀርቶ አንድ ለመሆን አቅደውና ተስማምተው ቃልኪዳን ኑሮን የሚጀምሩበት /የሚመሠርቱበት/ ሕይወት ነው፡፡ በዚህ ሕይወት ውስጥ ሲታለፍ ብዙ በረከቶች እንዳሉ ሁሉ ብዙ ተግዳሮቶችም ሲገጥሙ ይችላሉ፡፡ እንደ ክርስቲያን ባለትዳሮች ለሁለቱም ሳይሸነፉ ለተገኘው በረከት ምንጩን እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ለሚገጥሙት ፈተናዎች /ተግዳሮቶች ከእርሱ ጸጋን እየለመኑ በእምነት መገጠሙ አማራጭ አይኖረውም፡፡ እንግዲህ ይህንን ያህል ካልኩ ስለራሴ ሕይወት ያሳለፍኩት እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

አባ ወራዉ ብርሃኑ ያዉ እውነተኛው ብርሃኑ ነዉ፡፡ ሁል ጊዜ በሥራ የተጠመደ፣ የጊዜ ስስት ያለበት፤ ዓለምን የናቀ፣ እንዲያውም ስለ ዓለምና በውስጧ ስለሚካሄዱት ሁኔታዎች ሲገልጽ ‹ይህች መጨቅጨቂት ዓለም እንደሆነች በቅጽበት ታልፋለች› እያለ የሚናገር፤ ለተሳካለት ነገር እግዚአብሔርን አመስግኖ የሚቀበል፤ ሳልተሳካው ደግሞ የግድ ካልሆነልኝ ብሎ ከጌታ ጋር የማይታገል፤ ለኑሮ እሽቅድምድም የማይሮጥ፤ በውጭም በቤቱም ውስጥ አንድ ዓይነት ባህርይ ያለዉ ሰው፣ በእግዚአብሔር የሚታወቀውን ሕይወቱን በሁሉም ሥፍራ የሚኖርና ማስመሰል የሌለበት፣ ግልጽና ድብብቆሽ ጨዋታ የማያውቅ፣ የማይሆንለትም፣ በሉቃስ 14፡ 25 ላይ እንደ ተገለጸው ስለ ወንጌል ሁሉን የተወ፤ በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነቱን ኑሮ ራሱ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡም ሆነ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ቢኖሩት የሚያስደስተው ሰው ነዉ፡፡ የእውነተኛው ብርሃኑ የጊዜ ስስት ምንጩ የጌታ ሥራ ነዉ፡፡ በተለያዩ አገልግሎቶች፣ በቦርድ ስብሰባዎች፣ የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸውን ሰዎች በመርዳት፣





በጥቅሉ ከቤተሰቡ ውጭ ላሉ ሰዎች አገልግሎት በመስጠት የተጠመደ ሰው ነው፡፡



ዳንኤል ብርሀኑ፣ሲ/ር አልማዝ፣ ቤርሳቤህ ብርሀኑ እና ዶ/ር ብርሀኑ

ሆኖም ልጆቹን በጣም የሚወድና አብሯቸው ብዙ ቢያሳልፍ የሚፈልግና የሚመኝ ግን እንደሚወደው ያልሆነለት ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ያለችውን ጥቂት ጊዜ በልዩ ጥንቃቄ ስለሚጠቀምባት (በተለይም ከልጆቹ ጋር) ጥቂቷን ጊዜ በቁም ነገር ላይ እንድትውል በማድረግ ምሳሌነቱንም የተወ ሰው ነው፡፡

አባ ወራዉ ብርሃኑ፡- ጊዜ ብቻ ሳይሆን ገንዘብም የሌለው፣ ወዶና ፈቅዶ፣ ደስ እያለውም የድህነትን ኑሮ ለመኖር የመረጠ፣ በዚህም ተፈትኖ ያልወደቀ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ማንኛውም አባት ለልጆቹ መልካም ቢያደርግላቸው የሚወድ ነበር፡፡



ጽንኤል ብርሀኑ፣ሲ/ር አልማዝ፣ ቤርሳቤህ ብርሀኑ እና ዶ/ር ብርሀኑ

## ጉርሻ

### እናት አባት ይሆናልን?

*ዳኒኤል ሳትጠነክር ቤርሣቤህ ተወለደች። እናት አዲሷን አራስ ሲንከባከቡ ዳኒኤል ብቻዋን በነበረችበት ጊዜ የሚሰጧት ትኩረት መቀነሱ አልቀረም። ያንን ለማካካስ (ሥራዬ ብለው ባይሆንም) አባት ባላቸው ጊዜ ሁሉ ለዳኒኤል ጥያቄዎች (መነጫነጮች ልቅሶዎች) ምላሽ ለመስጠት ሞከሩ። አባቷን የበለጠ መቅረብ ጀመረች። ስታጣቸው ደግሞ መነጫነጭ።*

*በህፃንነት ወራቷ አባት አሜሪካ አገር ሄደው ከወር በላይ ሰነበቱ። ከአሜሪካ ከተመለሱ ቀናት በኋላ ደግሞ ጋምቤላ ሄዱ። ዳኒኤል ታመመች። መብላት መጠጣት አቆመች። እናት ተጨነቁ። ሐኪም ቤት ወሰዷት፤ ህመሟ ‹‹ይህ ነው›› የሚባል ሆኖ አልተገኘም። ጤናዋ ግን ታወከ።*

*ችግሩን የሰሙ የቤተሰቡ ወዳጆች ዳኒኤልን ለመጠየቅ በእነዶ/ር ብርሃኑ ቤት እንደተሰበሰቡ አባት ከጋምቤላ መጡ። ዳኒኤል የአባቷን ድምፅ ስትሰማ ዓይኗን ገለጠች፤ ምንም እንዳልሆነ ሰው ከመኝታዋ ተነሣች፤ እንደ ወትሮዋም መጫወት ጀመረች። ለካንስ ሕመሟ ናፍቆት ነበር።*

*ከሰዓት በኋላ ዶ/ር ብርሃኑ ለባብሰው ወደ ውጭ ሲወጡ ሲሉ የምሯን አለቀሰች። የልጃቸው ህመም ምክንያት ናፍቆት መሆኑ የገባቸው ሲስተር አልማዝ ‹‹ኧረ እባክህ ናፍቆቷ እስቲ ወጣላት ድረስ አጫውታት!. . .›› አሉ ባለቤታቸውን - በመገረምና በቁጣ መካከል በሆነ ድምፀት። ልለርዘው የማልችል ቀጠሮ አለኝ፤ አንድ የማገለግለው ቤተሰብ አለ›› ሲሉ መለሱ። ወደ ልጃቸው መለስ ብለው ደግሞ ‹‹ዳኒዬ ቶሎ እመለሳለሁ! ከእናትሽ ጋር ተጫወቺ፤ እሺ?›› በማለት አባበሏት። **ህጻን ዳንኤልም ኃይለኛ በምብ - የቃል በምብ** ወረወረችባቸው፤ ከአሰቡት መንገድ አላስቀራቸውም እንጂ። ‹‹ታዲያ እናት አባት ይሆናል እንዴ!!!›› ነበር ያለቻቸዉ።*





አንዲት ምስክርነት ብሰጥ ደስ ይለኛል፡- በአንድ ወቅት ዕቃ ለመግዛት ወደፒያሳ ከኔ ጋር አብረን ሄድን አንድ ሱቅ ስንገባ ጥሩ የሆነ የልጆች መጫወቻ አየን፣ አስታውሳለሁ ዋጋው 54.00 ብር ነበር። ብርሃኑ መጫወቻውን መሳልሶ አየና እንድንገዛው ጠየቀኝ፣ እኔም ውድ ስለሆነና ትርፍ ገንዘብ በእጃችን ላይ ስለሌለ መግዛት እንደማንችል ነገርኩት። እርሱም <<ሕልሚ ልጆች እኮ ዋጋ ያስከፍላሉ እባክሽን እንግዛው>> አለኝና መጫወቻውን ገዛነው መጫወቻው በመገዛቱ በጣም ደስ አለው።

እውነተኛው ብርሃኑ ንጽሕና ይወዳል፤ የሕይወት ንጽሕና፣ የኑሮ ንጽሕና፣ ውበት ባይኖረውም፣ ዋጋው ቢረክስም - ንጽሕና። ምንም ብዙ አሸብራቂ ነገሮች ባይኖርበትም ንጹሕ ቤት ውስጥ ባርኩማ ላይ ቢቀመጥ ይወዳል፤ ምንም ባይጣፍጥ ንጹሕ ከሆነ ለምግብ ምርጫ የለውም፤ በነገራችን ላይ ይህ ለብዙ ወንዶች ችግር የሚፈጥር አነጋጋሪ አጀንዳ ነው። ብቻ ሕይወቱ በንጽሕና ጀምሮ በንጽሕና የተጠናቀቀስት ሰው ነው። እንግዲህ እንደዚህ ካለው ሰው ጋር ተስማምቶ ለመኖር /እርሱ በሚፈልገው ንጽሕናና ሕይወት ለመመሳሰል/ እጅግ ከባድ ስለሆነ የዓላማ ሰው መሆን እና ቆራጥ ውሳኔን ይፈልጋል፤ አለፍ ሲልም ልዩ ጸጋ ከእግዚአብሔር መቀበልን ይጠይቃል።

ይህ ምስክርነት በትውውቅ አንድ ዓመት፣ በእጮኝነት ሰባት ዓመት፣በጋብቻ ለሃያ አራት ዓመት ከሰባት ወር፣ ካወቅሁት ሰው የተሰጠ ማጋነን ያልታከለበት እውነተኛ ምስክርነት ነው። ከዚህ በላይ እንደ ገለጽኩት በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ትዳርም ቢሆን ብዙ በረከቶች እንዳሉበት ሁሉ ብዙ ተግዳሮቶችም ያጋጥሙታል። ነገር ግን ያስጀመረ እግዚአብሔር ኃላፊነትን

ስለሚወስድ በእርሱ እርዳታ ወደ መልካም ግብ ያደርሰዋል፡፡ በእኛም ትዳር ውስጥ የእኛም ዓላማ አዘል ውሳኔ ታክሎበት ከላይ የጠቀስኳቸውን ዘመናት አብረን ዘልቀናል፡፡ ይህን ምስክርነት ስሰጥ በመካከላችን ምንም ዓይነት ግጭት ኖሮ አያውቅም ለማለት አልደፍርም፡፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር እና ምናልባት አልፎ አልፎ ልጆቻችን (ጉዳዩን ከሰሙት) ካልሆኑ በስተቀር አማጊሌ ወይም ዳኛ በመካከላችን ገብቶ አያውቅም፡፡ ለዚህ አባትነቱ፣ ስላደረገልን ቸርነት ስላሳየን ፍቅሩና ርኅራሄው እንዲሁም በዚህ ውስጥ እንድናልፍ ለሁለታችንም ስለ ተሰጠን ጸጋው፣ በውስጡም ስለተካፈልነው በረከት እግዚአብሔር አምላኬን እጅግ አድርጌ አከብረዋለሁ፣ አመሰግነዋለሁም፡፡

## በትዳር ሕይወት ውስጥ የነበረው ትልቁ ተግዳሮት

እንደሚታወቀው ሁሉ ኑሮ ትግል ነው፣ይህን የትግል ሕይወት ታግሎ ለማሸነፍ ብዙ ውጣ ውረዶችን ማለፍ የግድ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በእኛ ቤተሰብ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ትግል ያለበትን ሕይወት መግጠም በዶ/ር ብርሃኑ አመለካከት /መረዳት/ ቦታ ስለሌለው ኑሯችን ሁልጊዜ የተለመደና አዲስ ነገር የማይታይበት ነው፡፡ አዲስ ነገር ለማግኘት ተዓምራትን የሚጠይቅ ስለሆነ በቤት ውስጥ ጥቂት የኑሮ ለውጥ ሲኖር በብዙ ምስጋናና አክብሮት ነው የምንቀበለው፣ በእርግጥ ስለ ሁሉም ነገር እግዚአብሔርን እንድናከብርና እንድናመሰግን ምክኒያት ሆኖልናል፡፡ ይህ ሁኔታ ነው እንግዲህ ብዙ ሰዎች የመሰከሩትና የዶ/ር ብርሃኑን ሕይወት አቋመ ጠንካራ ያደረገው፣ ለመንፈሳዊ ብስለቱም አስተዋጽዖ ያበረከተው፡፡ ሴት ከመሆኔና በእጄ ያለውን በጀት አብቃቅቶ ቤተሰብን ከማስተዳደር አኳያ ይህ አኗኗር ለእኔ ቀላል ተግዳሮት አልነበረም፡፡





የዶር ብርሃኑ የሕይወት ዘይቤ ቀን ሳለ የላከኝን ፈቃድ ሳደርግ ይገባኛል በሚለው እና ሉቃስ 14፡ 25 ላይ በተጻፈው ቃል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህን ዓይነቱን ሕይወት በጸጋ ተቀብሎ አብሮ ለመኖር ምንም እንኳን ሰባት የዕጮኝነት ዘመን ብናሳልፍም በዚህ አቋሙ አላውቀውም ወይም አልተረዳሁትም ነበር፡፡ ስለዚህም ይህንን ኑሮ ኑሮዬ ብሎ ለመቀበልና አሜን ለማለት ጊዜ ወስዶብኛል፡፡ ብዙ ባልተመቻቹ ሁኔታዎች ውስጥ አልፌአለሁና ለእኔ ቀላል ተግዳሮት አልነበረም፡፡ የዶ/ር ብርሃኑ ጊዜ በአብዛኛው በአገልግሎቶች፣ በቦርድ ስብሰባዎችና ለሌሎችም ሰዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ስለሚውል አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች እንኳን ከእርሱ ጋር ጠቃሚ ጊዜዎችን ለማሳለፍ ቀደም ብሎ ቀጠሮ መያዝ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ያም ቢሆን ቅድሚያ የሚሰጠዉ ለእግዚአብሔር ሥራ ነዉ፡፡ ይህም ቀላል ተግዳሮት አልነበረም፣ ስለዚህ እነዚህንና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች በጸሎትና እግዚአብሔርን አምኖ ከመቀበል ውጪ ሌላ አማራጭ ሲኖረኝ ስለማይችል ምስጢረኛዬና ገመናዬ በመሆን እግዚአብሔር እየደገፈኝ በጸጋው አቁሞኛል፡፡ ዛሬ ግን ማንም የማያውቀዉን አንድ ገጠመኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ብናገር እወዳለሁ፣ ምክንያቱም ለባለትዳሮች በተለይም ሁለንተናቸዉን ለጌታ ሥራ የሰጡ አገልጋዮች ልጆችና ባለቤቶቻቸዉ ይጠቅማል ብዬ ስለ አሰብኩ እነሆ ላካፍላችሁ፡፡

ሁኔታዉ የእኔም በጎ ፈቃድ ታክሎበት ለአገልግሎት የተከፈለ መስዋዕትነት ነው፡፡ እናቴ ለ7 ዓመታት ያህል ከእኛ ጋር ነበረች፣ወደ ጌታዋ በምትሄድበት ሕመም ታመመችና በ1994 ዓ.ም. ዐረፈች፡፡ (ጌታን ተቀብላ ለአራት ዓመታት ያህል አምልካው ነው ወደ ዕረፍቷ የሄደችው)፡፡

በዚያ ቀን 100 ለሚያህሉ በሚሲዮናዊነት ለሚያገለግሉ አገልጋዮች ሥልጠና ለመስጠት የሚጀመርበት ቀን ነበር፤ የስብሰባው የመክፈቻውን ፕሮግራም የሚያካሂደው ብርሃኑ ነበር፤ እናቴም ያረፈችው በዚህ ዕለት ማለዳው ላይ ነበር:: ብርሃኑ ሁለት አጣብቂኝ ውስጥ ወድቆ ግራ እንደገባው ተረዳሁ:: ፕሮግራሙን ለሚያስተባብሩት ሰዎች ደውሎ በመንገር የቀብሩን ጉዳይ ለመከታተል ወሰነ::

እንግዲህ የእኔ እናት ስለሆነች እንጂ ስለእርሱ እናት አሟሟት የሰማሁት ምስክርነት ትዝ አለኝ:: ‹እናቱን አስታሞ በእጁ ላይ ነበር ያረፉት:: ከገነዘና ካስተካከለ በኋላ ወደ ጸሎት ቤት ሄዶ ጸልዮ ሁሉን ለጌታ ካስረከበ በኋላ ነበር ለሚመለከታቸው ሰዎች መናገር የጀመረው:: ብዙ ባይጋነንም በታላቅ እህቱ ሞትም (እኛው ቤት ስለነበር ያረፈችው) በመጠኑ ይህኑ ሁኔታ ተጋርቼ ነበር፤ ዛሬ ደግሞ እኔም በተራዬ በእናቴ የቀብር ጉዳይ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ነበረብኝ::

ቀብሩን ዛሬ አናደርግም፣ ለዘመድ አዝማድ ይደወልና ነገ ሁሉም በተገኙበት እንሰናበታታለን፤ ስለዚህ አንተም ወደ አገልግሎትህ ሂድ፣ልጆችም ወደት/ቤት ይሂዱ፣እቤት ውስጥ ካለነው ሰዎች ውጪ ማንም ማረፏን እንዳይሰማ እንጠነቀቃለን፤ ምክኒያቱም ይህ ቀጠሮ ከሁለት ወር በፊት እንደተቀጠረ አውቃለሁ፣ሞቱ ግን ለማንም ቀጠሮ ሳይሰጥ በድንገት ስለሆነ የመጣው በድንገት የመጣውን እንግዳ ተረጋግተን አስበንበት በጌታ እርዳታ እንስተናግደዋለን አልኩት:: ያልጠበቀው ነገር ስለነበር ቢደንቀውም እግዚአብሔር ይባርክሽ በማለት ወደ አገልግሎቱ ሄደ::





እኔም ባለቤቴን ወደ አገልግሎቱ ልጆቼን ወደት/ቤት ከሸኘሁ በኋላ በተራዬ እናቴን እያለቀስሁ ብቻዬን ገነዝሁኝ:: ደግነቱ ነርስ በመሆኔ አልተደናገርኩም ሙያዬ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጎልኛል፤ ሩቅ ያሉትን በማስቀደም ስልክ በመደወልና በመዘጋጀት ዋልን:: (እናቴ ባለብዙ ዘመድ ባለብዙ ልጆችና የልጅ ልጆች እናት ናት፣ ነገር ግን እርሷን በመጦርና ሽምግልናዋ በመልካም እንዲጠናቀቅ እኔንና ዶ/ር ብርሃኑን የቀደመን ሌላ ሰው ስለሌለ ነፃነቱንም ያገኘነው ከዚህ የተነሳ እንደሆነ መግለጽ እወዳለሁ)::

አገልግሎቱም ተሰጠ የእናቴም አስክሬን በማግስቱ በተረጋጋ ሁኔታ ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ በክብር ተሸኘ:: ይህ ሲፈጸም አላዘንም፣ አላለቀስንም ከሰው ውጭ ሆነን ነበር፣ ማለት እንዳልሆነ ማንም ይረዳናል፤: ጌታን ስናገለግል አብረን የገጠመን ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነ ሁሉም ሰው ባይሆን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማገልገል የቆረጡና ነፍሳቸውን ሳይሰስቱ፣ ለማንነታቸው ሳይሳሱ፣ ወጉንና ማዕረጉን ወደጎን በማለት ጌታቸውን ለማገልገል የቆረጡ ሰዎች አይፈርዱብኝም፣ ይረዱኛል እንጂ ብዬ አምናለሁ:: እንደ ሰው ብዙ ያማል ያውም የእናት ሞት! ነገር ግን የዓላማ ጽናትና ውሳኔን ይጥይቃል:: መፈለግንም ማድረግንም በእኛ ውስጥ የሚፈጽም እግዚአብሔር ስለሆነ በእርሱ ጸጋ ሁሉንም እንድንፈጽም ረድቶናል፣ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን!!!

## የቤተሰቡ የአምልኮና የጸሎት ፕሮግራሞች

ጋብቻችንን ከፈጸምንበት ከሐምሌ 1975 ዓ.ም ጀምሮ ዶ/ር ብርሃኑ ወደ ጌታ እስከ ሄደበት የካቲት 2000 ዓ.ም. ድረስ ለብዙ ጊዜ በምሽቱ ክፍል፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በማለዳው ጊዜ ቤተሰቡ በአንድነት ሆኖ ነበር የሚጸልየው:: ሳይቋረጥ በየቀኑ ለሃያ

አራት ዓመት ከሰባት ወራት (ከዕሁድ በስተቀር) ለሁለት ሰዓታት ያህል የሚቆይ ነበር፡፡ ይህ ፕሮግራም በጣም የሚከበርና የሚወደድ ጊዜ ነበር፣ በቤት ውስጥ ሲኖር ጸሎቱን የሚመራው ዶ/ር ብርሃኑ ሲሆን እርሱ በማይኖርበት ጊዜ እኔ እሆናለሁ፡፡

ምናልባት ሁለታችንም ባንኖር በቤት ውስጥ ያለ በመንፈሳዊ ሕይወት ቀደም ያለ ሰው ይመራዋል፡፡ ስለፕሮግራሙ አካሄድ ሪፖርት ስለሚቀርብ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር በምንም መልኩ ፕሮግራሙ አይቋረጥም፡፡ ይህ ጸሎት ለሕይወታችን ዕድገት፣ ለብርሃኑ አገልግሎት ጸጋና ምሪት፣ ለሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች መፍትሄ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ከሕመማችን የምንፈወስበት፣ ከኀዘናችን የምንጽናናበት በአጠቃላይ ብዙ በረከቶችን ከእግዚአብሔር የተቀበልንበት መድረክ ነው፡፡ ስለዚህም በረከት ጌታን አመሰግናለሁ፡፡





# 9. ጨለማው ሲገፈፍ ፕሪዉ ደመቀ

## *9.1. ጨለማው ነጋ*

**እግዚአብሔር ይመራኛል፣**
**እግዚአብሔር . . .**
**እግዚአብሔር ይሸሽገኛል፣**
**እግዚአብሔር . . .**
**ከአንበሣ ግሣት - ከጠላት ጡጫ፣**
**እግዚአብሔር አለዉ መዉጫ፡፡**

*(የብርሃነ ወንጌል ቤ.ክ መዘምራን፤ 1972)*

በ1983 ዓ.ም እግዚአብሔር ታላቁን ተራራ በጠጠር/በጠጠሮች ሲንደው የደርግ መንግሥት አከተመለት፡፡ ይፋዊዉ የስደት ምዕራፍ ተዘጋ፡፡ በየቀበሌው፣ በየሰፈሩ፣ በየዱሩና በጫካው በትናንሽ ቡድኖች ተሰባስበው ክፉዉን ዘመን ያሳለፉት ሕብረቶች ከሞላ ጎደል ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንነት አድገዉና ተስፋፍተዉ ብቅ አሉ፡፡

በእብደት ሩጫዉ የፈረሱ፣ የተዘጉና የተወረሱ ቤተ ክርስቲያናት በፍጥነት ተከፈቱ፡፡ ቢሮክራሲዉ ወይም ልዩ ሁኔታዎች ባልፈቀዱበት ሁኔታ አዳዲሶች ህንፃዎችና አዳራሾች ተሠሩ፡፡ በቤት ውስጥ ማለት በጓዳና በሳሎን ተወስነው የነበሩት ሁሉ ወደ ትላልቅ ድንኳኖች ተለወጡ፡፡ በገጠር በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ በጫካና በዋሻ ውስጥ የነበሩት እልፍ ሆነው እየዘመሩ ወደ ሚያማክሏቸው ከተሞች ተመለሱ፡፡